ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ማክሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 001 መስከረም 1 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ



ሸህ ኢድሪስ አሊ



አቡነ ብርሃነ እየሱስ



ቄስ ዶክተር ዮናስ ይገዙ



ፓስተር ሰንበቶ ባሼ

## በአዲሱ ዓመት ችግሮች በውይይትና በሕግ እየተፈቱ የሀገርና የሕዝብ ሉዓላዊነት፣ ነጻነትና አንድነት መረጋገጥ አለበት

### - የሃይማኖት አባቶች

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- በአዲሱ ዓመት ችግሮችን በውይይትና በሕግ እየተፈቱ የሀገርና የሕዝብ ሉዓላዊነት፣ ነጻነትና አንድነት መረጋገጥ እንዳለበት የሃይማኖት አባቶች አሳሰቡ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ- ክርስቲያን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀጳጳስ ዘአኩስም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት የ2016 ዓ.ም አዲስ ዓመትን ምክንያት በማድረግ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ እንዳስታወቁት፤ በአዲሱ ዓመት የሰው ሕይወትን የሚቀጥፉ የመሳሪያ አፈ ሙዞች በሙሉ ወደ መጋዘን መግባት አለባቸው። ችግሮችን

በአዲሱ ዓመት ችግሮች ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## «ኢትዮጵያ በውጣ ውረድ ውስጥ እያሸነፈች ተጉዛለች»

### - ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በውጣ ውረድ ውስጥ እያሸነፈች ተጉዛለች ሲሉ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ የ2016 ዓ.ም የዘመን መለወጫ በዓልን አስመልክቶ ባስተላለፉት የእንኳን አደረሳችሁ መልእክት እንደገለጹት፤ ጽኑ መርሕ፤ ብርቱ ሕዝብና የማይሸነፍ አምላክ ስላለን እዚህ ደርሰናል።

እስካሁን ብዙ ነገሮችን አሳክተናል፤ አያሌ ፈተናዎችንም በድል ተወጥተናል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር)፤ እልፍ መሰናክሎች ቢደረደሩም ጠንካራ መሰረት ሆነውን አልፈዋል ብለዋል።

"የተሳኩልን ሁሉ የኅብረ ብሔራዊ አንድነታችን ውጤቶች

«ኢትዮጵያ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## አዲሱ ዓመት የሰላም እና የአንድነት እንዲሆን የመዲናዋ ነዋሪዎች ምኞታቸውን ገለጹ

ዳግማዊት አበበ እና ማህሌት ብዙነህ

አዲስ አበባ፡- አዲሱ ዓመት የሀገሪቱ ሰላም እና አንድነት የሚመለስበት እንዲሆን የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ያነጋገራቸው የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ምኞታቸውን ገልጸዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ የሆኑት ወይዘሮ ትዕግስት መኮንን ከዚህ በፊት በዘመን መለወጫ በዓል የነበረው ሽርጉድ ሰፊ መሆኑን አስታውሰው ዘንድሮ የተለመደውን ያህል ባይሆንም ጥሩ የበዓል ድባብ እንዳለ ገልጸዋል።

የባንክ ሰራተኛ የሆኑት ወይዘሮ ትዕግስት አዲሱ ዓመት ሀገሪቱ ወደ ቀድሞ ሰላሟ ተመልሳ የምንጠያየቅበት እና ዜጎቿ እርስ በእርስ ተደጋግፈን በፍቅር ተሳስበን የምንኖርበት ዓመት እንዲሆን መልካም ምኞታቸውን አስተላልፈዋል።

ሌላኛዋ በመዲናዋ በንግድ ስራ ላይ ተሰማርታ ያገኘናት ወጣት መአዛ በበኩሏ፤ አዲስ ዓመት አዲስ እቅድ

አዲሱ ዓመት የሰላም ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ወጣት መአዛ መኮንን



ወይዘሮ ትግስት



አቶ አስራት ታደሰ



አቶ አምባቸር ልዑልሰገድ

## አዲስ ዓመትን ስናከብር በአብሮነትና በመረዳዳት ሊሆን ይገባል

### - የሃይማኖት አባቶች

አመለወርቅ ከበደ

አዲስ አበባ፡- ምዕመኑ አዲስ ዓመትን በአብሮነትና በመረዳዳት ስሜት ሊያከብር እንደሚገባ የሃይማኖት አባቶች ገለጹ።

በቅድስት ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ የነገረ መለኮት መምህር አባ ጌዲዮን ብርሃነ ሊትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያውያን መለያ የሆነውን አዲስ ዓመትን በአብሮነት ስሜት ማክበር ያስፈልጋል።

የክርስትናም ሆነ የእስልምና እምነት ተከታዮች በጋራ በመደጋገፍ በዓሉን ማሳለፍ ከቻሉ አብሮነታችንን ማጠናከር ይቻላል ያሉት መምህሩ፤ የበዓሉን የአንድነት ተምሳሌትነት ማጠናከር ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

ሕዝቡ አብሮነትን ለሚያጠናክሩ ትብብሮች የበለጠ ዋጋ ሊከፍል ይገባል ያሉት መምህሩ፤ ትናንት የነበረውን የአንድነት ስሜት በመረዳት ለአዲሱ ዓመት ሁሉም ዜጋ ለአብሮነት መረባረብ ይኖርበታል ብለዋል።

ሕዝቡ አዲሱን ዓመት ሲያከብር ማዕድ ማጋራቱ እንዳለ ሆኖ ጊዜው የትምህርት መጀመሪያ እንደመሆኑ የትምህርት ቁሳቁስ የሚቸገሩ ተማሪዎችን ባለን አቅም መደገፍ ይገባል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

በተለያዩ ምክንያቶች የመማሪያ ቁሳቁስ አጥተው ከትምህርት ገበታ ውጪ የሚሆኑ ተማሪዎች መኖራቸውን የጠቆሙት መምህሩ፤ የተቸገሩትን ለመርዳት ህብረት መፍጠር እንደሚያስፈልግ አመላክተዋል።

በዕድሮች፣ በመንፈሳዊ ማህበራትና በሀገሪቱ የሚገኙ የተለያዩ ማህበራትን በመጠቀም በዘመቻ

አዲስ ዓመትን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል















ዜና



አቶ በላይ ደጀን

# አዲስ አበባን የሚመጥን ስብዕና ያለው ወጣት ለማፍራት እየተሰራ ነው

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- አዲስ አበባ የአፍሪካ መዲና በመሆኗ በስብዕና የታነጸ በእውቀት የጎለበተ ከተማዋን የሚመጥን ወጣት ለማፍራት ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ አቶ በላይ ደጀን ገለጹ።

የትውልድ ቀንን ምክንያት በማድረግ "አዲስ የክረምት በጎ የወጣቶች ፌስቲቫል" በሚል መሪ ሃሳብ የከተማው የወጣቶች ፌስቲቫል ጷጉሜን 5 ቀን 2015 ዓ.ም ተካሂዷል።

የአዲስ አበባ ከተማ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ አቶ በላይ ደጀን በእለቱ እንደተናገሩት፤ አዲስ አበባ የሁሉም ብሔር ብሔረሰቦች መገኛ እንዲሁም የአፍሪካ መዲና በመሆኗ ከተማዋን የሚመጥን በእውቀትና በሥነ ምግባር የታነጸ ብቁ ወጣት ማፍራት ወሳኝ ነው።

አቶ በላይ አክለውም አዲስ አበባ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ስብሰባዎች የሚካሄዱባት ከተማ በመሆኗ ባህል፣ ሃይማኖት እንዲሁም ቋንቋ ሳይለይ በአብሮነት የሚኖር ወጣት ማፍራት ያስፈልጋል ያሉ ሲሆን፤ ቢሮው ከከተማ አስተዳደሩ ጋር በመሆን ወጣት ተኮር ስራዎች እያከናወነ እንደሆነ ጠቁመዋል።

የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት ማዘመንና የወጣቶች ስፖርት ማዘውተሪያ ቦታዎች ማስፋፋት ላይ ሰፊ ሥራዎች ተሰርቷል ያሉት አቶ በላይ፤ በከተማው 510 የሚጠጉ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጓል ብለዋል።

እንደ ቢሮ ኃላፊው ገለጻ፤ በከተማው በ112 የወጣት ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት ከ18 በላይ አገልግሎቶች ሲሰጡ ቆይተዋል ያሉ ሲሆን፤ ቢሮው ወጣቶች የአዳዲስ ሃሳብ ፈጠራ ባለቤት እንዲሆኑ፣ በሥነ- ምግባር የታነጸና ከፍተኛ የሥነ-ልቦና ውቅር እንዲያጎለብቱ እንዲሁም በየሙያው ዘርፍ ተተኪ ባለሙያዎች ለማፍራት እየተሰራ ነው።

የስፖርት ማዘውተሪያዎቹ ተተኪ ስፖርተኞች ከማፍራት ባሻገር ወንድማማችነትና እህትማማችነት እንዲጎለብት የሚያስችል ነው ያሉት ቢሮ ኃላፊው፤ ከመደመር ትውልድ መጽሐፍ ሽያጭ 12 የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ተሰርተዋል ብለዋል።

አቶ በላይ አክለውም ፌስቲቫሉ ለልምድ ልውውጥ፣ የፈጠራ ሥራዎች ለማሳደግ፣ በከተማው ተተኪ የኪነ ጥበብ ባለሙያዎችና ልዩ ልዩ ባለተሰጦዎች ለማበረታታት እንዲሁም ጊዜያቸውን ባልባሌ ቦታዎች የሚያጠፉ ወጣቶች ወደ ወጣት ማዕከላት በመቅረብ ተጠቃሚ እንዲሆኑ እገዛ እንደሚያደርግ ተናግረዋል።

በፌስቲቫሉ ስፖርታዊ ውድድሮች፣ የኪነ ጥበብ ስራዎች፣ በከተማው ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ሲካሄድ የቆየው የወጣት ስብዕና መገንቢያ ማዕካት የኪነጥበባት የፍፃሜ ውድድርና የአሸናፊዎች ሽልማት፣ እንዲሁም በክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት ሲከናወኑ የነበሩ ተግባራት ለእይታ ቀርበዋል።

ወጣቶች የክረምት እረፍት ጊዜያቸውን አልባሌ ቦታዎች እንዳያውሉ በክረምት በጎ ፈቃድ ስራዎችን ላይ እንዲሳተፉ አድርጓል ያሉ ሲሆን፤ በአእምሮም በሰውነትም የጎለበተ ጤነኛ ወጣት ከማፍራት አኳያ ወደፊትም በትኩረት እንደሚሰራ ነው አቶ በላይ የተናገሩት።

# ኢፕድ ያዘጋጀው የፎቶ አውደ ርዕይ አዲሱ ትውልድ ታሪኩን እንዲያውቅ የሚያስችል ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**



ፎቶ፡ አሸናፊ ጉደታ

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ያዘጋጀው ስለኢትዮጵያ 14ኛው የፎቶግራፍ አውደ ርዕይ አዲሱ ትውልድ ታሪኩን እንዲያውቅ የሚያስችል በመሆኑ ቀጣይነት ሊኖረው እንደሚገባ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ገለጹ። አውደ ርዕዩ በአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ሲጎበኝ ቆይቶ ትናንት ተጠናቋል።

ስለ ኢትዮጵያ የፎቶግራፍ አውደ ርዕይ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጋር በመተባበር "አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ተምሳሌት" በሚል መሪ ሃሳብ የተዘጋጀ ሲሆን ከነሀሴ 29 ቀን 2015 ዓ.ም እስከ ጳጉሜን 6 ድረስ በነጻ ለዕይታ ክፍት ሆኖ ቆይቷል።

የፎቶግራፍ አውደ ርዕዩን ሲጎበኙ ያገኘናቸው የአዲስ አበባ ነዋሪ አቶ እንግዱ በላቸው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በአውደ ርዕዩ የአዲስ አበባ ከተማን የትናንት፣ የዛሬና የነገን ገጽታ እና በመዲናዋ እየተከናወኑ ያሉ ዘርፈ ብዙ አገልግሎቶችን የሚያሳዩ ፎቶ ግራፎች ለእዕይታ ቀርበዋል። ይህም አዲሱ ትውልድ ታሪኩን እንዲያውቅ የሚያስችል ነው። ስለዚህ ቀጣይነት ሊኖረው ይገባል ብለዋል።

ፎቶ ግራፎቹ የአዲስ አበባ ለውጥ ምን ያህል ፈጣን እንደሆነ የሚያሳዩ ናቸው ያሉት አቶ እንግዱ፤ በከተማዋ እየተሰሩ ያሉ የልማት ስራዎች ለወጣቱ ሰፊ እድል እንዳለ ተስፋ የሚሰጥ ነው። የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ማህበረሰቡ ስለኢትዮጵያ ማወቅ ያለበትን መሰረታዊ ጉዳዮች እንዲያውቅ የፎቶ ግራፍ አውደ ርዕዩን አጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት አሳስበዋል።

ሌላኛው የፎቶግራፍ ጎብኚ አቶ በቀለ ፈለቀ በበኩላቸው፤ አውደ ርዕዩ ቀጣዩ ትውልድ ካለፈው ታሪክ የሚማርበትና ለወደፊቱ የበለጠ ለመስራት የሚነሳሳበትን እድል የሚፈጥር ነው። ለሀገር፣ ለከተማ እና ለማህበረሰብ እድገት ሁሉን አሳታፊ ተግባር ማከናወን ወሳኝ ነው። በከተማዋ እየተሰሩ የሚገኙ እና በቀጣይ ሊሰሩ የታቀዱ ስራዎች ስኬታማ እንዲሆኑ ወጣቱ የበኩሉን አስተዋጽኦ ሊወጣ ይገባል ብለዋል።

አውደ ርዕዩን የመንግሥት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች፣ የክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈፃሚዎች፣ ሕፃናት፣ ወጣቶች እና አረጋውያን ሲጎበኙት ነበር ያለው ደግሞ የአውደ ርዕዩ አስጎብኚ ጋዜጠኛ አዲሱ ገረመው ነው።

እንደ ጋዜጠኛ አዲሱ ገለፃ፤ ጎብኚዎች አውደ ርዕዩን በሚመለከት መልካም አስተያየቶችን ሲሰጡ ነበር። በተለይ የእድሜ ባለጸጋ ጎብኚዎች በወቅቱ የነበራቸውን ትውስታ ሲነግሩን ነበር። የከተማዋ ለውጥ ፈጣን፣ ተጨባጭና ሊታይ የሚችል እንደሆነም ጎብኚዎቹ ተናግረዋል። የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የከተማዋን እና የሀገሪቷን ታሪክ ሰንዶ በማስቀመጥ ረገድ እየሰራ ያለው ሥራ የሚደነቅ መሆኑንም ገልጸዋል ብሏል።

ህዝብ ያልተሰሩትን ሥራዎች ከመተቸት ባለፈ የተሰሩ ሥራዎችን ማድነቅ እና መመስከር እንዳለበት ጎብኚዎቹ ተናግረዋል ያለው ጋዜጠኛ አዲሱ፤ ጎብኚዎች አዲስ አበባ ላይ ትልቅ ተስፋ እንዳላቸው እና የነገ ሀገር ተረካቢ ትውልድ ውብ እና ምቹ ከተማ ላይ እንደሚኖር በአውደ ርዕዩ መጨረሻ ላይ የቀረቡ ፎቶ ግራፎች ያስረዳሉ ብለዋል ሲል ተናግሯል።

የአውደ ርዕዩ አስተባባሪ ጋዜጠኛ ምህረት ሞገስ በበኩሏ፤ አብዛኛዎቹ ጎብኚዎች አውደ ርዕዩ የበፊቷን እና የአሁኗን አዲስ አበባ በትክክል ያሳየ መሆኑን ገልጸው አውደ ርዕዩ በጊዜ መወሰን እንደሌለበት እና ሁል ጊዜ መታየት እንዳለበት ተናግረዋል ብላለች።

# የበዓል ዘፈኖች ማህበረሰቡን ለተሻለ አዲስ ነገር የሚያነሳሱ ሊሆኑ ይገባል

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- አዲስ ዓመትን ጨምሮ ለበዓላት የሚዜሙ ዜማዎች ማህበረሰቡን ለተሻለ ነገር የሚያነሳሱ ሊሆኑ እንደሚገባ የኪነጥበብ ባለሙያዎች ገለጹ።

በሀገር ፍቅር ቴያትር የሙዚቃ ስቴጅ ማናጀር አቶ ነብዩ ግርማ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት ለበዓላት የሚዜሙ ዜማዎች ማህበረሰቡ በፖለቲካዊ፤ በማህበራዊ እና በኢኮኖሚው ዘርፍ ለተሻለ ነገር እንዲነሳሳ የሚያደርጉ ሊሆኑ ይገባል።

አዲስ ዓመት በሰዎች ልብ ተስፋን የሚጭር እና መነሳሳትን የሚፈጥር ነው። በመሆኑም የሚዜሙ መዝሙሮች ለለውጥ የሚያነሳሱ መሆን ይኖርባቸዋል ሲሉ ተናግረዋል።

በተጨማሪም አቶ ነብዩ እንደተናገሩት ሙዚቃ አንድነትን ከማጠናከር አኳያ ትልቅ ሚና ስላለው ህብረተሰቡ ነገ ምን ይመጣል በሎ ከመጨነቅ ይልቅ ነገ ምን ልስራ ብሎ እንዲያስብ እና እንዲሰራ ሰላምን የሚሰብኩ መዝሙሮች መሆን አለባቸው።

በሀገር ፍቅር ትያትር የትወና እና የተውኔት ጥበባት ቡድን መሪ አርቲስት ሰለሞን ሐጎስ በበኩላቸው በዓልን አስመልክቶ የሚዜሙ ዜማዎች ሀገርን በሚገነባ ነገር ላይ የሚያጠነጥኑ መሆን አለባቸው ሲሉ ገልጸዋል።

ጥላቻን እና አግባብ ያልሆኑ መልእክቶችን የሚያስተላልፉ ሙዚቃዎች ሀገርን የሚያፈርሱ መሆናቸውን በመገንዘብ፤ ሀገራዊ እሳቤ ኖሮዋቸው ለሥራ የሚያነሳሱ ሰላምን የሚሰብኩ፤ እውቀትን የሚያስጨብጡ እና ማህበረሰብን የሚያንጽ መልክት ያላቸውን ስራዎች መስራት ሚናው የጎላ ነው ብለዋል።

ከከፉ ነገሮች ጭምር መማር ይቻላል ያሉት አርቲስት ሰለሞን ዘፈኖች የሚገለጹባቸው መንገዶች ማህበረሰቡን የሚያስተምሩ ሊሆኑ እንደሚገባ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ የተለያየ ባህል እና ቋንቋ ያላት ሀገር እንደመሆኑዋ በተለያዩ ባህሎች በርካታ በዓላት ይከበራሉ። እነዚህንም የበዓላት አከባበር የሚገልጹ በርካታ ዘፈኖች መዜማቸውን አንስተዋል።

ኢትዮጵያ ዓለም ላይ ካሉት ሀገራት የራሷ የዘመን አቆጣጠር ያላት ሀገር እንደመሆኑዋ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በመስከረም ወር አዲስ ዓመትን ይቀበላል።

በዚህም የመስከረም ወርን አስመልክቶ በርካታ የሀገሪቱ ገጣሚዎችና ዘፋኞች ግጥሞችን፤ የበዓል መዝሙሮችን ሰርተዋል።። እነዚህም ዘመን የማይሽራቸው እና በማህበረሰቡ ሕይወት ላይ አዲስ ተስፋን የሚጭሩ ናቸው ሲሉ አስረድተዋል።

የበዓል ዘፈኖች ማህበረሰቡ ውስጥ በጎ የሆነ ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ የተናገሩት ቡድን መሪው፤ በዚህም ማህበረሰቡ የአዲስ ዓመት ዘፈኖችን ሲሰማ የራሱ የሆነ የዘመን አቆጣጠር፤ ቋንቋ እና ሥርዓት ያለው ህዝብ መሆኑ ይሰማዋል ሲሉ ተናግረዋል።።

አርቲስት ሰለሞን እንደተናገሩት የበዓል ዘፈኖችን የበለጠ ለማሳደግ እና ብቁ ለማድረግ በዘርፉ የሚሰሩ አካላት በሀገሪቱ የሚገኙ የተለያዩ ባህሎችን ጥናት በማድረግ በጥልቀት መረዳት ያስፈልጋል።

እያንዳንዱ ብሄር የራሱ የሆነ የግጥም አጻጻፍ፤ ዘዬ



አቶ ነብዩ ግርማ



አርቲስት ሰለሞን ሐጎስ

አለው።። እነዚህን ተንትኖ መረዳት ዘፋኙ የተሻለ ሃሳብ እንዲኖረው ይረዳል ሲሉ አስረድተዋል።።



# በአዲስ እቅድና አስተሳሰብ ወደ አዲስ ማንነት መሸጋገር ይገባል

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- ከአሮጌው ዓመት በጎዎቹን በማስቀጠል፣ መጥፎዎቹን ነቅሶ አውጥቶ በመጣል በ2016 ዓ.ም በአዲስ እቅድና አስተሳሰብ ወደ አዲስ ማንነት መሸጋገር እንደሚገባ መላከ ሕይወት ቆሞስ አባ ወልደ እየሱስ ሰይፉ ገለጹ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የቋሚና ጊዜያዊ ፕሮጀክት መምሪያ ሃላፊ መላከ ሕይወት ቆሞስ አባ ወልደ እየሱስ ሰይፉ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት፤ አዲሱ ዓመት የአንድነት፣ የከፍታ፣ የበጎነት፣ የመግባባት፣ የመፋቀርና ወደ አዲስ ማንነት የመሸጋገር ዘመን እንዲሆን ተመኝተዋል።

በአንድነት አዲስ ዓመትን መቀበል ይገባናል። ኢትዮጵያ አልጠበበችንም። የጠበበው የሰው አስተሳሰብ ነው። ምድሪቱ ሰፊ፣ የበረከት ሀገር ናት። በሃይማኖት፣ በዘር፣ በጎሳና በቋንቋ መከፋፈል ቀርቶ መተባበርና መከባበርን ማጠናከር ይገባናልም ብለዋል።

በበጎነት፣ በመልካምነት፣ በመራራት፣ በአብሮነት የሚኖርባትን ምድር መፍጠር እንደሚያስፈልግ፣ መደማመጥና መከባበር ባህል እንዲሆን፣ የሰው ልጆች መብት ክብር እንዲያገኝ ማድረግ እንደሚገባ፣ ከክፉ ልምምድ በመውጣት አንድ መሆን እንደሚያስፈልግም ነው ያሳሰቡት።

የታሪክና የቅርስ ባለቤት፣ ሃይማኖተኛ ሀገር ሆነን በመከፋፈል፣ በመገፋፋት የምንኖርበት መሆን የለበትም። ጨዋ ኢትዮጵያዊነት ሥነምግባርን መመለስ ያስፈልጋል ብለዋል።

በሃጥያታችን ፣ በጎጠኝነትና በቋንቋ ምክንያት ተሰብረናል፤ በመሆኑም ኢትዮጵያውያን ወደ እግዚአብሄር መንገድ መመለስ ይገባናል። መጥፎ ነገርን በመተው ወደሃይማኖት፣ ወደ ጽድቅና በጎነት መመለስ ያስፈልገናል ሲሉም መክረዋል።

ነዳያንን በማገዝ፣ ያለው ለሌለው በማካፈል፣ አብሮ በመብላትና በመጠጣት፣ ከጎረቤቶች ጋር በፍቅር ማሳለፍ እንደሚገባም ነው የተናገሩት።

ድር ሲገመድ ሃይል ኖሮት ሃያሉን አንበሳ ያስራል ያሉት መላከሕይወት ቆሞስ አባ ወልደ እየሱስ፤ አንድነታች በብዙ መንገድ ተሸርሽሯል፣ ፍቅረ ንዋይ በዝቷል፣ የፍላጎት ጥግ ርቋል ብለዋል። ይህን በማስተካከል አርአያ መሆን ይገባል። ከመለያየት ይልቅ አንድነት ይሻለናል ብለዋል።

በ2015 ዓ.ም ብዙ የፈተና እና የበጎነት ጊዜ አልፏል። ያሳለፍነው መነቋቆር፣ መከራ ከነግሳንግሱ ትተን በጎውን ብቻ ይዘን በአዲስ መንፈስ፣ በአዲስ ራዕይ፣ በአዲስ ተስፋ ወደ 2016 ዓ.ም ልንሻገር ይገባል ሲሉም ተናግረዋል።

ከዘመን ዘመን መሸጋገር እንደስራችን ሳይሆን እንደምህረቱ ያገኘነው ነው። አዲስ ዓመት አዲስ ማንነት፣ አዲስ እቅድ የሚታቀድበት፣ አዲስ ሕይወት የሚታሰብስበት እና ነገን ተስፋ አድርገን የምናይበት ይሁንልን ሲሉም ተመኝተዋል። በዕድሜያችን ዓመታትን የሚጨመሩልን ያልሰራነው እንድንሰራ፣ ያላየነውን እንድናይ፣ ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም እንድንኖር ነው ብለዋል።

ጎጠኝነቱ፣ አንዱ በአንዱ ላይ መነሳቱ፣ በፖለቲካ እና በሃይማኖት ተቋማት መገፋፋት አይጠቅመንም። እንዲህ አይነት ተግባር ለአማኝ የሕይወት ጨለማ፣ በድንግዝግዝ ውስጥ እንደመጓዝ ነው። ካለፈው ትምህርት በመውሰድ መተባበርን ማጎልበት ይገባናል ብለዋል።

የሰው ሕይወት ጠፍቷል፣ አካል ጎድሏል፣ ንብረት ወድሟል፣ ብዙዎች ተፈናቅለው በሸራ ተጠልለው የሚገኙትን ልናስብ ይገባናል ሲሉም አሳስበዋል።

አሮጌውን ዓመት አሳልፎ ወደ አዲስ አመት ስላሸጋገረን ማመስገን ይገባናል። አዲሱ ዓመት ሕይወታችን የሚቀየርበት፣ አገር የምንለውጥበት፣ የአባቶቻችንን ታሪክ ጠብቀን ለቀጣይ ትውልድ የሚተላለፍ ታሪክ የምንሰራበት ዓመት እንዲሆንም ተመኝተዋል።

በተጠናቀቀው ዓመት አቅደን ያልጨረስነው እና ያልሰራነውን ለማጠናቀቅ መነሳሳት ያስፈልጋል ያሉት መላ ህይወት፤ እንኳን ወደ 2016 ዓ.ም በሰላም፣ በጤና በሕይወት ጠብቆ አሸጋገራችሁ በማለት የመልካም ምኞታቸውን ገልጸዋል።

# «ከአባቶች የተረከብነውን የአብሮነት እሴት ለሀገር ሰላምና አንድነት ማዋል ይገባል»

- ሸህ ኢድሪስ አሊ

**አማን ረሺድ**



አዲስ አበባ፡- ከአባቶች የተረከብነውን የአብሮነት እሴት ለሀገር ሰላምና አንድነት ልናውለው ይገባል ሲሉ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት የፈትዋ (ብይን)ና የምርምር ዘርፍ ኃላፊ ሼህ ኢድሪስ አሊ ገለጹ።

ሸህ ኢድሪስ አሊ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አባቶች ከዚህ ቀደም ጠብቀው ያቆዩትን የአብሮነት እሴት ወጣቱ ትውልድ ለሀገር ሰላምና አንድነት ማዋል አለበት።

ለሰው ልጅ የአብሮነት የሕይወት ዑደት መተዛዘን፣ መዋደድና መከባበር መሠረት መሆኑን የጠቆሙት ሼህ ኢድሪስ፤ ወጣቱ ትውልድ የብሔርና የሃይማኖት ልዩነት ሳይገድበው ሰውነትን በማስቀደም አብሮነቱንና አንድነቱን በሚያጠናክሩ ጉዳዮች ላይ ማተኮር ይኖርበታል ብለዋል።

በዚህም ትውልዱ በሁሉም አካባቢ ተንቀሳቅሶ በአብሮነት እንዲሰራ ከተደረገ ከራሱ አልፎ የሀገርን ሁለንተናዊ ዕድገትና ብልፅግና ማምጣት እንደሚችል ሼህ ኢድሪስ አስረድተዋል።

በአብሮነት ስሜት ኢትዮጵያ ሰላምን በማድረግ ሕዝቦች ከችግር የሚወጡበት እንዲሁም ለጦርነት የሚወጣ ሀብት የሰውን ሕይወት ወደሚለውጡ የተለያዩ የልማት ሥራዎች ማዋል ይቻላል ብለዋል።

ዜጎች ፈጣሪ ያዘዘውን ትዕዛዝ በማክበርና ከመንግሥት ጋር ተቀራርበ ለችግሮች መፍትሄ በመፈለግ ውጤት ማምጣት ይችላሉ ሲሉ ሼህ ኢድሪስ ገልጸዋል።

የሃይማኖት አባቶችና የሀገር ሽማግሌዎች በሰዎች ዘንድ ተሰሚነታቸው ትልቅ በመሆኑ መንግሥት ከነዚህ አካላት ጋር በትብብር መስራት እንዳለባቸው ጠቁመዋል።

ዘረኝነትንና ጎጠኝነትን አባቶቻችን አልተጠቀሙበትም፤ ወጣቱ ትውልድም ከዚህ ክፉ ሃሳብ በመራቅ እና ሀገርን ለመጥፎ ሰዎች ባለመተው የተሻለች ኢትዮጵያን ለመገንባት መተባበር እንዳለባቸው ሼህ ኢድሪስ አስረድተዋል።

ከሚያለያዩን ነገሮች ይልቅ በርካታ የሚያስተሳስሩን ጉዳዮች ስለሚበልጡ ሰላማችንና አንድነታችንን በማስቀድም አብሮነታችንን ማስቀጠል ይገባል ብለዋል።

ለዘመናት በወንድማማችነትና በአንድነት ተሳስሮ በኖረው ህብረተሰብ መካከል ልዩነትና ጥርጣሬ እንዲኖር የሚያደርጉትን አካላት በመገሰፅና በመቃወም ዜጎች ፊታቸውን ወደ ልማት እንዲያዞሩ የሃይማኖት አባቶችና የሀገር ሽማግሌዎች የበኩላቸውን ድርሻ መወጣት እንዳለባቸውም ሼህ ኢድሪስ አስገንዝበዋል።

በአብሮነታችን ለሌሎች ምሳሌዎች መሆን አለብን ያሉት ሼህ ኢድሪስ፤ ወጣቶች የአባቶቻቸውን አብሮነት እንዲያስቀጥሉ ሁላችንም ጥረት ልናደርግ ይገባል ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

# አብሮነት ኢትዮጵያን ያጸና እሴት ነው

**መስከረም ሰይፉ**



**ወርቅነሽ ብሩ**

አዲስ አበባ፡- አብሮነት ኢትዮጵያን ያጸና እሴት መሆኑን የባህልና የስፖርት ሚኒስቴር ገለጸ።

የባህልና የስፖርት ሚኒስቴርና ተጠሪ ተቋማት በአብሮነት ቀን የተሰየመውን ጳጉሜን ስድስት ቀን በኢትዮጵያ የስፖርት አካዳሚ በተለያዩ መርሀ ግብሮች በትናንትናው እለት አክብረዋል።

የባህልና የስፖርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ወርቅነሽ ብሩ እንደገለጹት፤ አብሮነት ለኢትዮጵያውያን አብሯቸው የኖረና በእያንዳንዱ የኑሮ ዘዴያቸው የሚስተዋል እሴት ነው።

ሚኒስትር ዴኤታዋ ቀደምት አባቶች የተለያየ ባህል፣ ሃይማኖት ፣ ቋንቋ ያላት ሀገርን በአብሮነት አጽንተው አቆይተዋልና የአሁኑም ትውልድ ይህንን በመረከብ የጋራ እሴቶችን ማጽናትና ማስቀጠል እንደሚገባ ተናግረዋል።

ብዝሀነት በሚታይባት ኢትዮጵያም አቅም የሌላቸው ወገኖችን ለመደገፍ ፣ ቅሬታዎችን በባህላዊ መንገድ ለመፍታት እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ላይ እልባት ለማግኘት የሚያስችሉ እሴቶችን የተማሩ አባቶች በጽሁፍ ያልተማሩ በቃላቸው ከትውልድ ወደ ትውልድ አስተላልፈዋል። ለዚህም ባህላዊ የእርቅ ሥነ ሥርዓት ፣ እቁብ ፣ እድር የመሳሰሉ እሴቶች ምስክር ናቸው ብለዋል።

ወ/ሮ ወርቅነሽ ሀገሪቱ የቆመችው በትልቅ የአብሮነት ምሰሶ ነው ያሉ ሲሆን ባለፉት ጊዜያት ኢትዮጵያን ሊያጠቁ የሚፈልጉ የውጭም የውስጥም ሃይሎች በአብሮነት መረታታቸውን ገልጸው በቀጣይም ሀገሪቱ የሚያጋጥሟትን ችግሮች በአብሮነት መንፈስ በመስበር ሀገሪቱን ካጋጠማት ችግር ማሻገር እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል።

አብሮነት የሁሉ ነገር መሰረት ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ ማህበረሰቡ ከብሄር መሰረት ጀምሮ በጋራ በመሆን ችግሮች የሚፈቱበትና አብሮነትን የሚያስቀጥልበት መንገድ ላይ መወያየት አስፈላጊ መሆኑን ጠቁመዋል።

በአዲሱ ዓመትም ኢትዮጵያ ከደረሰባት መከራ ሁሉ ወጥታ ከጠባቂነትና ከጥላቻ መንፈስ ለመላቀቅ ያንዱን ማንነት አንዱ ማክበርና የሰላም፣ የአብሮነት እና የፍቅር እሴቶችን ማጎልበት አስፈላጊ መሆኑን ተናግረዋል።

ወ/ሮ ወርቅነሽ አብሮነት በዚህ ዘመን አባቶች ባስተላለፉት ልክ አለ ወይ የሚለው ሲታይ በርካታ አጠያያቂ ጉዳዮች ይነሳሉ ያሉ ሲሆን በተለይም ከቴክኖሎጂና ከዘመናዊነት ጋር በተያያዘ በሀገሪቱ የአብሮነት እሴት እየተሸረሸረ መሆኑ ማሳያዎች አሉ ብለዋል።

ይህን አስመልክቶም እድገትና ለውጥ አይምጣ ባይባልም የምንጠቀምባቸውን ቴክኖሎጂዎች ከውጭው ዓለም በቀጥታ ከመቀበል ይልቅ ለኛ የሚሆን ነው ወይ ብሎ መገምገም አስፈላጊ መሆኑን ጠቅሰዋል።

ሚኒስትር ዴኤታዋ ኢትዮጵያን ወደ ኋላ የሚያደርጉ ሃሳቦችን በመስበር ካጋጠሟት ችግሮች በጋራ ልናወጣት ይገባል ሲሉም መክረዋል።

# ቢሮው የትውልድ ቀንን በቢሾፍቱ ከተማ አከበረ

በጋዜጣው ሪፖርተር

ቢሾፍቱ፡- የኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ ከክልሉ ስቴት ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር የትውልድ ቀንን በቢሾፍቱ ከተማ በልዩ ልዩ መርሃግብሮች አከበረ።

በመርሃግብሩ ላይ የተገኙት የክልሉ የትምህርት ቢሮ ምክትል ሃላፊ አቶ ግርማ ባይሳ እንደገለጹት ትውልድ ካልተገነባ ሀገር ሊቀጥል አይችልም፤ ሀገርንም የሚፈለገው የእድገት ደረጃ ላይ ማድረስ አይቻልም።

ከዚህ በመነሳት የኦሮሚያ ክልል የትምህርት ሥርዓቱ ቀጣዩን ትውልድ ማዕከል ያደረገና ዘላቂ እድገትን ሊያመጣ በሚችል መልኩ እዲቀረጽ በማድረግ ከፍተኛ ሥራ እየተሰራ መሆኑን የጠቀሱት አቶ ግርማ፤ በዚህም በትምህርት ሥርዓቱ ላይ ከፍተኛ ስራ እየተሰራ ነው ብለዋል። ዛሬ የሚገነባ ትውልድ ሀገርን ለማሻገር ትልቅ አቅም እንደመሆን የጠቀሱት አቶ ግርማ በዚህ ሂደት ውስጥ ትምህርት ወሳኝ ሚና እንዳለውም ጠቁመዋል።።

ከዚህ በመነሳትም ሀገሩን የሚያውቅ፣ የሚወድና የሚንከባከብ ትውልድ ለመገንባት እየተሰራ መሆኑን አብራርተዋል።

የኦሮሚያ ስቴት ዩኒቨርቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ገረመው ሁሉቃ በበኩላቸው ትውልድ ላይ መስራት የሀገር ግንባታ ላይ መስራት መሆኑን በመጥቀስ በክልሉ ከፍተኛ ስራ እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል።

ሀገር የሚገነባው በትውልድ ቅብብሎሽ መሆኑን የጠቀሱት ዶክተር ገረመው፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የመደመር ፍልስፍናም በዚሁ ላይ የተመሠረተ መሆኑን ጠቁመዋል።

የመደመር ትውልድን ለመፍጠር ቤተሰብ፣ ማህበረሰብና ሚዲያ ሃላፊነት እንዳለባቸው በመጥቀስም ሁሉም በዚህ ሂደት ውስጥ የበኩላቸውን ሃላፊነት እንዲወጡ ጥሪ አቅርበዋል።

በእለቱ በዚሁ ዙሪያ ጥናታዊ ጽሁፍ ያቀረቡት ዶክተር ፍቃዱ ደረጀ እንደገለጹት፤ አንድ ሰው ከተወለደ በኋላ በቅድሚያ ከቤተሰብ ይማራል። በዚህ ውስጥ ቤተሰብ ፤ ትምህርት ቤት ብሎም ማበረሰብ ትልቅ ድርሻ አላቸው ብለዋል።

ትውልዱ አንድ መሰረት ላይ ቆሞ ተገቢው እድገት እንዳያመጣ በየጊዜው ሲለዋወጥ የነበረው የፖለቲካ አካሄድ የራሱ አሉታዊ ተጽዕኖ መፍጠሩን የጠቀሱት ዶክተር ፍቃዱ፤ ለአብነትም ካለፈው ግማሽ ምዕተ ዓመት ወዲህ ብቻ እንኳን የነበረውን ብንመለከት በደርግ ዘመን ሶሻሊዝም፤ ከዚያ ቅይጥ ኢኮኖሚ፤ በኢህአዴግም በተመሣሣይ መጀመርያ ሶሻሊዝም ፣ ከዚያ በአንድ ወቅት ነጭ ካፒታሊዝም የሚሉ አመለካከቶች ነበሩ ብለዋል። እነዚህ ደግሞ ከውጭ የተቀዱ መሆናቸው ሌላው ተግዳሮት እንደነበር አንስተዋል።

ሆኖም በአሁኑ ወቅት ትውልድና የሀገርን እውቀት መሰረት ያደረገ የመደመር ፍልስፍና ተግባዊ መሆኑን አብራርተዋል። እንደዚህ አይነት ሀገር በቀል እውቀቶች ለትውልድ ግንባታ ጠቃሚ መሆናቸውም ጠቁመዋል።

ሌላው ጥናታዊ ጽሁፍ ያቀረቡት አቶ ደረጀ ተርፋ በበኩላቸው ፤ ትውልድ የሚፈለገውን ለውጥ እንዲያመጣ እውቀት፣ ሥነምግባርና ቁርጠኝነትያስፈልጋል ብለዋል።

በተለይ የውጭ ጫና በትውልዱ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እየፈጠረ መሆኑን የጠቀሱት አቶ ደረጀ እንዲህ አይነት ተጽዕኖዎችን ለመቋቋም በትምህርት ሥርዓቱ ላይ መስራት ተገቢ መሆኑን አብራርተዋል።

ከዚህ በመነሳትም የኦሮሚያ ክልል የህዝቡ ከፍተኛ እሴት የሆነውን የገዳ ሥርዓት በትምህርት ሥርዓት ውስጥ በማስገባት ትውልዱን ለመቅረጽ እየሰራ መሆኑም አብራርተዋል።

በእለቱ አባገዳ ጎበና ሆላ በሰጡት አስተያየት ኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ በትውልዱ ላይ እየሰራ ያለው ስራ አመርቂ መሆኑን በመጠቆም ለነገው የተሻለ ሀገር ዛሬ እየተሰራ ያለው ስራ የሚመሰገን ነው ብለዋል።

በመርሃግብሩ ላይ አባገዳዎች፣ ሃደስንቄዎች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ ጥሪ የተደረገላቸው ልዩ ልዩ የመንግሥት የስራ ሃላፊዎች፣ ምሁራንና ተማሪዎች ተገኝተዋል።

# አዲስ ዓመትን ስናከብር...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

መልከ የመማሪያ ቁሳቁሶችን ማሰባሰብና ተማሪዎች ከትምህርት ገበታቸው እንዳይለዩ ማድረግ ይገባል ብለዋል።

የተቸገሩ ዜጎችን ካልረዳንና ካልደገፍናቸው በልባቸው የሚበቅለው ፍቅር ሳይሆን የጭቆናና የመገፋት ስሜት ነው ያሉት አባ ጌዲዮን፤ አብሮነትን ሳናሳያቸው ካደጉ ለሀገር ወዳጅ ይሆናሉ ብሎ ማሰብ ያልዘሩትን እንደማጨድ ነው ሲሉ ተናግረዋል።



አባ ጊዲዮን ብርሃኑ

አባ ጌዲዮን እንዳመለከቱት፤ አብሮነትን ለማጎልበት ሕዝቡ ቆም ብሎ አብሮነቱን እየሸረሸሩ ያሉ ነገሮች ምን እንደሆኑ በማሰብ የመረዳት ባህሉን ሊያሳድግ ይገባል።

በመጨረሻም አባ ጌዲዮን ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ አዲሱ ዓመት የሰላም፣ የፍቅርና የጤና እንዲሆን ምኞታቸውን ገልጸዋል።



ኡስታዝ አቡበከር አህመድ

የእስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት ፕሬዚዳንት አማካሪ ኡስታዝ አቡበከር አህመድ በበኩላቸው፤ አዲስ ዓመት የሰው ልጅ ህልሙን ለማሳካት አዲስ ምዕራፍና ዕድል የምናገኝበት በመሆኑ ፈጣሪን በማመስገን በአብሮነት ልናሳልፈው ይገባል ብለዋል።

በአዲስ ዓመት በአብሮነት ስሜት ከራስ አልፎ ለሀገርና ለማህበረሰብ የተሻለ ነገር ለማምጣት ማሰብና መስራት ያስፈልጋል ሲሉ ተናግረዋል።

ኡስታዝዝ አቡበክር እንዳመለከቱት፤ እንደሀገር የሚበጀው አብሮነት በመሆኑ መደጋገፍን በማጠናከር ለችግሮቻቸው የመፍትሄ አካል ለመሆን ወስኖ መንቀሳቀስ ይገባል ።

እንደ ሀገር የሚበጀን ተከባብረንና ተደጋግፈን ለጋራ ዕድገታችን ጥረት ማድረግ ነው ያሉት ኡስታዝ አቡበከር፤ አዲሱን ዓመት ስናከብርም ሌላው ምን አድርጓል የሚለውን መመልከት ሳይሆን ወደራሳችን በመመልከት እኔ ለአብሮነታችን ምን አበርክቻለሁ የሚለውን ማሰብ ይገባናል ብለዋል።

የሰው ልጅ ሲኖር ለእራሱ ስለኖረ ኖረ አይባልም ያሉት አማካሪው፤ እንደማህበረሰብ እርስበስርስ በመረዳዳት ችግራችንን በጋራ መፍታት እንደሚገባ ጠቁመዋል።

ሰጪነት ፈጣሪ የሰጠን ዕድል ስለሆነ በአዲሱ ዓመት የተፈናቀሉ ዜጎችን በመርዳት፣ የፈሰሱ እንባዎችን በማበስና የተሰበሩ ልቦችን በጋራ በመጠገን ልናሳልፍ ይገባል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

# «ኢትዮጵያ በውጣ ውረድ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ናቸው፤ የተፈተንባቸው ደግሞ በመለያየት የተነሳ የመጡ ናቸው" ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ በቀጣዩ ዓመትም ፈተናዎቻችን እጅግ ቀንሰው ፤ ኅብረ ብሔራዊ አንድነታችን ከአልማዝ ጠንክሮ ፤ የኢትዮጵያን ሰላምና ደኅንነት በጽኑ መሰረት ላይ እናጸናዋለን ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) በመልዕክታቸው ልማትና ብልጽግናዋንም ወደሚመጥናት ደረጃ እናሸጋግረዋለን፤ አዲሱ ዓመትም የኢትዮጵያ ብልጽግና ዓመት እንዲሆን እመኛለሁ ብለዋል።

# በአዲሱ ዓመት ችግሮች በውይይትና...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በውይይት፣ አሊያም በሕግ እየተፈቱ የሀገርና የሕዝብ ሉዓላዊነት ነጻነትና አንድነት መረጋገጥ አለበት።

ሀገርንና ሕዝብን ለዘለቄታው በአንድነት ለማስቀጠል የሕግ የበላይነትን ማክበር፣ እኩልነትን ማረጋገጥ፣ የጋራ ተጠቃሚነትን እውን ማድረግ፣ የተጐዳውን መደገፍ፣ ሆድ የባሰውን ማለዘብ፣ የተጠቃውን ማጽናናት ይገባል ያሉት ፓትርያርኩ፤ በአዲሱ ዓመት ይህንን ለማድረግ በቁርጠኝነት ከተነሣን ሰላማችን ወደነበረበት ይመለሳል ፤ ሀገራችንም በበረከት ትሞላለች ብለዋል።

ስለዚህም ኢትዮጵያውያን የሆናችሁ ልጆቻችን ሁሉ ይህንን ጥሪያችንን ተቀብላችሁ የጥፋት መሳሪያችሁንም አስቀምጣችሁ ወደ ሰላም ማእድ ቀርባችሁ በወንድማማችነት መንፈስ ችግራችሁን በክብ ጠረጴዛ በውይይት በመፍታት የሀገሪቱንና የሕዝቡን አንድነት እንድታስቀጥሉ ሁሉን በሚያይ እግዚአብሔር ስም እንማጸናችኋለን ሲሉ አሳስበዋል።

የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት የፈትዋ (ብይን)ና ምርምር ዘርፍ ኃላፊ ሽህ ኢድሪስ አሊ በበኩላቸው፤ ባለፈው ዓመት ያሳለፍናቸውን መጥፎ ነገሮች በመተው መልካም ነገሮችን በመያዝ ወደ ሚቀጥለው አዲስ ዓመት መሸጋገር ይኖርብናል ብለዋል።

ባለፈው ዓመት መስኪድና ቤተክርስቲያን ላይ የተለያዩ ችግሮች ተከስተዋል፣ የሰው ልጅ ሕይወት በግፍ ተነጥቋል፣ መፈናቀል ደርሷል፣ የንብረት ውድመትና አፀያፊ ድርጊቶች ተፈፅመዋል ያሉት ሽህ ኢድሪስ አሊ፤ በአዲስ ዓመት በፈጣሪ ዘንድ የሚያስጠይቁ ድርጊቶችን ባለመፈጸም አብሮነትን ማጠናከር አስፈላጊ መሆኑን አስረድተዋል።

ከሚለያዩን ነገሮች ይልቅ ወደ ሚያግባቡን ነገሮች ትኩረት በማድረግ ሰላሟ የተረጋገጠ ሀገር እንዲኖረን መስራት ያስፈልጋል ያሉት ሽህ ኢድሪስ፤ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በዓሉን ሲያከብር የተቸገሩ ወገኖችን በማሰብ ሊሆን ይገባል። አዲስ ዓመት የሰላም፣ የአንድነትና የመከባበር እንዲሁም የኢትዮጵያ ከፍታ የሚረጋገጥበት እንዲሆን ተመኝተዋል።

የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ብጹዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነኢየሱስ በበኩላቸው፤ አዲሱ ዓመት መልካም ታሪኮችን የምንተርክበትና የምንፈጽምበት እና የጥላቻ ትርክቶችን በበጎ ትርክቶች እንዲተኩ የበኩላችንን ጥረት የምናደርግበት ሊሆን ይገባ ብለዋል። አዲሱን ዓመት ሁላችንም በጸጋና በምስጋና፤ በትህትናና በተስፋ ብንቀበለው ወደ ማመስገን ከፍ ያደርገናልም ብለዋል።

አቡነ ብርሃነ እየሱስ "የተወደዳችሁ ወገኖች፤ እርስ በእርሳችን በመገፋፋትና በመጋጨት መጠፋፋትንና መገዳደልን የምናስተናግድ ሆነናል። ሁሉም ባለድርሻ አካላት በሁሉም መስክ በአስተዋይነትና በጥበብ ነባራዊውን የጥፋት ሁኔታ ከባለፈው የስቃይ ጊዜ በመማር እና የሁሉንም የሀገሪቱ ህዝቦች ድምጽ በመስማት የወንድማማቾችን ግጭት በህዝቦች ውይይት፣ በእርቅና በሰላም ብሎም በእውነትና በመቻቻል መንፈስ ማስከን ይገባናል" ሲሉም መልዕክታቸውን አስተላፈዋል።

ዜጎች በሰላምና በደስታ በልማትና በሥራ እንዲተጉና እንዲሳተፉ ታዳጊ ልጆችም በተስፋና በፍቅር የሚያድጉባት ሀገር እንድትኖረን ተግተን እንስራ ሲሉም አሳስበዋል።

አሁን ሀገራችን ላጋጠማት የሰላምና የጸጥታ መደፍረስ፤ እንዲሁም ለዘርፈ ብዙ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶች መፍትሄው በኛው እጅ አለ ያሉት ደግሞ የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ ፕሬዚዳንት ቄስ ዶክተር ዮናስ ይገዙ ናቸው።

ላጋጠመን ሀገራዊ ችግሮች የመጀመሪያው መፍትሄ የልብ ቅንነት ነው። ቅን ልብ ቅንነትን ለማብዛት ይጥራል፤ ችግሮችንም ሳይሸሽ ችግሮቹን ወደ በጎ ለመለወጥ ይተጋል። ታዲያ ራሳችንን እንደቅኖች እናስብና ስላለንበት ሁኔታ ራሳችንን እንጠይቅ ነው ያሉት ቄስ ዶክተር ዮናስ።

እንደ ፕሬዚዳንቱ ገለፃ፤ ከሰላም በላይ ጦርነትን፤ ከይቅርታ ይልቅ ለቂመኝነት ሥፍራ መስጠት የጎዳን መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም። መፍትሄው ከነዚህ ጎጂና የመልካም ስብዕና ተፃራሪ ከሆኑ ዝንባሌዎች ሁሉ በመመለስ በይቅርታና ተከባብሮ፤ ልዩነትን እንደ ጠቃሚ እሴት ተንከባክቦ መኖር ነው ብለዋል።

አዲሱ ዓመት ለሀገራችን ህዝብ በሙሉ የሰላም፣ የእረፍትና የመረጋጋት ዓመት እንዲሆን ተመኝተው፤ በዓሉን ስናከብር ችግር ያለባቸውን በማሰብ እና ቸርነትን ለማድረግ በመትጋት ሊሆን ይገባል። ዓመት በዓሉ የደስታ፣ የሐሴትና የመተሳሰብ በዓል እንዲሆንም ተመኝተዋል።

የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስትያናት ህብረት ምክትል ፕሬዚዳንት ፓስተር ሰንበቶ ባሼ እንደገለጹት፤ የፈረሰው የሚታደስበት፣ ከቤተሰብ እስከ ሀገር ትላልቅ ራዕዮች የሚፈልቁበት፣ የስራ መንፈስ የሚገነባበትና አንዱ ለአንዱ ያለውን ወንድማዊ ሃላፊነት የሚወጣበት ብሩህ ዘመን እንዲሆን በትጋት በመስራት መንፈሳዊ ሃላፊነትን መወጣት እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል።

ፓስተር ሰንበቶ፤ አንዳንድ ማህበራዊ ሚዲያዎች ከመንፈሳዊነትም ሆነ ከአብሮነት ጋር ቁርኝት የሌላቸው የሌሎችን ክብር የሚነካ፣ ጥላቻን የሚዘሩ፣ ሁከትን የሚዘሩ በመሆናቸው ይህ እንደማይጠቅም በመገንዘብ በሰላምና በፍቅር ለመኖር የሚረዱ ሃሳቦችን ወደ ህዝቡ እንዲያስተላልፉ መክረዋል።

አዲሱንዓመትም መላው ምእመን የተቸገሩትን በመደገፍ፣ ያዘኑትን በማጽናናትና የታመሙትን በመጎብኘት በፍቅር የምንቀበልበት እንዲሆን ምኞታቸውን አስተላልፈዋል። ሰላምን በማምጣት ሂደት ህይወታቸውን ላጡ፣ የአካልና የመንፈስ ስብራት ለደረሰባቸው ወገኖችም መጽናናት እንዲሆንላቸው እንጸልያለን ብለዋል።

# አዲሱ ዓመት የሰላም...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የሚታቀድበት ብሎም አዲስ የሕይወት ምዕራፍ የምንጀምርበት ሲሆን ካለፈው ዓመት ስራችን የምንማርበትንና የጎደለውን የምናስተካክልበት ነው ብላለች።

በዓሉን ስናከብር የተቸገሩትን በማሰብ እንዲሁም ለሀገር ሰላም በመጸለይ መሆን እንደሚገባ አስታውቃ፤ 2016 ሀገራችን ላይ ጽኑ ሰላም የሚሰፍንበት እንዲሁም ሀገር የምትበለጽግበት እንድትሆን እመኛለሁ ብላለች።

ነዋሪነታቸውን በአዲስ አበባ ከተማ አራት ኪሎ አካባቢ ያገረጉት አቶ አስራት ታደሰ በበኩላቸው፤ በአዲሱ ዓመት የተጀመሩ እና የተሰሩ መልካም ሀገራዊ ስራዎችን በማስቀጠል ለበለጠ እድገት የሚመዘገብበት እንዲሆን መልካም ምኞታቸውን ተመኝተዋል።

በ2016 መባቻ የዓባይ ግድብ አራተኛ ሙሌት በስኬት መጠናቀቁ ለሁላችንም የተበረከተ የአዲስ ዓመት ስጦታ ነው ያሉት ነዋሪዎቹ መንግሥት የሚስተዋለውን ብልሹ አሰራር እና የኑሮ ውድነት የሚያባብሱ ሕገወጥ ነጋዴዎችን በመቆጣጠር ቀጣይ ዓመት ዘላቂ የሆኑ ሰላም እና ኢኮኖሚያዊ እድገት እንዲሆን ሁሉም የበኩሉን መስራት አለበት ብለዋል።

አዲሱ ዓመት የሕይወታችንን አዲስ ምዕራፍ የምንጀምርበት ነው ያሉት ሌላኛው የከተማዋ ነዋሪ አቶ አምባኋሮ ልኡልሰገድ ሲሆኑ ምኞቶቻችን ከምኞትነት ባለፈ ተግባር ላይ የሚውልበት አዲስ ዓመት እንዲሆን እመኛለሁ ሲሉ ተናግረዋል።

ሀገራችን አሁን ካለችበት ግጭት ወጥታ ወደቀድሞ ሰላሟ እና አንድነቷ እንድትመለስ መንግሥት ብሎም ህብረተሰቡ የበኩሉን ማድረግ አለበትም ብለዋል።

ነዋሪዎቹ አዲሱ ዓመት የጤና፣ ፍቅር እና የብልጽግና ዘመን እንዲሆን ተመኝተው በሀገሪቱ የተጀመሩ ፈጣን ልማትና እድገት ቀጣይነት እንዲኖረው መሰራት አለበት ብለዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## አዲስ ዓመት - አዲስ የተስፋ ፍኖት!

ፍኖት - በብርሃን የተሞላ መተላለፊያ ነው። ብርሃናማ መተላለፊያ ደግሞ ወደ ሕልማችን መግቢያ በር፤ ወደ ሕልማችን መዳረሻ መንገድ፤ የሕልማችን መገለጫ አውድ ሜዳ/አደባባይ ነው። እኛ ኢትዮጵያውያን ደግሞ አዲስ ዓመትን ስንቀበል አዲስ ሕልም ይዘን፤ አዲስ ግብ አስቀምጠን፤ አዲስ ስኬትን በመሻት ነው። ለዚህ ሕልማችን እውን መሆን፤ ግባችን መሳካት እና ስኬታችን እውን መሆን ፍኖት (በር፣ መንገድና መገለጫ አደባባይ) ያስፈልገናል።

ይህ እውን ይሆን ዘንድ ደግሞ በመጀመሪያ ሕልሞቻችንንና መሻታችንን ይዘን የምንዘልቅበት የመግቢያ በር ያስፈልገናል። ይህ ደግሞ የመሻታችን ፍኖት በር ሆኖ ያገለግለናል። ይሄ በአዲሱ ዓመት ለያዝነው ሕልምና መሻት እውን መሆን የመጀመሪያው መግቢያ በራችን ደግሞ የዓመቱ የመጀመሪያው ወር፤ ከወሩም የመጀመሪያው ዕለት መስከረም አንድ ቀን ነው፡፡

በእለተ እንቁጣጣሽ የብሩህ መሻታችን ተምሳሌት በሆነ መልኩ ደምቀንና አምረን የምናሳልፈው የወርሃ መስከረም የመጀመሪያው ቀን ታዲያ፤ የዓመቱ ጉዟችን፣ የሕልማችን ከፍታ አውድ ሆኖ ይገለጣል። በዕለተ እንቁጣጣሽ የፍኖት በርነት አንድ ብለን የምንጀምረው አዲስ ዓመት በመጀመሪያው ቀን ውሏችን የምንሰንቀው ከፍ ያለ የደስታ፣ የፍቅርና የአብሮነት አቅም ለዓመቱ ጉዟችን ብርታት ሆኖ ያገለግለናል፡፡

በዕለተ እንቁጣጣሽ በርነት ሕልምና መሻታችንን ይዘን የዘለቅንበት አዲስ ዓመት ታዲያ፤ በቀጣዩቹ ቀናት፣ ሳምንታትና ወራት ዑደት ውስጥ ወደ ግባችን እንድንራመድ ያስገድደናል። ለግባችን መዳረሻ ደግሞ መንገድ ያስፈልገናል፤ ብርሃናማ መንገድ፤ በእንቅፋትና እሾህ የማይስተጓጎል መንገድ፤ በፍቅርና አብሮነት፣ በሰላምና ይቅርታ፣ በሃሴትና ፌሽታ፣ በትጋትና በጥበብ የታጀበ መንገድ፡፡

ይህ ፍኖት/መንገድ ለሕልማችን መሳካት የምንራመድበት እንደመሆኑ፤ በዕለተ እንቁጣጣሽ የገለጥነውን የአብሮ መዋልን፤ የአብሮ መብላትን፤ የአብሮ መደሰትን፤ አብሮ የመራመድን፣... በድምሩ በኅብርና በኅብረት መገለጥን ይሻል። ይሄ ኅብረት ነው ኃይልም፣ ጥበብም ሆኖ ወደ ግባችን የሚያራምደን፤ ይሄ አብሮነት ነው ወደ ብልጽግናችን በምናደርገው ግስጋሴ ፍኖት ሆኖ ከግባችን የሚያደርሰን፡፡

አዲሱ ዓመትም ይሄንን አብሮነት አብዝቶ ይሻል። ምክንያቱም አብሮነት አቅም ነው፤ አብሮነት ጥበብ ነው፤ አብሮነት አሸናፊነት ነው፤ አብሮነት ሰላም ነው፤ አብሮነት ለሰው ልጆች ሕልምና ምኞት መሳካት፤ ከፍ ላለችው ኢትዮጵያ የበለጠ ከፍታ መጎናጸፊያ ሰንደቅ ነው። በመሆኑም ዛሬ በአዲሱ ዓመት የመጀመሪያው ዕለት ላይ ሆነን የምናሳያው አብሮነት፣ ፍቅርና መተሳሰብ በቀጣዮቹ ቀናት፣ ሳምንታትና ወራት ጅረት ውስጥ የማይቋረጥ ወንዝ ሆኖ መፍሰስ ይኖርበታል፡፡

ይህ ሲሆን ወደ ሦስተኛው ፍኖት እንደርሳለን። ሦስተኛው ፍኖት፣ ሜዳ ወይም አደባባይ ነው። በኅብር ደምቀን ከሕልማችን ጋር በመስከረም በር እንደዘለቅን ሁሉ፤ በኋላም በቀናት ድልድይነት በተገነባው መንገድ በወል ተራምደን ወደ ግባችን ካመራን፤ በመጨረሻ ግባችንን መትተን በስኬት ሜዳ/ አደባባይ መዋላችን አይቀሬ ነው። ምክንያቱም በፍቅር የተከፈተ በር፤ በአብሮነት የተጀመረ መንገድ መዳረሻው ከከፍታ ነውና፡፡

እናም ዛሬ ወደ ሕልማችን መዳረሻ መስከረም አንድ ላይ ከፍተን የገባንበት እና መንገድ የጀመርንበት አዲሱ የ2016 ዓመተ ምሕረት፤ ቀን ቀንን እየተካ፣ ሳምንታት ወራትን እየወለዱ አዲስ ብለን የተቀበልነውን ዓመት አሮጌ ብለን መሸኘታችን አይቀርም። ይሄ ሲሆን ደግሞ ሕልምና መሻታችን በግቡ ይመዘናል፤ ከስኬቱም አንጻር ይወራረዳል፡፡

ታዲያ የዛኔ፣ ሕልመኞች ብቻ ሆነን ልንገኝ አይገባም። ይልቁንም የምናልም፤ ለሕልማችንም የምንተጋ፤ ካስቀመጥነው ግብ ደርሰንም በስኬታችን የምንገለጥ ልንሆን የተገባ ነው። ለዚህም ነው ፍኖት የሚያስፈልገን። ምክንያቱም ፍኖት ወደ ሕልማችን መግቢያ በር ነው፤ ፍኖት ወደ ግባችን መራመጃ መንገድ ነው፤ ፍኖት ሕልማችን ሰምሮ በስኬት ሜዳ ወይም አደባባይ የምንገለጥበት አውድም ነው፡፡

በመሆኑም አዲሱ ዓመት ሕልም ብቻ ሳይሆን ፍኖትም ሊኖረን ይገባል። ይሄ ፍኖት ደግሞ የሰላም ፍኖት ነው፤ የአብሮነት ፍኖት ነው፤ የይቅርታ ፍኖት ነው፤ የመተሳሰብ ፍኖት ነው፤ አንዳችን የአንዳችን አለኝታ የመሆን ፍኖት ነው፤ በኅብር የደመቀ ኢትዮጵያዊነትን ከፍ የማድረግ ፍኖት ነው፤ ስለ ሕዝብና ስለ ሀገር ክብርና ሉዓላዊነት ራስን አሳልፎ የመስጠት ልዕልናን የመላበስ ፍኖት ነው፤ ተነጋግሮ የመግባባት፣ ተመካክሮ ለይቅርታ የመዘጋጀት ሰብዕናን የመጎናጸፍ ፍኖት ነው፡፡

ይሄ ፍኖት ነው ኢትዮጵያን የሚያልቃት፤ ይሄ ፍኖት ነው ኢትዮጵያውያንን በክብርና በሞገስ የሚገልጠው፤ ይሄ ፍኖት ነው በአዲስ ዓመት ልናሳካ የምናልማቸውን ነገሮች ከግብ እንድናደርስ አቅም የሚሆነው፤ ይሄ ፍኖት ነው የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ብልጽግናን እውን በማድረግ ጉዞው የጥበብም፣ የሞራልም ስንቅ የሚሆነው። አዲሱ ዓመትም በአዲስ ሕልም፣ በአዲስ መዳረሻ እና በአዲስ ስኬቶች ሊገለጥ የሚችለው ይሄ ሲሆን ነው፡፡

ከዚህ አኳያ ዛሬ አንድ ብለን የጀመርነው የ2016 ዓመተ ምህረትም ከቀን ቀመርነት የተሻገረ ነው። ምክንያቱም ዓመቱ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን የብዙ ተስፋዎች ዓመት ነውና። የመልማት ዓመት ነው፤ የሰላም ዓመትም ይሆንልናል፤ የመመካከርና የመግባባት ዓመትም ነው፤ በቂምና በቀል ፈንታ ለፍቅር ተሸንፎ በይቅርታ የመሻገር ዓመታችንም ነው። ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያውያን በማኅበራዊው፣ ኢኮኖሚያዊው፣ ፖለቲካዊው፣ ዲፕሎማሲያዊው መስክ ብዙ ሠርተው ብዙ የሚያተርፉበትም ነው። በጥቅሉ አዲሱ ዓመት ለኢትዮጵያውያን አዲስ ፍኖት ሆኖ የሚገለጥ ነው!


## አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4200

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## አዲስ የምንሆንበት አዲስ ዓመት

ፍሬሕይወት አወቀ

አሮጌውን ዓመት ሸኝተን አዲስ ዓመትን በአዲስ መንፈስ የምንቀበልበት የዓመቱ የበኩር ወር መስከረም። የወራቶች ንጉሥ የሆነው ወርሃ መስከረም ለእኛ ኢትዮጵያውያን ልዩ ወር ነው። በአሮጌው ዓመት የቱንም ያህል ባይደላን፣ ሞልቶ የማያውቀው የኑሮ ሸንቁሩ አብዝቶ ቢያጎድልብን፣ መከራና ኀዘን ቢፈራረቅብን፣ ብናዝን፣ ብንከፋም አዲስ ዓመትን ተስፋ አድርገን እንጠባበቃለን እንጂ ተስፋ አንቆርጥም። ይህ የኖረ ልማዳችን ነው። እኛ ኢትጵያውያን እንኳንስ ኑሮ ጎድሎብን ሁሉ ነገር አልጋ በአልጋ ሆኖ አሸወይና አይነት ዓመት ብናሳልፍ እንኳ፤ አዲስ የነበረውን አሮጌ ብለን ሸኝተን አዲስ ዓመትን በአዲስ መንፈስ በአዲስ ተስፋ መጠበቅና መናፈቃችን አይቀሬ ነው።

በአዲስ ዓመት የጎደለው እንዲሞላ፤ የራቀው እንዲቀርብ፣ የጠፋው እንዲገኝ ከመመኘት ባለፈ የሞላውም ሞልቶ እንዲትረፈረፍ በአዲስ ዓመት ተስፋ የምንሰንቀውም ለዚሁ ነው። እኛ ኢትዮጵያውያን በአሮጌው ዓመት በብዙ ብንፈተንም በፈጠርናቸው ችግሮች እግር ከወርች ተይዘን መከራ ተፈራርቆብን ይሆናል። ያም ቢሆን ታዲያ ችግሮቻችን ሁሉ በሐምሌና ነሐሴ ጎርፍ ተጠራርገው እንደሚሄዱ እናምናለን እንጂ ከአሮጌው ዓመት ጋር አሮጌ አንሆንም። ይህ ደግሞ የብዙዎቻችን እምነት ነው። ‹‹እምነት ያድናል›› እንዲል ታላቁ መጽሐፍ እምነታችን ዕውነት ሆኖ ዝናቡ ጋብ ሲል አዲስ ዓመትን በብዙ ተስፋና በአዲስ መንፈስ በአበቦች መዓዛ ለመቀበል እንጓጓለን ጓግተናልም።

ጉጉታችን ዕውን ሆኖም ለወትሮው አዲስ ብለን የተቀበልናቸውን ብዙ ሺ አዲስ ዓመታት አሮጌ ብለን ሸኝተናል። በተመሳሳይ አዲስ ዓመትን በወርሃ መስከረም ከሚፈኩ አበቦች ጋር ፈክተን ተቀብለናል። ይኸው ዛሬም መጣሁ መጣሁ የሚለውን 2016ን አዲስ ብለን ለመቀበል ስንዱ እመቤት ሆነን ከላይ ታች እንላለን። አዲስ ዓመት ሲነሳ ታዲያ ዘመን ተሻጋሪ የሆኑ የጥበብ ሥራዎች መነሳታቸው የግድ መሆኑ ዕሙን ነው። ለዚህ ደግሞ አንጋፋው ድምጻዊ የክብር ዶክተር አርቲስት ጥላሁን ገሰሰን የሚቀድመው ባይኖርም የተከተሉት ድምጻውያን በርካቶች ናቸው። እንዳለ አሮጌ ሆኖ ከሚሰናበተው ዓመት ጋር በሽታና ችግር ተጠራርገው እንዲወገዱ ድምጻዊው በምኞቱ ሲያዜም...

‹‹ክረምት አልፎ በጋ መስከረም ሲጠባ፤  
አሮጌው ዓመት አልፎ፣ አዲሱ ሲገባ፤  
በአበቦች መአዛ ረክቷል ልባችሁ፤  
ህዝቦች ሁሉ በጣም እንኳን ደስ አላችሁ፤  
የበሽታን አይነት በሙሉ ጠራርጎ፤  
ከቆሻሻ ጋራ ጎርፉ ሙልጭ አድርጎ፤  
ፈሳሽ የወንዝ ውሃ ተውሳኩን ይውሰደው፤  
ጤና መሆኑን ነው እኛ የምንወደው...››

እርግጥ ነው ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ዛሬ ለሀገራችን ሰላምን፤ ለዜጎቿ ስኬትና ብልጽግናን አጥብቀን የምንመኝበት የአዲስ አመት ዋዜማ ላይ እንገኛለን። ታድያ እንዳለፉት ብዙ ሺ ዓመታት ሁሉ 2015 ዓ.ም አሮጌ ብለን ስናሰናብተው አብረን ተባብረን የምናሰናብታቸው እግር ከወርች የያዙን አንድ ሺ አንድ ችግሮች ስለመኖራቸው ለአፍታ እንኳ መዘንጋት የለብንም። ሀገር ሰላም ውላ እንዳታድር ከውስጥም ከውጭም ሲጎነትሉን የኖሩ እሾህ አሜኬላዎች እንዲነቀሉና ተጠራገው እንዲወገዱ፤ ህዝብ ለህዝብ ተባብሮና ተከባብሮ መኖር የሚችልበትንና ኢትዮጵያዊ አንድነቱን የሚያጠናክርበት አዲስ ዓመት እንዲሆን አጥብቀን ልንመኝ ይገባል፡፡

ክረምትና በጋ የሚፈራረቅባት ለምለሟ ኢትዮጵያ ሳትጠብ የጠበበ አመላችንን አስፍተን እርስ በእርስ የምናደርገውን መገፋፋትና መጠላለፍ፤ ጥላቻና ኤኔ እበልጥ እኔ እበልጥ ያልተገባ ፉክክርን እንዲሁም ዘረኝነትን ከውስጣችን አስወግደን የሁላችን በሆነችው አንዲት ሀገር በአንድነትና በመተሳሰብ በጋራ ተረዳድተንና ተከባብረን ለመኖር አዲሱ ዓመት መነሻ ይሁነን። መገፋፋትና መከፋፈልን በጽኑ አውግዘን ‹‹...ፈሳሽ የወንዝ ውሃ ተውሳኩን ይውሰደው ጤና መሆኑን ነው እኛ የምንወደው...›› እንዳለው ድምጻዊው በ2015 ዓ.ም የደረሰብን የሰላም ዕጦት፣ ችግር መከራ፣ ስደት ጉስቁልና፣ ጦርነትና መፈናቀሉን አጠቃላይ የተፈጥሮ አደጋውና ተውሳኩን በሙሉ ፈሳሽ የወንዝ ውሃው ጠራርጎ እንዲወስድልን አጥብቀን እንሻለን።

ዛሬ ከተሰናባቹ 2015 ዓ.ም የመጨረሻ ጠርዝ ላይ እንዲሁም ከአዲሱ ዓመት ዋዜማ ደጃፍ ላይ ሆነን ለሀገራችን ሰላምን ከመመኘት ባለፈ ለሰላም ዘብ በመቆም ሙሉ አቅማችንን አሟጠን መጠቀም የግድ ይለናል። ምክንያቱም የሰፈረብን የጥላቻና የዘረኝነት ዛር እንዲህ በቀላሉ የሚለቀን እና እንደቀደመው ጊዜ ሁሉ በአዲስ ዓመት “ማጨስ አቆማለሁ...” “መጠጥ አቆማለሁ...” “ማምሸት አቆማለሁ...” “ትምህርቴን እጨርሳለሁ...” “መሥሪያ ቤት እቀይራለሁ...” “የግል ሥራ እጀምራለሁ...” ወዘተ... በማለት ለግል ሕይወታችን ቃል ገብተን የምናልፈው ጉዳይ አይደለም። በእውነት ስለዕውነት ስለሀገራችን ሰላም ቃል የምንገባበት እንጂ፤ በግል ሕይወታችን ልናሳካ ያሰብነውና ያቀድነው ሁሉ ከሀገር ሰላም ውጭ የሚታሰቡ አይደሉምና ለኢትዮጵያ ሰላምና አንድነት በአዲሱ ዓመት ቃል እንግባ፡፡

የሰላም አስፈላጊነት ከማንኛውም የግል ጥቅም፣ ፍላጎት እና የጦር መሳሪያ ኃይል የሚበልጥ ሆኖ ሳለ ብዙዎች በሰላም ስም ጦር መዘው ቃታ ይስባሉ። እርግጥ ነው ብዙ ሀገራት ለሰላማቸው መደፍረስ አይነተኛ ምክንያት ቢኖራቸውም ሰላማቸውን የማረጋጋጥ ኃላፊነትም በእጃቸው መዳፍ ላይ መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነው። ይሁን እንጂ ብዙዎቹ ለሰላም ዋጋ ሲከፍሉና ቅድሚያ ሲሰጡ አይስተዋልም።

እንደሌሎች ሀገራት ሁሉ ታዲያ ኢትዮጵያም ሰላሟን ያደፈረሱና እያደፈረሱ ያሉ ለቁጥር የበዙ ችግሮቿን ከአሮጌው ዓመት ጋር አራግፋ ወደ አዲስ ዓመት ለመሸጋገር በጣት የሚቆጠሩ ቀናት ቀርተዋታል። አንዱን ችግር ተሻገርኩ ስትል ሌላው እየተከተለ ከልማት ጉዞዋ ብቻ ሳይሆን ክቡር ከሆነው ከሰብዓዊነት ጎዳና ጭምር ሊያወጣት ሲፈታተናት መቆየቱ ገና ትዝታ አልሆነም። ታዲያ ለመውደቅ ጫፍ ያደረሷትን ችግር በአሮጌው ዓመት አሮጌ በማድረግ ጠራርጎ ማስወገድ የግድ ይሆናልና ለዚሁ ክንዳችንን እናበርታ።

አሮጌ ያልነውን 2015 ዓ.ም ስናሰናብት አብረን ልናሰናብታቸው የሚገቡ ለቁጥር የበዙ ህመሞችና ተውሳኮች አሉ። እነዚህ ተውሳኮች በፈሳሽ የወንዝ ውሃ ተጠራርገው እንዲወሰዱና ሀገር ሰላም እንድትሆን ዜጎች በጤና፣ በፍቅርና በደስታ እንዲኖሩ አጥብቀን እንመኛለን። በተለይም በአዲስ ዓመት ዋዜማ ላይ ሆነን በአዲስ ተስፋ ተሞልተን ሁሉም ጥሩ እንደሚሆን እንመኛለን። ከምኞት ባለፈም ታዲያ አጥብቀን ለምንሻው ለሀገር ሰላምና ለዜጎች ስኬትና ብልጽግና ከእያዳንዳችን የሚጠበቅ የቤት ሥራ ስለመኖሩ ለአፍታም መዘንጋት አይገባንም።

አዲስ ዓመት አሮጌነትን አውልቀን አዲስ የምንሆንበት እንጂ ሲያለያየንና ሲከፋፍለን የነበረ ማንኛውም ችግር ከትናንቱ አሮጌው ማንነታችን ወደ አዲሱ ተስፋችን አምጥተን ተስፋችንን የምናጨልምበት አይሆንም። ከሁሉም በላይ ግን በሀገር ደረጃ የሚያወዛግቡንን ጉዳዮች በመለየትና በመወያየት እንደ ሀገር ከግጭትና ቀውስ አዙሪት ውስጥ ለመውጣት የሚያስችለንን ሰላማዊና ሁሉን አቀፍ የሆነ ትጥቅ ታጥቀን ከአሮጌው ጋር አሮጌ ሳንሆን አዲሱ ዓመትን በአዲስ መንፈስ በብዙ ተስፋ እንቀበለው።

ልዩ ዕትም

# ዘመን መለወጫ እና አደይ አበባ

**የአሰሳው ኃይረዲን ከዲር ነኝ**

ኢትዮጵያውያን ተከባብረንና ተፈቃቅረን እንጂ ተነጣጥለን የምናከብረው አንድም ክብረ በዓል የለንም። በቅድሚያ ሁሉም የሀገራችን ዜጎች በጋራ ለምናከብረው በዓል እንኳን በጤና አደረሳችሁ!! እንኳን አደረሰን!!

የኢትዮጵያ ሕዝብ በየዓመቱ በታላቅ ስሜት ከሚያከብራቸውና ከሚያዘክራቸው በዓላት አንዱና ተወዳጁ የዘመን መለወጫ በዓል ነው። እንደ ዕፅዋት ሁሉ ሰውም በወርሃ መስከረም በተስፋ ስሜት ይለመልማል። ከዋዜማው ጀምሮ በየቤቱ ጨፌና ቄጠማ ይጎዘጉዛል። አበባ በሥርዓት እየተዘጋጀ በየቦታው ይቀመጣል።

በተለይ ልጆች አዳዲስ ልብሳቸውን ለብሰው በደስታ ይፈነድቃሉ። የአዲሱ ዓመት መባቻ አንድ ብሎ ሲጀምር በውብ ቢጫማ ቀለማቸው ዙሪያ ገባውን የማፍካት ተፈጥሮአዊ ጸጋን ተጎናጽፈው የኢትዮጵያ አዲስ ዓመት ወይም ዘመን መለወጫ በዓልን ይበልጥ ያደምቁታል።

በአረንጓዴ ቅጠሎቻቸው፣ በቢጫ ቀለም አበቦቻቸው ደምቀው ሲታዩም ለኢትዮጵያውያን ልዩ ትርጉም አላቸው። የተስፋ፣ የልምላሜ፣ የሰላም፣ የምኞት መግለጫ ተደርገውም ይታሰባሉ።

በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር /የጊዜ ቀመር/ አንድ ዓመት በውስጡ አሥራ ሦስት ወራትን የያዘ ሆኖ በአራት ወቅቶች የተከፈለ ነው፤ ከእነዚህ አራቱ ክፍላተ ዘመን (ወቅቶች) ከሚባሉት ጊዜያት አንዱ ክረምት ነው።

የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ክረምቱ ሰኔ 26 ቀን ጀምሮ መስከረም 25 ቀን ያበቃል። የዘንሮው ክረምት ግን ከተለመደው ጊዜ ቀደም ብሎ መዝነብ የጀመረ መሆኑም ብዙዎች ይጋሩታል።

መስከረም የኢትዮጵያውያን ዘመን መለወጫ (አዲስ ዓመት)፣ እንቁጣጣሽ፣ አደይ አበባ... "ተነጣጥለው የሚታዩ አይደሉም፤ በእርግጥ የየራሳቸው ልዩ መገለጫዎች ቢኖሯቸውም ሁሉም የወርሃ መስከረም ስጦታዎች ወይም ገጸ በረከቶች ናቸው።

እንዲያው ከኖርንበትና ከምናውቀው እውነታ ጨልፈን፣ ከማህበረሰቡ የልማድ ተሞክሮ፣ ከሃይማኖት ሊሂቃንና ከተለያዩ የምሁራን ጥናቶች ተነስተን እውነታውን በወፍ በረር ለመቃኘት እንሞክር።

የክብር ዶክተር ከበደ ሚካኤል በቀድሞው የ3ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መጽሐፍ ላይ ስለ ሁሉም ወራቶች ባህራይትና ግብር በዘረዘሩበት"የዓመቱ ወራት የሚል ርዕስ በሰጡት ግጥማቸው ውስጥ፡-

"ጨለማው ሲጠፋ ዝናቡ ሲያቆም፣
ያ የለውጥ ወራት መጣ መስከረም።
ሰዎች ይነሳሉ ሊሰሩ ታጥቀው፣ መስከረም ነውና ብርሃን ሰጪው። " ማለታቸው አይዘነጋም።

ጋሼ መንግስቱ ለማ፡- "የመስቀል ወፍና የአደይ አበባ፣ ምን ቀጠሮ እንዳላቸው መስከረም ሲጠባ።" ማን ያውቃል? ብሎ ተቀኝቷል። ለመሆኑ አደይ አበባና የመስቀል ወፍ ዓመቱን ሙሉ ተሰውረው ሳይታዩ ከርመው የመገናኛ ጊዜያቸውን በጋራ ስምምነትና ውሳኔ በቀጠሮ አስቀምጠውት የሄዱ በሚመስል አኳኋን ወርሃ መስከረምን ጠብቀው አብረው የሚከሰቱበት ምስጢር ምንድነው ?።

እውነታው አጃኢብ አያስብልምን? አደይ አበባስ ለምን ይሆን በፀደይ ወራት ብቻ ታይቶ የሚጠፋው? መቼም ለዚህ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ ለማግኘት ተፈጥሮ ረቂቅና እጅግ ጥልቅ ነውና ሠፊ ምርምር፣ ብዙ ጥናት ማድረግ ብቻውን አይበቃም፤ ይህንን እውነታ በተጨባጭ ለማስረገጥ መለኮታዊ መሰጠት(ተሰጥኦ) እንደሚሻ ይሰማኛል።

ለአብነት ያህል በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሥነ-እፅዋት መምህር ፕሮፌሰር ሰብስቤ ደምሰው በአንድ ወቅት እንደተናገሩት ፣ የአደይ አበባንና የመስከረም ቀጠሮ የሚመሳስሉት ከሰዓት ጋር ነው። "ማታ ተኝተን ጠዋት እንድንነቃ ሰዓት እንሞላለን፤ ልክ እንደዚያው እፅዋት የራሳቸው ጉዳዮች ከተሳካላቸው፣ የሚፈልጉትን መጠን ዝናብና ፀሐይ ካገኙ'አሁን ነው የምታብቡት' የተባሉ ይመስል ሰዓቱን፣ ቀኑንና ወሩን ሳያዛንፉ በተፈጥሮ ውስጣዊ ግፊት ያብባሉ ይህም 'ባዮሎጂካል ክሎክ' በመባል ይታወቃል።

መስከረም 1 የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር የሚጀምርበት አዲስ ዘመን ነው፤ ይህ ጊዜ ርእሰ ዐውደ ዓመት የሚባልበትና የርእሰ ዐውደ ዓመቱ መጠሪያ እንዲሆን አባቶች ደንግገዋል። ዕለታቶቹ በሙሉ የሚገለፁበትና የተሰየሙበት ምክንያታዊ መጠሪያ አላቸው። ለምሳሌ ከመስከረም 9 እስከ 15 ባሉት 7 ቀናት ወይም ዕለታት መካከል "ፍሬ"፣ "ተቀጸል ጽጌ"(አበባን ተቀዳጅ) ተቀጸል ጽጌ ልዩ የመዝሙርና የጸሎት ሥርዓት" የሚባሉ ሲሆን የተዘራው ዘር ደርሶ ለፍሬ መብቃት የሚጀምርበት ጊዜ ነው።

ገበሬው የተዘራው ዘር ሁሉ ለፍሬ ባይበቃም አብዛኛዎቹ ፍሬዎች አፍርተው እሸት መብላት የሚጀመርበት ወቅት ስለሆነና ገበሬው ያሳለፈው ውጣ ውረድና ድካም በከንቱ ሳይቀር ለፍሬ የሚበቃበት ወቅት ስለሆነ ዘሩንም ከተለያየ አደጋ አትርፎ ለፍሬ ያበቃው ፈጣሪ የሚመሰገንበት ጊዜ ነው።

የኃይማኖት ሊሂቃን አባቶች በበኩላቸው "ከመስከረም 17 እስከ 25 ድረስ ያሉ 9 ቀናት(ዕለታት) ደግሞ መስቀል የሚል ስያሜ መያዛቸውን ይገልጻሉ፤ በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር እያንዳንዱ ቀን (ዕለት)፣ ሳምንት፣ ወር፣ ወቅት(ዘመን) በታላላቅ ሐይማኖታዊ የመጠሪያ ምክንያቶች የተሰየመ ሆኖ የሰው ልጅ ሕይወት ከጨለማ ወደ ሚደነቅ ብርሃን የሚሸጋገርበት፣ ከእርኩሱ የዲያብሎስ ቁራኝነት ነጻ የሚወጣበትና ሠናይ የፀደይ ዜና የሚታወጅበት ነው"ይላሉ።

በተጨማሪም...ዶክተር ሃብተማርያም አሰፋ "የኢትዮጵያ ታሪክ ጥያቄዎችና ባሕሎች" በሚለው መጽሐፋቸው "መስከረም" መስ-ከረም" ከከረመ በኋላ ወይም ክረምት ካለፈ በኋላ ማለት ነው። የመስከረም ወር ዝናብ የሚቆምበት፣ ፀሐይ የምትወጣበት፣ ወንዞች ንጹሕ ውሃ፣ ጽሩይ ማይ የሚጎርፍበት፣ አፍላጋት የሚመነጩበት፣ አዝርዕት አድገው ማሸት የሚጀምሩበት፣ ሜዳዎችና ተራራዎች ሸለቆዎችም በአበባ የሚያሸበርቁበትና የሚቆጠቆጡበት ነው» ይሉታል።

እንዲህም በመሆኑ የጨለማ የችግርና የአፀባ ጊዜ የሚያበቃበት የብርሃን፣ የደስታ የእሸት፣ የፍሬና የጥጋብ ጊዜ የሚጀምርበትና የሚተካበት ነው ብሎ ሕዝቡ ስለሚያምንበትም የዕንቁጣጣሽ በዓልን ከሁሉ አብልጦ ግምት ስለሚሰጠው በእሳት ብርሃንና በእሳት ቡራኬ በየቤቱ እንደ ሁኔታው ከብት አርዶ፣ደግሶ ይቀበለዋል።

በወርኃ መስከረም መሬቷ በአደይ አበባ አሸብርቃ ስለምትታይና በተለይም ዕንቁ የመሰለ አበባ ስለምታወጣ መሬቷን ዕንቁጣጣሽ፣ ዕንቁ የመሰለ አበባ አስገኘሽ ለማለት 'ዕንቁጣጣሽ' ተብላለች። አቧራ፣ ቡላ የነበረው መሬት በዝናቡ ኃይል ለምልሞ ተመልከቱኝ፣ ተመልከቱኝ የምትል ያሸበረቀች፣ አበባ የተንቆጠቆጠች ሆነች የሚል-ለዕንቁጣጣሽ ስያሜ መነሻ ሊሆን እንደሚችል መዛግብት ይጠቁማሉ።

አበው "መስከረም በአበባ፤ ሠርግ በጭብጨባው ይታወቃል"። አንድም መስከረም ርዕሰ-ዓውደ ዓመት፣ የዘመን መለወጫ በመሆኑ ወርሃ አደይ፣ ወርሃ ጽጌ እፁብ ጌጡ ነው ይባላል። ለዚህ አብነቱ "ኢትዮጵያውያን በርዕሰ-በዓልነት ታላቅ ማዕዘን ላይ ያስቀመጡት ወርሃ መስከረም፣ ትልቅ የሆነ ሃይማኖታዊና ታሪካዊ ፋይዳን የያዘ ሃይማኖታዊና ባህላዊ በዓላትን አቅፏል።" ብለው በመተንተን ገለፃውን አጠናክረውታል።

ታዲያ ከዕንቁጣጣሽ በዓል ቀጥለው በሰፊው ከሚታወቁት በዓላት መካከልም፤ ተቀጸል ጽጌ፣ ዳመራ፣ የመስቀል ሥነ-ሥርዓት በአጠቃላይ ወርሃ መስከረም በተለያዩ ዐውደ በዓሎች ድምቅምቅ የሚል ልዩ ወር ነው ማለት ይቻላል፤ በዚህ ወር ብቻ ታላላቅ የበዓል አከባበር ሥርዓቶች ይከናወናሉ።

የተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦችም የዘመን መለወጫ በዓሎቻቸውን ያከብራሉ፡፡ በእነዚህ ክብረ በዓላት ውስጥ በርካታ የዳበሩ እሴቶች ያሉ ሲሆን በዓሉ ከመድረሱ ቀደም ብሎ ባሉት ቀናት ቂም እና ቂያሜን በይቅርታ ሽሮ በአዲሱ ዓመት፣ በአዲስ የሥነ-ልቦና ዝግጅት፣ በብሩህ ተስፋ ለአብሮነት መነሣት በየብሔረሰቡ ተወላጆች የሚከናወን ተግባር መሆኑ የተለመደ ነው።

እንደ ዕፅዋት ሁሉ ሰውም በወርሃ መስከረም ላይ በተስፋ ስሜት ይለመልማል። ከዋዜማው ጀምሮ በየቤቱ ጨፌና ቄጠማ ይጎዘጉዛል። አበባ በሥርዓት እየተዘጋጀ በየቦታው ይቀመጣል፤ በተለይም ልጆች አዳዲስ ልብሳቸውን ለብሰው በደስታ ይፈነድቃሉ።

**አደይ አበባን ያለ ዘመን መለወጫ ዘመን መለወጫን ያለ አደይ አበባ ማሰብ ለኢትዮጵያውያን ማይታሰብ ነው። ስመሆኑ አደይ አበቦችን ከሌሎች የዕፅዋት ዝርያቸው የሚለያቸው ባህሪ ምንድን ነው? ከውበት ባለፈ የሚሠጡትስ ጥቅም ምን ይሆን**

በአመሻሽ ላይ ደግሞ ችቦ አቀጣጥለው "እዮሃ አበባዬ፣ መስከረም ጠባዬ፣ እዮሃ...የበርበሬ ውሃ" እያሉ ያዜማሉ። እናም!! አደይ አበቦች የምድር ገፀ በረከቶች፥ የውበት ምስጢራት፥ልዩ እና ብሩህ ካባዎች ናቸው።

አደይ አበባን ያለ ዘመን መለወጫ ዘመን መለወጫን ያለ አደይ አበባ ማሰብ ለኢትዮጵያውያን ማይታሰብ ነው። ለመሆኑ አደይ አበቦችን ከሌሎች የዕፅዋት ዝርያቸው የሚለያቸው ባህሪ ምንድን ነው? ከውበት ባለፈ የሚሠጡትስ ጥቅም ምን ይሆን? ።

ከዓመታት በፊት በዘርፉ ጥናትና ምርምር ያደረጉት ዶክተር በላይነህ አየለ ሙያዊ የማብራሪያ ገለጻቸው ላይ "አደይ አበባ ከሳር ዝርያዎች ይመደባል። ስሩ አጭር በመሆኑ ከላይኛው የመሬት ክፍል የሚገኙ ማዕድናትን ለምግብነት ይጠቀማል። የበጋውን ደረቃማ የአየር ንብረት ተቋቁሞ የክረምቱ እርጥበታማ የዝናብ ወቅት መምጣቱን ሲያጤን ከተኛበት ተፈጥሮአዊ እንቅልፍ ይነቃል።

በወርሃ ሰኔ፣ ሐምሌ እና ነሐሴ ለምልሞ በወርሃ መስከረም መግቢያ መጀመሪያ ቀናት "የአማርኛው አደይ አበባ ወይም የመስቀል አበባ በኦሮምኛ ቋንቋ 'ኬሎ'፣ በትግርኛ ደግሞ 'ገልገለ መስቀል' ተብሎ የሚጠራው እፅዋት...በጋራና ሸንተረሮች አናት ላይ፣ በወንዞች ዳርቻ ዙሪያ አልፎ፣ አልፎ መፍካት ይጀምራል።

የአዲሱ ዓመት መባቻ አንድ ብሎ ሲጀምር ግን በውብ ቢጫማ ቀለማቸው ዙሪያ ገባውን የማፍካት ተፈጥሮአዊ ጸጋን ተጎናጽፈው አዲሱን ዘመን መለወጫ የኢትዮጵያን በዓል የበለጠ ያደምቁታል። በአረንጓዴ ቅጠሎቻቸው፣ በቢጫ ቀለም አበቦቻቸው ደምቀው ሲታዩም ለኢትዮጵያውያን ልዩ ትርጉም አላቸው። የተስፋ፣ የልምላሜ፣ የሰላም፣ የምኞት መግለጫ ተደርገውም ይታሰባሉ" ብለዋል ዶክተሩ።

በአደይ አበባ የተፈጥሮ ዑደትና ልዩ ባህሪያት ያደረጉትን ጥናታቸውን ዶክተሩ ሲተነትኑ "አደይ አበቦች የወቅቱን ሙቀት መጨመርና መቀነስ መረዳት የሚያስችል ልዩ ባህሪ እንዳላቸው፤ የሙቀት ሂደቱ ሲጨምር ከእንቡጥነት ወደ ማበብ፣ ከማበብ ወደ ዘርን ተክቶ መክሰምና ለቀጣይ ዓመት ብቅለት ራሳቸውን እንደሚያሸጋግሩ ይህ ባህሪያቸውም ከሌሎች የሳር ዝርያዎች በተለየ ተርታ እንዲመደቡ ያደርጋቸዋል" በማለት አስረድተዋል።

አደይ አበቦች ከሚሰጡት ተፈጥሮአዊ ድምቀት ባለፈም የአካባቢ ሥነ ምህዳር ሚዛንን ለመጠበቅ ቁልፍ ሚና አላቸው። ከፍተኛ ማር ለማምረት የሚውል ንጥረ ነገር በውስጣቸው አላቸው፤ በዚህም ምክንያት በማር ምንጭነቱ ይታወቃል። ታዲያ ንቦች ይህን ንጥረ ነገር በመቅሰም ማር ያዘጋጃሉ።

ሰዎች ደግሞ ከንቦች የሚያገኙትን ተፈላጊ የማር ምርት ለምግብነት፣ ለመድኃኒትነት ይጠቀሙበታል። ለገበያ አቅርበውም ኢኮኖሚያቸውን ይደግፉበታል፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እንደሚታየው ደግሞ በከተሞች አካባቢ አደይ አበባ በባህላዊ ቀሚስ እና በካናቴራ ላይ ታትሞ አሊያም ተጠልፎ የሚሸጥበት አጋጣሚ በርክቷል።

እናቶችና ወጣቶችም ኑሯቸውን ለመደገፍ ከቄጠማ ጋር ቀላቅለው ስለሚሸጡት የዕለት ጉርስም ለመሆን ችሏል። እንዲሁም በክረምት ወራት የአፈር ለምነትን ለመጠበቅ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ። አደገኛ ጎርፍ ለም መሬትን እንዳይጎዳ በስሮቻቸው የመሸርሸር አደጋን ይከላከላሉ። በእርጅና ወቅታቸውም አገዳቸው፣ ስራቸው እና ቅጠላቸው ስለሚበሰብስ ለመሬት ለምነት መጠበቅ ያገለግላሉ።

በተጨማሪም ስለ አደይ አበባ የተፃፉ የሥነ ጽሁፍ ውጤቶች እንደሚያሳዩት ደግሞ ቅጠሎቻቸውና አበቦቻቸውም ሰዎችን ከተለያዩ በሽታዎች ለመፈወስ የሚያስችል ፍቱን መድሃኒት ለማዘጋጀት ይጠቅማሉ። የታሪክ ተመራማሪ ፕሮፌሰር መስፍን ታደሰ ከ35 ዓመታት በፊት በኢትዮጵያ ባደረጉት ጥናት አደይ አበባዎች ጋራና ሸንተረሩን፣ ሜዳና ተራራውን ከማስጌጥ ባለፈ በተለያዩ አደጋዎች ለሚከሰቱ የደም መፍሰሶች፤ በተለይም እናት ሴቶች ወልደው ደም እየፈሰሰ አልቆም ካላቸው ጨቅጭቀው ጭማቂውን ከጠጡ የሚፈሰውን ደም እንደሚያስቆምላቸው፣ፀረ-ተዋህስ/Anti-infction/ በመሆን እንደሚያገለግለም ጠቁመዋል።

ሌሎች አንዳንድ የምርምር ውጤቶች እንደሚያመለክቱት ደግሞ የአደይ አበባ ለስኳር በሽታ፣ ለጭንቅላት ካንሰር ህክምና እንደሚውል ፍንጭ ሰጥተዋል። ከአደይ አበባ ክሬም ተመርቶም ወንዶች ጺማቸውን ከተላጩ በኋላ ለማለስለሻነት፣ ሴቶች ደግሞ ለማዲያት መከላከያ(ማጥፊያነት)፣ ለውበት መጠበቂያነት፣ ጭማቂው ለልብስ ማቅለሚያነት የሚውል መሆኑም ታውቋል።

በአንዳንድ ሀገሮችም ቅጠሎቻቸው ለሻይ ቅጠል አገልግሎት እንደሚውልም ጥናቶች ይጠቁማሉ። ለሌሎችም በርካታ አገልግሎቶች እንደሚውል ይታመናል። አደይ አበቦች ከተፈጥሮ ሚዛን መዛባት ችግሮች ጋር በተያያዘ የብቅለት ሂደታቸውም ይሁን ለፍካት የሚወስድባቸው የጊዜ ዑደት ከቦታ ቦታ ይለያያል።

ዕድሜና ጤና ከሰጠን ስለአደይ አበባ በርካታ ያልተነገሩ አስገራሚ ጉዳዮችን እየቆነጠርን ተከታታይ መጣጥፎችን እስከ ፀደዩ ማሳረጊያ ለአንባብያን ለማድረስ እሞክራለሁ። እስከዛው ለሀገራችንና ለህዝባችን ፍቅርና ሰላም ያበዛልን። ሠናይ አዲስ ዓመት!!

# ሴቶችና የበዓል ውሎ

**ስምስም መንግሥቱ**



ወይዘሮ ፋና ኤጀሬ፤



ወጣት መድኃኒት ሳይመን፤



ወይዘሮ አዜብ ይልማ፤

አዲሱ ዓመት እንዴት እያለፈ ነው? የቄጤማው፣ ከዶሮው፣ ከጠላው ሽታ ጋር ቡናውም በእጣን ታጅቦ ቤቱ በመልካም መአዛ ታውዶ፣ ቤተሰቡ ከወዳጅ ዘመድና ከጎረቤቱ ጋር ተሰባስቦ እየበላ እየጠጣ፣ አበባዮሽ የሚጫወቱ ታዳጊዎች፣ የእንኳን አደረሳችሁ በወረቀት የተሳለ የአበባ ስጦታ የሚያበረክቱ ወዶች ልጆች አካባቢን እያደመቁ በዓሉን በደስታ እያሳለፋችሁ እንደሆነ ተስፋ እናደርጋለን። በሀገር ባህል ልብስ መድመቁ እንደተጠበቀ ሆኖ ነው ታዲያ። በዚህ መካከልም በትምህርት፣ በትዳር፣ በኑሮ፣ በሌላም የልባቸው መሻት እንዲሳካላቸው ምርቃቱ፣ ለሀገር ሰላም መመኘቱ በአዲስ ዓመት የተለመደ ነው፡፡

በዓል በዚህ ድባብ ውስጥ እንዲያልፍ በማድረግ ሴቶች ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛሉ። ለበዓል የሚሆነውን ገበያ ከመገብየት ጀምሮ ተሳትፎአቸው በእጅጉ የጎላ በመሆኑ ነው ሚዛኑ ወደ ሴቶች ያደላው። ምግቡን አዘጋጅቶ ማቅረቡ በመስተንግዶውም ብሉልኝ ጠጡልኝ የሴቶች ድርሻ ትልቅ ነው። በዓልን ምክንያት በማድረግ በመዲናችን ዞር ዞር ብለን ሴቶችና የበዓል ውሎአቸውንና በበዓላት ወቅት ያለባቸውን የሥራ ጫና በተመለከተ በተለያየ የሙያ ዘርፍ ላይ ያሉ እንስቶችን አነጋግረናል፡፡

ታዲያ ካነጋገርናቸው አንዳንዶቹ በሙያ ማነስ ይሁን ድካምን ለመቀነስ ግልጽ አላደረጉትም ግን በተወሰነ ደረጃ በወላጆቻቸው ቤት የበዓል ሥራ እንደሚያሰሩ ነግረውናል። ከዛ በተቃራኒው ደግሞ ለሥራቸው ቅድሚያ የሚሰጡ እንስቶችም አጋጥመውናል።

በበዓል መዳረሻ ሥራ ከሚበዛባቸው የአገልግሎት መስጫዎች መካከል የውበት ሳሎኖች ተጠቃሽ ናቸው። ሴቶች በዓሉን አምረውና ደምቀው ለመዋል በዘመናዊው ስቲም፣ በባህላዊው ወይባ ጢስ፣ በፀጉር ተኩስና ሹሩባ እንደምርጫቸው ይጠቀማሉ። የውበት ሳሎን ሥራ ላይም በስፋት የሚገኙት ሴቶች ናቸው፡፡

በዚህ ዘርፍ ላይ የተሰማሩት በዓልና ሥራን እንዴት አጣጥመው እንደሚያሳልፉ ቦሌ አካባቢ ከሚገኙ የሴቶች ውበት መጠበቂያ ሳሎን ወደ አንዱ ጎራ በማለት የፋና ወይባ ጢስና ስፓ ባለቤት ወይዘሮ ፋና ኤጀሬን አገኘናቸው። በመልካም ፈገግታ የተቀበሉን ወይዘሮ ፋና ምንም እንኳን አዲስ ዓመት በአዲስ ተስፋና በአዲስ መንፈስ ሁሉም ሊቀበለው እንደሚገባ ቢያምኑም ደስታውን ቅድሚያ የሚሰጡት ለደንበኞቻቸው ነው። እንደ ፍላጎታቸው አስተናግደው ተውበውና ተደስተው ሲሄዱ ነው የበለጠ የሚያስደስታቸው፡፡

«ሴቶች ለበዓል ያዘጋጁት ምግብ ብቻ ሳይሆን እነርሱም ሲዋቡ በዓሉ ይደምቃል። ለዚህ ነው ሴቶችን ለማስዋብ ቅድሚያ የሰጠሁት» የሚሉት ወይዘሮ ፋና የሴቶች ውበት ሳሎን ከመክፈታቸው በፊትም በኪነጥበቡ ውስጥ ስለነበሩ የሥራ ዘመናቸው ሁሉ ሌሎችን በማስደሰት ነው ያሳለፉት። እራሳቸውን ለሌሎች ደስታ እንደተፈጠሩ አድርገው ነው የሚያዩትም፡፡

ለሌሎች ደስታ ለመፍጠር እርሳቸው ብቻ ሳይሆኑ በሥራቸው ያሉ ሠራተኞች ጭምር ተባባሪያቸው እንደሆኑ ይገልጻሉ። ሙሉ ጊዜያቸውን ለደንበኞቻቸው ቢሰጡም ለበዓል የሚጠበቅባቸውን የሴትነቱ ጉዳይም ቢሆን እንደማይቀርባቸውና በሙያ እንደማይታሙ አጫውተውናል። በቤት ውስጥ በሥራ መተጋገዙ እንዳለና እርሳቸውም አጋዥ እንዳላቸው ነው የነገሩን። የበዓሉ ዕለትም ለበዓል የተዘጋጀውን ምግብና የሚጠጣውንም በመያዝ በሥራቸው ቦታ ከሠራተኞቻቸው ጋር ደመቅ አድርገው እንደሚውሉና እግረ መንገዳቸውንም ደንበኛ ከመጣ ሥራቸውም እንደማይስተጓጎል ነው የገለጹልን፡፡

ወይዘሮ ፋና ሥራቸው በደማቸው ውስጥ የገባ ያህልን ነው በነበረን ቆይታ የተረዳነው። በሥራቸው የበለጠ ደንበኞቻቸውን ለማስደስት እንዲያስችላቸው ከኪራይ ቤት ወጥተው በግላቸው የሚሰሩበት የመሥሪያ ቦታ ለማግኘት ምኞታቸውና ፍላጎታቸው ነው። በ2016 ዓ.ም እድሉ እንዲገጥማቸው ይመኛሉ። በእናታቸው ሞት የተጎዳው አእምሯቸውም ነፃ ሆኖ አዲሱ ዓመት የሰላም እንዲሆንላቸውም እንዲሁ ተመኝተዋል፡፡

ሌላዋ ያነጋገርናት ወጣት መድኃኒት ሳይመን ትባላለች። መድኃኒት በአዲስ አበባ ከተማ ተወልዳ ያደገች ቢሆንም ቤተሰቦችዋ የጋምቤላ ክልል ተወላጆች በመሆናቸው በዚያ አካባቢ ለበዓል የሚደረገውንም ዝግጅት የማየቱን እድል አግኝታለች። እናትዋም ስለአካባቢው ባህል ስለሚነግሯት ጠንቅቃ ታውቃለች። በመሆኑም በጋምቤላና በምትኖርበት አዲስ አበባ ከተማ ለበዓል የሚደረገውን ዝግጅትና የሴቶችን የሥራ ጫና በንጽጽር እንዲህ አጫውታኛለች፡፡

ወጣት መድኃኒት በጋምቤላ ቤተሰቦችዋ ለበዓል ስለሚያደርጉት ዝግጅት እንደነገረችኝ፤ ለበዓል ዝግጅት ሴቶች ምግብና የሚጠጣ ነገር ማዘጋጀት ብቻ ሳይሆን ቤት ማሳመርም ይጠበቅባቸዋል። ቤት የማሳመሩ ሥራ ከባድ ነው፡፡አሮጌው ቤት ለአዲስ ዓመት አዲስ እንደሆን ስለሚፈለግ ባህላዊ የሣር ቤት ከሆነ የሣር ክዳኑ ይቀየራል። ግድግዳው በጭቃ፣መሬቱም እንዲያምር ይደረጋል። የሣር ክዳኑን ለመቀየር ካልሆነ በስተቀር ወንዶች አይሳተፉም። ሴቶች ናቸው የሚያሳምሩት። ዘመናዊ ቤትም ቢሆን ቀለም በመቀባት ለማሳመር ጥረት ይደረጋል። በመተጋገዝ የሚሰራ ቢሆንም ቤት ማሳመሩ ጊዜ የሚወስድና አድካሚ ነው፡፡

ለበዓል የሚሆን ምግብና መጠጥ የማዘጋጀቱ ሥራም የሴቷ በመሆኑ ከቀናት በፊት ጀምሮ ነው ሴቶች ሥራ የሚጀምሩት። ለበዓል የሚዘጋጀው ምግብ በአካባቢው አጠራር «ኮብ» ይባላል። ግብዓቱ የበቆሎ ወይንም የስንዴ ዱቄት ሲሆን የራሱ አሰራር ሂደትም አለው። ለማባያ የሚዘጋጀው ደግሞ አሣ ወይንም ጎመን በሥጋ በቅቤ ነው። ጣፋጭ የሆነ ለበዓል ብቻ የሚዘጋጅ ምግብ እንደሆነ ነው መድኃኒት የነገረችን፡፡

ስለመጠጥ ዝግጅቱም መድኃኒት እንደገለጸችልን፤ መጠጡ ከሰሊጥ የሚዘጋጅ ሲሆን ሰሊጡ በባህላዊው ወፍጮ በሰው ጉልበት ተፈጭቶ በደንብ ከላቀጠ በኋላ ውሃ ውስጥ ይዘፈዘፋል። እንዲፈላም እርሾ፣ ለጣዕሙ ደግሞ ስኳር ይገባበታል። በዚህ መንገድ ለተወሰነ ቀን ከቆየ በኋላ ውሃው ጠልሎ ለመጠጥ ይዘጋጃል። በአካባቢው አጠራርም «ከኛ» ይባላል። የበዓል እለትም ዘመድ፣ ጎረቤት ተጠርቶ በጋራ ይጠጣል ፡፡

ለበዓል የሚዘጋጀው የምግብ እና የመጠጥ ልዩነት ካልሆነ በአዲስ አበባ ከተማም ቢሆን እርሷ እንዳየችው የበዓል ዝግጅት ለሴቶች አድካሚ ነው። ቤት ማስዋቡ፣ የቤት ውስጥ የእቃ አቀማመጥ መቀየር፣ ቤቱንና የሶፋ ልብሶችን ማጠብ አለ። በምግብ ዝግጅት በኩልም ዶሮና ሥጋ ነው የሚሰራው። የበዓል ሥራን በመተጋገዝ ካልሆነ በአንድ ሰው ከባድ እንደሆነም ገልጻለች። እርስዎ ከወላጆችዋ ጋር ስለሆነች ከእህቶችዋ ጋር እናታቸውን በሥራ እንደሚያግዙ ነው የነገረችን፡፡

ሌላዋ ሃሳባቸውን የሰጡን ወይዘሮ አዜብ ይልማ ይባላሉ። ወይዘሮ አዜብም ለረጅም ጊዜ ከኢትዮጵያ ውጭ ነው የኖሩት። በተለያየ ጊዜ ወደ ሀገራቸው ቢመጡም በየትኛውም በዓል ላይ የመገኘት እድሉ አልገጠማቸውም። አሁን ላይ ግን ኑሮአቸውን በሀገራቸው አድርገዋል። 2016 ዓ.ም አዲስ ዓመት በሀገራቸው የመጀመሪያ በዓላቸውም ነው።

በውጭ ሀገር ሲኖሩ ሥራቸው ከተለያዩ የውጭ ሀገር ዜጎች ጋር በመሆኑ ምግብ አዘጋጅተው በዓል ለማስመሰል እድሉ አልነበራቸውም። በልጅነት ከቤተሰብ ጋር ሆነው ለበዓል የሚደረገውን ዝግጅት በማስታወስ በመከፋት፣ ቤተሰብ ጋር ስልክ ደውለው በማልቀስ ነበር የሚያሳልፉት፡፡

ለቅሶውም መከፋቱም አልፎ ሀገራቸው ገብተው የመጀመሪያቸውን በዓል አዲስ ዓመትን ለማክበር በመጓጓታቸውም ከሳምንት በፊት ጀምሮ የበዓል ድባብ ለእርሳቸው ልዩ ነበር። ታዲያ ለበዓል ዝግጅት ድርሻቸው ምን ይሆን ብለን ስንጠይቃቸውም ሳቅ ነበር የቀደማቸው። ሙያው ጠፍቶባቸው እንደሆን ጠየቅናቸው። የልጅነቱ እንዳልተረሳና በምግብ ዝግጅቱ ትልቁን ድርሻ ባይዙም ቤት በማጽዳትና በማሳመሩ እንዳሉበት ተናግረዋል፡፡

ቤተሰባቸው ሰፊ እንደሆነና ቀደም ሲል ጀምሮ ሰፋ ባለ ሁኔታ ዝግጅት እንደሚደረግ ነው ወይዘሮ አዜብ የነገሩን። ወደኋላም መለስ ብለው እንዳጫወቱን አባታቸው በሕይወት በነበሩ ጊዜ ለበዓሉ ለእርድ የሚዘጋጀውን በግ መርቀውና ለቤተሰባቸው፣ ለሕዝባቸውና ለሀገራቸው ቸር ተመኝተው ነው የሚባርኩት። በሀገር ባህል አልባሳት ቤተሰቡ ደምቆ በዓሉን ለማሳለፍ የነበረውን ሁኔታ በመልካም ጎኑ ያስታውሳሉ፡፡

ሴቶችና የበዓል ሥራ ጫናን በተመለከተም ወይዘሮ አዜብ እንደገለጹት፣ በዓሉ የደመቀ እንዲሆን፣ ቤቱ ጽዱ እንዲሆንና እንዲያምር ማድረግ፣ ገበያ መገብየት፣ የማጀቱ ሥራ፣ መስተንግዶው የሴቶች ድርሻ በመሆኑ ከአዘቦቱ የበዓሉ ሥራ ጫና አለው፡፡

ወይዘሮ አዜብ በውጭ በኖሩባቸው ሀገራት ለበዓል የሚደረግ ዝግጅትና በኢትዮጵያ ካለው ጋርም በንጽጽር ሲገልጹ እዛ ሥራን በሚያቀሉ ማብሰያ ስለሚጠቀሙና የምግብ ዝግጅቱም እንዲሁ እንጀራና ኮስተር ያለ ወጥ ባለመሆኑ ድካሙ ይለያያል። በኢትዮጵያ ግን ቤተሰብ ውስጥ ያሉ ሴቶች ሁሉ እረፍት እንደሌላቸውና ሥራውም በአድካሚ ሂደት ውስጥ እንደሚያልፍና ሰፊ ቤተሰብ ያለው ደግሞ ዝግጅቱም ሰፊ እንደሚሆን ነው ያስረዱት፡፡

ወይዘሮ አዜብ የውጭውንም የሀገራቸውንም የበዓል አካባበር ሁኔታ የማየቱን እድል ቢያገኙም የሀገራቸው የበዓል አከባበር እንደሚያስደስታቸው ነው የገለጹት። አሁን ላይ ያለው ሀገራዊ ወቅታዊ ሁኔታ እንደቀደመው በዓልን ለማድመቅ የሚመች እንዳልሆነ ጠቅሰው፣ አዲሱ ዓመት የሰላም እንዲሆን መመኘት ደግሞ ግድ ነው ብለዋል፡፡

«በአዲሱ ዓመት ሀገራችን ሰላም እንድትሆን፣ ሕዝቧም በፍቅር ተሳስቦ እንዲኖር ነው ምኞቴ። በዓሉን የምናከብረው፣ ልጆቻችን ተምረው ነገን ተስፋ የሚያደርጉት እኛም ሰርተን ለማደግ ሰላም ያስፈልጋል» በማለት ሰላም ያለውን ዋጋ በማስቀደም በዓልና ሴቶችን በተመለከተ ሀሳቧን ያካፈለችን ደግሞ ወይዘሮ ሰላም ሀብቶም ትባላለች።

ሰላም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በኤሌክትሪካል ኢንጂነሪንግ ተምርቃለች። በተለያዩ አገልግሎት መስጫዎች ውስጥ «በካሜራ እይታ ውስጥ ኖዎት» የሚሉ መልእክቶች ተለምደዋል። እሷም ለዚህ አገልግሎት የሚውሉ ካሜራዎችን ከውጭ ሀገራት በማስመጣት ሥራ ላይ ነው የምትገኘው።

ወይዘሮ ሰላም እንደቀደመው የሚበላውንም የሚጠጣውንም ለማዘጋጀትና በሀገር ባህል ደምቆ በዓሉን ለማሳለፍ የኑሮው ሁኔታ ምቹ እንዳልሆነ ትገልጻለች። ከሁሉም በላይ ደግሞ በሀገራችን ወቅታዊ ሁኔታ በዓልን ማሰብ ቀርቶ የእለት ጉርስ የቸገረው ብዙ ወገን ባለበት በተለየ ሁኔታ ለበዓል ዝግጅት ማድረጉ ብዙም አልታያትም። ካላት አካፍላ ወይንም እገዛ አድርጋ ሌሎችንም አስቦ መዋሉ ላይ ሁሉም ሰው ትኩረት እንዲያደርግ ነው መልእክቷ፡፡

የኑሮ ውድነቱን ማዕከል አድርጋ በጎ ተግባሩንም ሳይቀርባት በዓሉን እንደቤቷ ለማክበር መዘጋጀቷንም ገልጻልናለች። ታዲያ በሙያው በኩልም የሚስተካከላት እንደሌለ ነው የተናገረችው ወይዘሮ ሰላም አንዳንዶቹ በእናቷ እገዛ ነው የሚሚሉት ልክ እንደ «ቴክ አዌይ» መሆኑ ነው፡፡

ሥራውን ለማቅለልም እንደ ሽንኩርት መፍጫ ያሉ ዘመን ያፈራውን ቴክኖሎጂ በመጠቀም ድካምን ለመቀነስ ጥረት እንደምታደርግም ነው የገለጸቻቸው። በዚህኛው አዲስ ዓመት ካለው ሀገራዊ ሁኔታ በዓልም ቀለል ለማድረግ ስለሆነ ፍላጎትዋ ከዚህ ቀደም ሰፋ ያሉ ዝግጅቶች እንደማይኖሩና ድካምም እንደማይኖርባት አስረድታለች፡፡

ወይዘሮ ሰላም እንደምትለው የበዓል ሥራን አድካሚነት እየተገነዘበች የመጣችው ትዳር ከያዘች በኋላ ሲሆን ቤተሰቦችዋ ጋር ከነበረችበት ጊዜ ኃላፊነቷ ጨምሯል። በቤት ውስጥ ለበዓል ዝግጅት የሚያስፈልጉትን ማድረግ ብቻ ሳይሆን፣ ለበዓል ጥየቃ ወደ እርሷም፣ ወደ ባለቤትዋ ቤተሰብ ቤት መሄድ ተጨማሪ ሥራዎች ናቸው። በዓል ሥራው ብቻ ሳይሆን፣ ሰዎች ለረጅም ሰዓት ተቀምጠው በመብላትና በመጠጣት የሚያሳልፉት ጊዜም አድካሚ እንደሆነና የበዓል ድካም መቀነስ እንዳለበት ትገልጻለች፡፡

አሮጌ ዓመት አልፎ በአዲስ ሲተካ ሁሉም የሚጠብቀው ተስፋ አለ ወይዘሮ ሰላም ግን «ለእኔ ከአንድ ቀን ወደ ሌላኛው ቀን ስሸጋገር አዲስ ነው። የአንድ ዓመት እድሉ ሲሰጠን ደግሞ የበለጠ የተሻለ ነገር ሰርተንና ጥሩ ሆነን መገኘት አለብን ብዬ ነው የማስበው» በማለት ሰዎች በሥራው ለማደግም ሆነ ከመጥፎ ባህሪያቸው ለመለወጥ አንድ ዓመት ሙሉ መጠበቅ እንደማያስፈልግ፣ ሰዎች በየቀኑ እየተቀየሩ መሄድ እንዳለባቸው በዚህ አጋጣሚ መልእክት አስተላልፋለች፡፡

ልዩ ዕትም

# ‹‹የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ለየት ያሉ ባህርያት አሉት››

\- አባ ገብረሃና ገብረጻድቅ

ጽጌረዳ ጫንያለው

**ሊቀ ኅሩያን አባ ገብረሃና ገብረጻድቅ ይባላሉ። የቤተክርስቲያኑን ትምህርት ከዘመናዊው ጋር አዋህደው የተማሩ ናቸው። ኢትዮጵያን ለየት የሚያደርጋትን የዘመን አቆጣጠር ጭምር አብጠርጥረው ያጠኑ ናቸው። በቴኦሎጂ ወይም የነገረ መለኮት ትምህርት የሁለተኛ ዲግሪ አላቸው። በዘመናዊው ደግሞ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኤሌክትሪካል ኮሚዩኒኬሽን ኢንጂነሪግ ተመርቀዋል። በእነዚህ ትምህርቶቻቸው ደግሞ በተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ መሥሪያ ቤቶች የሰሩ ሲሆን፤ አሁን ላይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ቅድስት ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ የርቀትና የኦንላይን ትምህርት ኮሌጅ ዲን እና የፓስቶራል ቴኦሎጂ መምህር ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ። የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍልም ከእኚሁ ምሁር ጋር ቆይታ አድርጓል፤ መልካም ንባብ፡፡**



**አዲስ ዘመን፡- ለመነሻ ያህል ስለእርስዎ የትምህርት ሁኔታ እስኪ ጥቂት ይበሉን?**

**አባ ገብረሃና፡-** በቤተክርስቲያን ትምህርት ቅዳሴ ከደብረ ዓባይ ምስክር፣ ቅኔ ደራ ሐሙሲት ከየኔታ ጥበቡ፥ የባሕረ ሐሳብ ከዬኔታ ቀለመወርቅና አቡሻህርን ከዬኔታ ብርሃነ መስቀል ጉንድ ተክለሃይማኖት ገዳም እንዲሁም በነገረ መለኮት ትምህርት የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ዲግሪ ቅድስት ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ተምሬያለው። በዘመናዊው ትምህርት ደግሞ ቤት ከቤተክርስቲያን አገልግሎት ጎን ለጎን የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን በጎንደር እድገት ፈለግ ትምህርት ቤት፣ የመሰናዶ ትምህርቴን አዲስ አበባ ቅድስት ሥላሴ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተከታትያለሁ። ከዚያ ለከፍተኛ ትምህርት መግቢያ በማምጣት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመደበኛው ትምህርትም በኤሌክትሪካል ኮሚዩኒኬሽን ኢንጂነሪግ ተመርቄያለሁ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በሥራው ዓለም በሃይማኖቱም ሆነ በዘመናዊው ትምህርት የት የት ሰሩ?**

**አባ ገብረሃና፡-** በምንኩስናው ዓለም ውስጥ ሆኜ በግልም በመንግሥትም እንዲሁም መንግሥታዊ ባልሆኑ መሥሪያ ቤቶች ውስጥ ሰርቻለሁ። ለአብነት በንግድ ሚኒስቴር ውስጥ በሁለት የሥራ ዘርፍ ሰርቻለሁ። ይህም የኢንስፔክሽንና ሬጉላቶሪ ዳይሬክቶሬት ውስጥ የኳሊቲ አሹራንስ ኢንስፔክሽን ቁጥጥር ባለሙያ እና በአይሲቲ ዳሬክቶሬት የኔትዎርክና ሲስተም አድሚን ባለሙያ ሆኜ ሰርቻለሁ።

በተጨማሪ ደግሞ በልማት ባንክ በICT በኔትዎርክ ሲስተም ዝርጋታ ሰርቻለሁ። ከአንድ የቻይና ድርጅት በገጠር ሶላር ኢነርጂ ተከላ ሱፐርቫይዘር በመሆን አገልግያለሁ። በመንፈሳዊው ዓለም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ውስጥ በልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን በአቅም ግንባታ ፕሮጀክት አስተባባሪነት፥ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የቴሌቪዥን መገናኛ ብዙኃን ሥርጭት ውስጥ በአይቲና በሰው ኃይል አስተዳደር ኃላፊነት አገልግያለሁ። በአሁኑ ወቅት በቅድስት ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ የርቀትና ኦንላይን ትምህርት ዘርፍ የኮሌጅ ዲን እና የፓስቶራል ቲኦሎጂ መምህር ነኝ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ በርካታ አማኞች እና ዕሴቶች ያላት ሀገር ናት እያልን ከዛ በተጻራሪ የሚሰሩ ነገሮች ለምን ተበራከቱ ?**

**አባ ገብረሃና፡-** ኢትዮጵያ ውስጥ አማኞች እና እምነት የለም ብዬ አላምንም። እምነቱም አማኞችም አሉ። ከተሰራብን አንጻር ልንሆን ከምንችለው፣ የመጣብን ብዙ ቢሆንም አሁን እየሆነብን ያለው ግን ጥቂቱን ነው። ይህ ደግሞ ያለ እምነት አይመለስም ነበር። ቅዱሳንና እውነተኛ አማኞች ስላሉ ከብዙ ነገር ተጠብቀናል። የእነሱ እውነትና ፀሎት ከመጣብን ትልቅ ችግር ታድጎናል። በእነርሱ እውነትና ፀሎት ዛሬን አይተናል።

ስብራታችን የቱ ጋር ተፈጠረ ከተባለ መልከ ብዙ ነው። አንዱን ብናነሳ የተሰራብንና እኛነታችንን ያስተወን ነገር ነው። ፋይዳውን ሳናስብና ሳንመረምር መግባታችን እውነታዎቻችንን ወስዶብናል። ያ እውነት ደግሞ ማህበረሰብን ከእሴቱ ከእምነቱ ከእውነቱ ጋር በመጠኑ ለያይቶታል ብሎ መውሰድ ይቻላል። የኢትዮጵያዊነት እውነትን የሚሸረሽሩ ብዙ ነገሮች እንዲፈጠሩ አድርጓልም።

አንዱ የሚፈለገው እውነት አምላካዊ ማንነትን፤ መንፈሳዊ ሕይወትን ጥሎ ዓለማዊነትን፤ የሥጋዊ ፍላጎቶችንና ምኞቶችን ማሳኪያ መንገድን የሚያመቻች በጀት ነው። ሌላው ደግሞ ጉልበት ኃይል ሲሆን፤ ገንዘብ አለ አይዶሎጂ አብረው ይተባበራሉ። ይሁን እንጂ እነኚህ ሁሉ ተዳምረው እስካሁን እምነትን መጣል አልቻሉም፤ አማኒያንን ከእምነታቸው ማላቀቅ አልሆነላቸውም። በእርግጥ በዚህ መካከል ሰዎች ከእምነት አልወጡም ማለት ያስቸግራል። ብዙዎች ወርደዋል፤ ብዙዎች ተንጠባጥበዋል፤ ብዙዎች ከኋላ ቀርተዋል። እናም መወሰድ ያለበት የአማኒያንና የእምነት ችግር በሀገሪቱ ላይ ኖሮ ሳይሆን የተሳሳቱ እሳቤዎች ጎልተው መታየታቸው ነው ከጠንካራው እምነት ይልቅ ውድቀታችን ገዝፎ የታየው።

እኛ በእምነትም ለዓለም የምንተርፍ ምሳሌ ልንሆን የምንችል፤ እምነት ባፈራው እውቀት፤ እውነት በሰጠን ኃይል፤ እምነት በሰጠን ፀጋ ዓለምን የምናጠግብ ነን። ሆኖም የምናየው ሌሎችን መሆን ስብራታችንን እንዳንለየው አድርጎናል። ለእኛነታችን ፍላጎትና ስሜት ቅርብ የሆኑ ጥበቦችና ፍልስፍናዎች ቢኖሩንም ምርጫችን ግን አይደሉም። ሁሌ ታላቆቹ የአውሮፓውያን አስተሳሰብና ፍልስፍና ናቸው። የእነርሱ ባህል ባህላችን እንዲሆን እንደክማለን። ይህም የረቀቀ እውቀትም ኃይልም ከኢትዮጵያ ውጭና ውስጥ በሆነ በተቆራኘው ሕይወት ሕዝብና ሀገር ላይ ይሰራል። እናም ያንን በራስ ማንነት ማከም ካልተቻለ የስብራቱን ቦታ በቀላሉ ማወቅ አዳጋች ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ታዲያ ከዚህ አንጻር እንዴት ማህበረሰቡን ወደነበረበት ልንመልሰው እንችላለን ?**

**አባ ገብረሃና፡-** ለዚህ መፍትሔው አራት የእርቅ መርሆች ናቸው። የመጀመሪያው እንደ ሕዝብ ከፈጣሪ ጋር መታረቅ አለበት። ለሥራው በደል ይቅርታ የሚጠይቅ፤ ይቅርታ ለጠየቀው ይቅር የሚል፥ በጎ የሰራውን በአደባባይ በእውነት መግለጥ ይገባል። ሁለተኛው ሰው ከራሱ መታረቅ አለበት። ማለትም እንደ ሕዝብ ውስጡ ካለበት በቡድንም ሆነ በግል ከሰራው መጥፎ ነገር፤ ከክፋትና ከጥፋት ድርጊቱ መመለስ አለበት።

ሦስተኛው እርቅ ሕዝብ ከማንኛውም ፍጥረታት ጋር መታረቅ ይኖርበታል። ተፈጥሮን አክባሪና ተንከባካቢ መሆን ይገባዋል። የመጨረሻው ሕዝብ ከመሪ ጋር መታረቅ አለበት። እናም እነዚህን ካደረግንና በዚህ እሳቤ ውስጥ የምንጓዝ ከሆነ የምፈልገው ስኬት ላይ እንደርሳለን። ይህንን ውጤታማ ለማድረግ ሀገር በቀል ኃይላችንን እውቀታችንን ጥበባችንን መጠቀም ይኖርብናል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ዛሬ በጎ ሰዎች ያስፈልጉናል፤ ሀገርን የሚያደኑ እና የሚያሻግሩ ሰዎች ያሻናል። እነኛን ሰዎች እንዴት ማግኘት እንችላለን?**

**አባ ገብረሃና፡-** ሁልጊዜ ከግል እሳቤ ወጥተን ወደ ቡድን፤ ከቡድን እሳቤ ወጥተን ወደ ማህበረሰብ ከማህበረሰብ እሳቤ ወጥተን ደግሞ ወደ ሀገር መሻገር አለብን። ሀገር የሚለውን እሳቤ ለማምጣት ትንሹ ግለሰብ ነው። ትልቁ ደግሞ ሀገር ነው። እናም ትልቁን ሀገር እንገንባ ካልን ተፈቃቅደን፤ ተዋደን መኖር አለብን። ዓለም አንዱ ጠግቦ የሚተፋባት ሌላው ደግሞ ተርቦ የሚያድርባት መሆን የለባትም። በጎ ነገር ከግለሰብ ሊነሳ ይችላል። በጎ ሃሳብ ከአንድ ቦታ ሊመነጭ ይችላል። ግን ትልቁ ነገር ያ በጎነት ሀገር እስካልተቀበለው፣ የማህበረሰብ እስካልሆነ፣ በጋራ የማያቆምን ከሆነ እሱ መመርመር አለበት።

በጎነትን የሚጠላ መንግሥትና ግለሰብ አለ ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው። በበጎነት ስም ክፋቶች ስለበዙ በጎነት ሰጥቶ መቀበል ሆነ፤ በጎነት ምድራዊ ዋጋን ፈለገ። ነገር ግን መሆን ያለበት የምናደርገው በጎነት ስለነጋችን መሆን ይጠበቅበታል። በጎነት ከእኔ የመነጨ ሳይሆን እኔ ጋ የነበረ የእሱ የሆነ ነገር ነው የምሰጠው የሚለውን እሳቤ የያዘ መሆን ይገባዋል። በጎነት ስንል ሀገር፤ ማህበረሰብንና ግለሰብን ይጨምራል። ከየትኛውም ይነሳ ከየት ዓላማ እና ግቡ ግን አንድ ነው። የአንድ ሰውን ከችግር ስናወጣ ከአካላችን መካከል ታማ የነበረችን ጣት ማከም እንደማለት ነው።

በጎነት ከቅድስውና እና ከንጽህናው ውጭ ለሌላ ዓላማ፤ ከማንነቱ ውጭ ለሌላ ተግባር ሲውል በጎነት ራሱ የነበረው እሴት እና ዋጋ ያጣል። በጎነት እሴቱን ካጣ ደግሞ በጎነት የሚለው ቃል ይጠፋል። በጎነት እንደግለሰብም ከሃይማኖት አባት፤ እንደ ማህበረሰብም ከአንድ ማህበረሰብ ይጀምራል በየደረጃው ሃይማኖት እና የሀገር መሪ ኃላፊነት አለበት። ስለዚህ በጎነት መነሻው በውስጣችን ባለችን የሕሊናችን መንፈሳዊ ኃይል ነው። ዋናው ቁም ነገሩ ከየት መነጨ ሳይሆን የት ላይ ደረሰ፤ ዋጋው እንዴት ተተመነ የሚለው ነው።

**አዲስ ዘመን፡- መከባበር ፤መዋደድ፤ አብሮነት እና የመሳሰሉት እሴቶች መሸርሸር እንደ ሀገር ዋጋ አያስከፍለንም?**

**አባ ገብረሃና፡-** እያስከፈለን ነው እንጂ። አሁን እኮ የኃይማኖት አባቶች አይደመጡም፤ መሪዎች አይሰሙም፤ ወላጆች በልጆቻቸው ክብር ያጡበት ጊዜ ነው። መምህራን በተማሪዎቻቸው ዘንድ ዋጋ የላቸውም። ሃይማኖትም የማህበረሰቡ አንዱ ነጸብራቅ ሊሆን ይችላል። መሪም የማህበረሰብ ነጸብራቅ ነው። ግን ሁሉም በንቀት ሲታዩ ይስተዋላል። እናም እንዳንሰማማ፤ እንዳንከባበር፤ እንዳንደማመጥ፤ እንዳንተባበር ያደረገን ነገር ምንድነው የሚለው መመርመር ይኖርበታል። አንዱ ሁላችንም ከእራሳችን እሴት ለመውጣት ከምናደርገው ትግል የመነጨ ይመስላል።

መከባበር የእኛ እሴት ነው። እሱን አንፍልግም ብለን የሌላው እሴት እና የሌላውን ማንነት ይዘን በዚያ ማንነት ውስጥ እኛን ስንፈልግ ደግሞ እንዲህ አይነት ነገሮች መከሰታቸው የግድ ይላል። ስለዚህ ይህንን ችግር እልባት እንስጠው ከተባለ እኛነታችንን መፈለግ ያለብን እኛ ውስጥ ብቻ ነው። ማንነት እና እሴታችን ውስጥ እኛን ማየት ይገባናል።

የሌላው እሴት እና የሌላው ማንነት ይዘን በዚያ ማንነት ውስጥ እኛን እንፈልጋለን ማለት የጠፋብን እቃ ሌላ ቦታ ነው የምንፈልግበት ቦታ ደግሞ ሌላ ቦታ ነው እንደማለት ነው። እውነት ለመናገር የሃይማኖት አባቶቻችንን የማክበር ሥርዓታችን ጠፍቷል በሚባልበት ደረጃ አይደለም ቀንሷል እንጂ። ስለሆነም ያለውን ማቅናት ከምንም በላይ ያስፈልጋል።

አባቶቻችን አርዓያዎቻችን ናቸው። እንደ አርዓያም የመከተል ልምድ ነበረን። አሁን ግን ያንን የአርዓያነትን ትርጉም ዘመኑ ወደ ሌላ ወስዶታል። አሁን ላይ ከኃይማኖት አርዓያነት ውጭ ነው ትውልዱን እያኖርነው ያለነው። እነሜሲ የኢትዮጵያ ወጣቶች አርዓያዎች ናቸው። ቡድኖቻችን እነአርሴናል እና ማንቸስተር ሆነዋል። እምነቶቻችን እና ፍልስፋናዎቻችንም ምንጮቻቸው አውሮፖዊያን ናቸው። ሀገር በቀሉ፤ ያስተሳሰረን፤ በአንድ የጠበቀን እርስ በእርሳችን ልንነጋገርበት እና ልንወያይበት የምንችለውን እሴት እና ወግ ተትቷል። አይጠቅምም ወደሚለው ደረጃ ደርሷል። ስለዚህ መከባበራችን ተሸርሽሮ እንዳናቀናው ሆነናል።

**አዲስ ዘመን ፡- ወደ ራሳችን ስመመለስ ምን ማድረግ አለብን?**

**አባ ገብረሃና፡ -** የቀደመውን በቅንነት እና በእውነት እንመርምር። የምንመረምረው ስህተትን ለማውጣት ሳይሆን የበለጠ በጎነታችንን ለማሳየት ነው። በትናንቱ ማንነቶቻችን ውስጥ የነበሩ በጎ ያልሆኑ ስብራቶቻችን እንኳን ቢኖሩ ዛሬም እንዳንደግማቸው ይጠቅሙናል። የትላንት መልካምነቶች ደግሞ ለዛሬው መሰረቶቻችን ይሆናሉ። ከሌላው ዓለም ከምናመጣው ይልቅ የራሳችን ከእኛም አልፎ ለዓለም የሚተርፉ እሴቶች አሉን። እነዚህን እሴቶች መጠበቅ ያስፈልጋል።

በእርግጥ የውጭውም ሙሉ ለሙሉ አይጠቅምም ማለት አያስፈልግም። መመርምርና ለእኛ በሚጠቅም መልኩ ወደራሳችን ማምጣት አለብን። እውቀት ጥበብ የአንድ ሀገር ብቻ አይደሉም፤ ዓለም አቀፋዊ ይዘት ነው።

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

ልዩ ሰትም

# ‹‹የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር...

ከገጽ ገጽ 8 ዞሯል



ከእነሱ ክፉውን አስቀርተን የእኛን በጎውን ጨምረን እሴቶቻችን ማጎልበት አለብን። የውጭ አያስፍልግም የሚል ፍልስፍና የለም። ሁሉም ጥሩ ነው የሚል አለመካከትም ሊኖር አይችልም። የትናንት አይጠቅምም የሚለው ነገር ትክክል አይደለም። የትናንቱ ጥበብ ነው፤ የዛሬው ደግሞ ማንነታችን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ከሌሎች ሀገራት የተለየ ነው። ታሪካዊ አመጣጡ ምን ይመስላል?**

**አባ ገብረሃና፡-** ዘመን ረቂቅ አኃዝ ሲሆን ሥራውን እውነት ነው። እውነት ደግሞ የእኛን የምድራዊ ሕይወት ትርጓሜ የምንሰጥበት፥ ሁኔታዎች ማወቅና መረዳት የምንችልበት እንዲሁም ነገሮችን የምንተነትንበትና የምንለካበት መሣሪያ ነው። የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ሁለት መሠረታዊ ምንጮች አሉት። አንደኛው ተፈጥሯዊ ነው። ሁለተኛው ሃይማኖታዊ ነው። ተፈጥሯዊ ምንጭ ስንመለከት የሰው ልጅ የሕይወት ክንዋኔና የሥርዓተ አምልኮቱን አፈፃፀም ያለ ጊዜ እና ያለ ቦታ ማከናወን፥ መግለፅና ማሰብ አይችልም። ስለሆነም በተፈጥሮ የሚከናወኑ ዑደቶችን ተከትሎ የድርጊት፥ የሁኔታዎችና የእሳቤ መለኪያዎች ናቸው። አሁንም በጊዜ ውስጥ ሆነን እየተነጋገር ነው። በዚህም ኢትዮጵያ ለየት የሚያደርገው አንደኛው የዘመን መስፈሪያና መቁጠሪያ ስልት ብዛቶች ናቸው። ምዕራባውያን መስፈሪያ የሚያደርጓቸው ሶስት ዑደቶች ሲሆኑ፤ ኢትዮጵያ ደግሞ ሰባት አዕዋዳት መሆናቸው ነው። በዚህም ሀገራችን መጥቅዕ ጠቅሳ ጊዜያት አዕዋዳትን ቀምራ፥ በዘመን አቆጣጠር የዘመን መለወጫ ዕለት ወስና፥ ባሕረ ሃሳብን አስልታ አዲስ ዘመንን ታከብራለች።

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊ ሥርዓተ ትምህርት ወይም ኃይማኖታዊ መልኩን ስናየው የአንድ ዓመት ልኬት መስከረም መባቻው በማድረግ በፀሐይ 365 ከሩብ ቀን ይዘልቃል። አመዳደቡም 12ቱ ወር እያንዳንዱ ወር 30 ቀናት እንዲሁም ጳጉሜን ተብለው የሚታወቁ ሦስቱን ዓመታት 5 በአራተኛ ዓመት 6 ቀናትን የያዘ ነው። የአውሮፓውያን አቆጣጠር የሚባለው ጎርጎርዮሳዊው ቀመር ግን ከእርሱ በፊት የነበረው የጁሊየስ ቀመርን ጨምሮ ዓመቱን መጀመሪያቸው ጃንዋሪ በማድረግ በ12 ወሮች ሲመደቡ የእያንዳንዱ ወር የቀን ብዛት 28፣ 30 እና 31 በማድረግ ይቀምራሉ።

**አዲስ ዘመን፡- አበባዮሽ እና አዲስ ዓመት ያላቸው ግንኙነት ምንድን ነው፤ የእንቁጣጣሽ ትርጓሜስ ምንድን ነው?**

**አባ ገብረሃና፡-** አበባዮሽ የሴት ልጆች የአዲስ ዓመት ብቻ የደስታ መግለጫ ጨዋታ ነው። ለዚህም ማሳያው በዘመን መለወጫ በዓመት አንድ ጊዜ በወርሐ መስከረም የምትታብበውን አበባ ወይም እንቁጣጣሽ ወይም ደግሞ አደይ አበባን በመያዝ ልጆች መጫወታቸው ነው። ተስፋችንን እንዲያለመልመው መመኘታቸውም ነው። ልጆች የዛሬ አበቦች ናቸው፤ እንደ አበባ የሚታዩ። ነገ ደግሞ ወላጆች፣ ፍሬዎች የሚሆኑበት ጊዜ ነው። እናም ያንን እንድናስብ ያደርጉናል።

እንቁ ለብቻው ሲታይ ደግሞ አንድምታውን ወይም ታሪካዊ አመጣጡ በመጽሐፈ ነገስት አንደኛ 11 ላይ እናገኘዋለን። ይህም የኢትዮጵያ ንግስት ማክዳ ወይም ንግስት አዜብ ከሰሎሞን እውቀት እና ጥበብን ሽታ በሄደችብት ጊዜ እንቁ ተሰጥቷት እንደነበር ይነግረናል። ያንን እንቁ ለአንዳድን ጣቷችሽ ሲል የሰጣትን በመያዝም እንቁ ለጣትሽ እንድንለው ሆነናል የሚሉ አሉ።

**አዲስ ዘመን፡- አዲስ ዓመት አዲስ ዘመን እንደሆነ ይገለጻል። ይህ እንዴት ይብራራል?**

**አባ ገብረሃና፡-** የአዲስ ዘመን መባቻ ዋንኛ ትርጉም የሚሰጠው በቀድሞው ዘመን በመንገድና በስልጣኔ እጥረት የተነሳ ለሁለት የክረምት ወራት የሰው ግንኙት የለውም። ምክንያቱም ታቹም ላዩም ውኃ በመሆኑ የተነሳ ወገን ከወገኑ ዘመድ ከዘመዱ ይለያያል። በአዲስ ዘመን ግን ይህ የተለያየ ሰው የሚገናኝበት፤ የራቁት የሚቀራረቡበት ልዩ የደስታ ዕለት ነው።

እንደ ሀገር አዲስ ዓመት የደስታ ጨዋታ የሚጫወቱበት፣ በአዲስ ዓመት አበባ መገለጫ የምትገለጥበት፤ ሁሉም ሰው ያለፈውን በመተው አዲስ ተስፋ እና ምኞት የሚሰንቅብት በመሆኑ በገጠር በከተማ፣ ባለው በሌለው ሰው፣ በተማረው ባልተማረው፣ በሚያምነው በማያምነው ዘንድ ሁሉ ለአንድ አይነት የሕይወት መርህ እና የተግባር ለውጥ የሚነሳበትና በአንድ አይነት መዝሙር የሚደሰትበት ጊዜ ነው።

የዘመን መለወጫ በዓል አሮጊው አልፎ አዲሱ ሲተካ፥ የክረምት ጨለማው አልፎ ብርሃን ሲመጣ፥ ከአንዱ ዘመን ወደ ሌላ መሻገሩን ሁላችን በምናከብርባት መስከረምን መባቻ ዕለት ዝናብ የሚቆምበት ፀሐይ የምትጎላበት ወንዞች የጠራ ውኃ የሚፈሱበት፣ ምንጮች የሚፈልቁበት የተዘሩት ማበብ የሚጀምሩበት፣ ሜዳዎች፥ ተራራዎችና ሸለቆዎች በአበባ የሚያጌጡበት ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በኢትዮጵያ የተለዩ እምነቶች አሉ። ይሁን እንጂ አዲስ ዓመትን አብረው ያከብራሉ አብረው እንዲያከብሩ ያስተሳሰራቸው ምንድን ነው?**

**አባ ገብረሃና፡-** በሀገራችን የተለያዩ የሃሳብ፣ የእምነት፣ የፍልስፍና እና የባህል ልዩነቶች ሊኖሩ ይችላሉ። ግን አራት ነገሮች አንድ ያደርጋቸዋል ብዬ አስባለሁ። አንደኛው ባህላችን በዓሉን የሕይወታችን የኑሮ ዘይቤን በጋራ ደስታ አንድ አድርጎ መግለፅ በመቻሉ። ሁለተኛ ልጆቻችን በአንድነት መዝሙር አበባዮሽ ጨዋታን እንዲጫወቱ ማስቻሉ። ሶስተኛው ስለሀገራቸው፤ ስለቤተሰቦቻቸው ስለወደፊት ዕጣ ፈንታችን የጋራ ተስፋና ምኞት እንዲኖራቸው የሚያደርግ በመሆኑ። አራተኛው ብዙ አብረን የማናከብራቸው በዓላት በብዛት ቢሆኑም ይህ የጋራ ክብረ በዓላችን መሆኑ ትልቅና የተለየ ያደርገዋል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- አዲስ ዘመን ሲመጣ መልካም ምኞት የምንገልጽበት መሆኑ ይታወቃል፤ መጭውን ተስፋ በማሰብ እቅድም የምንይዝበት ጊዜ ነው። በዚህ ላይ የእርስዎ እይታ ምንድን ነው?**

**አባ ገብረሃና፡-** እንደ ግልም እንደ ሃይማኖትም እቅዶች ይኖራሉ። በዋናነት በኃይማኖት እሳቤ ውስጥ በቡድንም ይሁን በግል እቅድ ስናወጣ በደል፣ ኃጢያት፣ ክፉት ያለበትን ሕይወት ማስወገድ ነው። በአዲስ ዘመን ንስሐ ያልገባ ወደ ንስሐ ሕይወት እንዲገባ፣ የበደለው እንዲክስ፤ የቀማው እንዲመልስ፤ የተቸገረው እንዲገኝ ስለዚህ ከልብ የሆነ መጸጸት ይፈልጋል። ይህን ስናደርግ እቅዶቻችን የሰመሩ እና የተስተካከሉ ይሆናሉ፡፡

እንደማንኛውም ማኅበረሰብ ለሚያምነውም ለማያምነውም ግን ያለፈውን ነገር በሀቀኝነት መገምገም አለበት። ምን አቅም ኖሮኝ ነው ምን ያቀድኩት፤ የእኔ አቅም ምንድን ነው? የምችለው ነገር ምንድን ነው? የማልችላቸው ነገሮችስ ምንድን ናቸው? የሚሉት መመለስ አለባቸው። በአጠቃላይ ሰዎች በእውነተኛ ማንነታቸው ላይ ተመስርተው እቅድ ማወጣት አለባቸው።

**አዲስ ዘመን፡- በኢትዮጵያ የተለያዩ እምነቶች ቢኖሩም ሁሉም እንደየእምነቱ የራሱን ይዞና የሌሎችንም አክብሮ የመሄድ ባህሉ ከፍተኛ ነው፤ ከዚህ አንጻር የሀገራችንን የመቻቻልና የመተሳሰብ ባህል እንዴት ይገልፁታል?**

**አባ ገብረሃና፡-** ይህ እንደሰዎች አስተሳሰብ የሚወሰን ነው።፡ በአመለካከት፣ በሃይማኖት እንዲሁም በአካል እንለያያለን። አንድ ያደረገን ነገር ቢኖር የመሥሪያ ቤቱ ሕግና ሥርዓት ብቻ ነው። በግድም ቢሆን አንድ የሚያደርገን የተቋሙ ዓላማና ራዕይ ነው። ይህ ደግሞ በማህበረሰባችንም ውስጥ እንዲሁ ነው ያለው። ማህበረሰቡን አንድ የሚያደርገው የጋራ የሆነ እሳቤ አለው። የጋራ ህልምና የጋራ ራዕይ አለው። እነዚህ ከሌሉ ሀገር ሊኖር አይችልም። የጋራ ማንነት ከሌለ አንድ የሚያደርገን እሴት የለም ማለት ነው። ስለዚህም አንድ ያልሆነ ቤተሰብ እንደሌለ ሁሉ አንድ ያልሆነ ሀገር ሊኖር አይችልም። እናም ሀገር የምትኖረው በጋራ መሰረቶች ላይ ተመስርታ ነው።

መቻቻል በሀገር እሳቤ ውስጥ ትክክል አይመስለኝም። ምክንያቱም ቅራኔን ይዞ አንድነትን፣ ፍቅርንና ተስፋን ማምጣት አይቻልም። ስለዚህም የቋንቋው አገባብ የተለየ መሆን ይኖርበታል። ምክንያቱም መቻቻል መባል ያለበት ከሀገርና ከማኅበረሰብ ውጭ ባለ ጉዳይ ነው። ለአብነት እንደ ኢትዮጵያ ስናስብ ክርስትና ለእስልምና ጠላትም ሥጋትም አይደለም። እንዲሁ እስልምናው ለክርስትናው ጠላቱም ሥጋቱም አይደለም። በውስጥ ተደብቆ ሌላ አላማ ይዞ የሚሰራ አካል ከሌለ በስተቀር። ፈጣሪን የሚያመልኩና ለእርሱ የሚገዙ እስከሆነ ድረስ አንዱ ለአንዱ የሕልውና ጉዳይ ናቸው። የአንዱ መኖር ለሌላው ተስፋና ሕይወት ነው። ስለዚህም በዚህ እሳቤ ውስጥ ካለን ደግሞ አንዱ አንዱን ይንከባከባል እንጂ አያጠቃውም። ስለሆነም መቻቻል ሳይሆን መደጋገፍና ነገን ማሳመር ነው።

**አዲስ ዘመን፡- መቻቻልን የሚለው ትርጓሜ ስህተት አለበት ብለው ያምናሉ፤ ቋንቋውን እርስዎ እንዴት ያዩታል?**

**አባ ገብረሃና፡-** አዎ። የቋንቋ ትርጉም ልዩነቶች የሚከሰቱት የምንጠቀምበትና የማንጠቀምበትን አውድ መለየት ሳንችል ስንቀር ነው። አብሮ ለመኖር፤ ለመግባባት፣ ለአንድነት መጠቀም ያለብን መቻል የሚባለው ቃል ሳይሆን ከዚህ የተሻሉ ህብረትን የሚፈጥሩ ቃላት አሉ። ምክንያቱም መቻቻል ማለት በደልና ቅራኔን በውስጡ ያዘለ ነው። እስከመቼ የሚለውንም ያመጣል። የጊዜ ገደብን በውስጡ የያዘም ነው። የሚበድለኝን ሰው ልሸከመውና ዛሬን ልለፈው እንደ ማለትም ነው። ይህ ደግሞ አብሮ በሚኖር ሰዎች መካከል የሚሆን አይደለም። የአንዱ መኖር ለሌላው ሕልውናም እድገትም ነውና በምክንያታዊነት ይራመዳል እንጂ መቻል የሚለውን ነገር አያስገባም።

**አዲስ ዘመን፡- አዲስ ዓመት ብቻ ሳይሆን ሌሎች ባህላዊና ታሪካዊ እንዲሁም ኃይማኖታዊ በዓላት አሉ። እነዚህ ዓመታዊ በዓላት በትውልድ ቀረጻ ላይ የሚኖራቸው አንድምታ እንዴት ይብራራል? ይህ እንዲቀጥልስ ምን መደረግ አለበት ይላሉ ?**

**አባ ገብረሃና፡-** በዓላት ምንም ዓይነት መልክ ቢኖራቸውም በትውልድ ቀረጻ ላይ ትልቅ አቅም ፈጥረው የሚጓዙ ናቸው። ምክንያቱም እነርሱ የነበረውን ትናንት በስሜትም በኑሮም የሚያሳዩ ናቸው። ትናንትን ከእነሙሉ ክብሩ የሚያስረክቡ ናቸው። እነርሱ ላይ ስንሆን ግን ቅድሚያ ማህበረሰብ የሚለው ይጎላል። ሕብረት ይጎላል። በብዛት ጥልቅ ፍቅር እንጂ ጥላቻ አይስተናገድም። በሰላም መለያየት እንጂ መከፋፋት አይታይበትም። ድብድብ እንኳን ኖሮ «አይቆጡም ጌታ» ተብሎ ነው የሚታለፈው። ስለዚህም ለሰላምና ለጸጥታው፤ ለአንድነትና ለአብሮነት የሚሰጠው ግምት ከፍ ያለ ነውና ትውልዱ ያንን እያወቀ ማደጉ ደግሞ ሁሌም ሰላማዊና ሰውን አፍቃሪ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

ትውልድ የሚቀረጸው በባህልና በታሪክ ውስጥ ነው። ከሌላ ሳይሆን ከእምነቱ፣ ከባህሉ የሚመነጨውን ተቀበል ሲባልም ነው በቀላሉ ወደመተግበሩ የሚገባው። ይህም ቢሆን ጥንቃቄን ይፈልጋል። በተሳሳቱ ትርክቶች ከሞላነው ጥላቻን አንግቦ የማይሆን ሕይወት ውስጥ ይገባል። ስለዚህም እምነት እና ባህል ውስጥ ያለውን እምቅ ጥበብ በእውነቱ ልናስረዳው ይገባል። የማያግባቡን ትርክቶችን እንደእውነት እያደረግን መንገርን ከአሁኑ ልናስወግድ ይገባል።

**አዲስ ዘመን፡- ለኢትዮጵያውያንና ለመላው የዓለም ሕዝብ አዲሱን ዓመት መሠረት በማድረግ የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ ቢገልጹልን?**

**አባ ገብረሃና፡-** የማይነጋ ሌሊት እንደሌለ ሁሉ የማያልፍ መከራም ሆነ ችግር የለም። በኢትዮጵያ ትልቅ ተስፋ አለ። መከራዎቿ ተስፋዎቿን ትልቅ ያደርጉታል። አሁን ብዙ መከራ ውስጥ ነን። ለመሪም ለሕዝብም ብዙ ያልተመቹ ነገሮች አሉ። ጦርነቱ፣ መፈናቀሉ፣ መሰደዱና መራቡ እንዳለ እየተገለጠ ነው። እነኚህ ችግሮች ግን ሊወለድ ላለው ትልቁ ተስፋ መሠረቶች ናቸው። ከዚህ መከራ ጀርባ ትልቅ እውነት፤ ትልቅ ስኬትና ድል ይኖራል ብዬ አስባለሁ። እንደ ግለሰብም ሀገርም ከዚያ ችግራቸው በኋላ ነው የሚቆሙትም የሚጸኑትም። ስለዚህ ግን ሥራዎች ይፈልጋሉ።

አንዱ ጎልተው የሚደመጡት ነገሮች በጎነትን፣ አብሮነትን፣ ኢትዮጵያዊ ማንነትን የያዙ መሆን ይኖርባቸዋል። ለልዩነት እስካሁን ደከምን ያፈራነው ነገር አሁን እያየነው ነው። እናም ከችግሮቻችን ለመዳን መፍትሔው ለአንድነት መድከም ነውና የዛሬው ሥራችን ይህ መሆን አለበት። ከሚለያየን ትርክት ይልቅ የሚያስተሳስበንና የሚያስተሳስረን አዲስ ትርክት እንፍጠርለት። ከመሪ እስከተመሪ ድረስ ያለው አካል በግለሰብ ማንነቱ ራሱን ይፈትሽ። ለለውጥ እንደሚተጋ እርግጠኛ ይሁን። ከዚያ ያንን ወደ ቡድን ያምጣው። ይህ ሲሆን ደግሞ ሀገርን መሥራት ይቻላል።

ለማጥፋት ካልሰራን ለበጎነት ከተጋን በጎ ነገር የማያስማማው ግለሰብ አይኖርም። እናም እንደሀገር ከትናንትናው ስብራቶቻችን፣ ውድቀቶቻችን ይበልጥ የሚመጣው ተስፋዎቻችን ላይ እንመርኮዝ። እነርሱ የአዲስ ዓመት አበባዎቻችን ናቸው። በቀጣይ ፍሬን የምንለቅምባቸው። በባለፉት መከራዎቻችን በዓመተ ፍዳ፣ በዓመተ ኩነኔ ውስጥ ከሆንን እድገትን ሳይሆን ውድቀትን ነውና የምንጠራው እርሱን ለአለፈው ዘመን እንተውለት። ማህበራዊ ፍልስፍናዎቻችን፣ ማህበራዊ ጥበባችን፣ እውነተኛ የኃይማኖት ማንነቶቻችን ላይ ተመርኩዘን በጎ በጎውን ብቻ ይዘን እንሻገር። በጸሎት ማንነት ከፈጣሪ ጋ ከተጋመድን ደግሞ ተስፋችን ቅርብ ይሆናልና እርሱን እናድርግ። መልካም አዲስ ዓመት።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ማብራሪያ ከልብ እናመሰግናለን።**

**አባ ገብረሃና፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# "በአዲስ ዓመት ሰዎች ስለራሳቸው ብቻ ሳይሆን ስለሀገራቸውም ማቀድ አለባቸው"

- አቶ ጌታ ዋለልኝ
የሥነ ልቦና ባለሙያና
በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የሳይኮሎጂ መምህር

እፀገነት አክሊሉ

እዮሃ አበባዬ.............መስከረም ጠባዬ

እዮሃ አበባዬ............. መስከረም ጠባዬ

መስከረም ሲጠባ........አደይ ሲፈነዳ

እንኳን ሰው ዘመዱን.........ይጠይቃል ባዳ ይባላል። ይህ ዜማ አሮጌው ዘመን በአዲሱ የመቀየሩን ብሥራት አብሣሪው ነው።

የአዲስ ዓመት (እንቁጣጣሽ) በዓል፤ በእኛ በኢትዮጵያዊያን ዘንድ ልዩ ሥፍራ ከሚሰጣቸው በዓላት ውስጥ አንዱና ዋነኛው ነው። የጨለማ ተምሳሌት የሆነው ጭጋጋማው የክረምት ወቅት አልፎ፣ ቀን ከሌሊት ይዘንብ የነበረው ዝናብና አስገምጋሚው መብረቅ ጋብ የሚልበት፣ ምድር በአደይ አበባ ተጥለቅልቃ በልምላሜ የምትታይበት፣ አሮጌው ዘመን ወደኋላ ተትቶ አዲሱ ሊተካ "እዮሃ አበባዬ" የሚባልበት በዓል በመሆኑ በብዙዎቻችን ዘንድ የተለየ ትርጓሜ ይሰጠዋል።

የኢትዮጵያ አዲስ ዓመት ተፈጥሮም ጭምር የሚለወጥበት ነው። በመስከረም ወር አዝመራው ያብባል፣ የደፈረሱ ወንዞች መጥራት ይጀምራሉ፣ አደይ አበባ ምድሪቱን ያለብሳታል ፣ የመስቀል ወፎች ከተደበቁበት ይወጣሉ። ለዚህም ነው አዲስ ዓመት የብሩህ ተስፋ መጀመሪያ ተደርጎ የሚታሰበው፡፡

ዓመቱ ለሀገራችን አዲስ ተስፋን የሰነቀ የሰላም፣ የፍቅር እና የዕድገት እንዲሆን ሁላችንም እንመኛለን። እርስ በእርሳችንም እንኳን አደረሳችሁ! ዘመኑ የሰላም፣ የፍቅር፣ የደስታና የሐሴት ይሁንልህ/ሽ እንባባላለን፤ ይህ በራሱ አዲሱን ዓመት በአዲስ ተስፋ እንድንቀበለው የሚያስገድድ ልዩ ስሜትን ይፈጥራል።

የ2016 ዓ.ም አዲስ ዓመትም ከምንጊዜውም በተለየ ሁኔታ የብሩህ ተስፋ ዘመን እንዲሆንልን የምንመኘው በ2015 ዓ.ም ያሳለፍናቸውን ፈተናዎች ተወጥተን ሰላም የሚሰፍንበትና ልማታችን ላይ የምናተኩርበት ዘመን እንዲሆንልን ካለን ጽኑ ፍላጎት በመነጨ ነው፡፡

በመጪው አዲስ ግጭትና ያለመረጋጋት እንዲወገድ፣ ከቀያቸው በጦርነት ተፈናቅለው በየመጠለያው ያሉ ወገኖቻችን ወደየቤታቸው እንዲመለሱ፣ የወደሙ መሠረተ ልማቶች እንዲጠገኑ በአጠቃላይ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሕይወታችን እንዲታደስ ጠንክረን የምንሰራበት ዘመን ሊሆንም ይገባል፡፡

ኢትዮጵያ ከሌሎች የዓለም ሀገራት በተለየ የራሷ የዘመን ስሌትና ቀመር ያላት ሀገር ናት። ብቸኛዋ የአስራ ሦስት ወር ፀጋ ባለቤትም መሆኗ ይታወቃል። ታዲያ አስራ ሦስተኛው የጳጉሜን ወር አብቅታ የአዲሱ ዓመት መባቻ የሆነው የመስከረም ወር ሲዋጅ፣ ብዙዎቻችን አዳዲስ የሕይወት ዕቅዶችን ማውጣት ወይንም የጀመርነውን አጠናክረን በመቀጠል ውጤታማ ለመሆን እናስባለን። ዘመን ዕለቱን ጠብቆ ሲቀየር የእኛም የአስተሳሰብ፣ አመለካከትና አጠቃላይ የሕይወት ዘይቤና እሳቤ እንዲቀየርም እንተልማለን። መስከረም በራሱ ለሰዎች ተስፋን ይዞ የሚመጣ ወር ነው ተብሎ በብዙዎች የመታመኑ ምስጢር ይኸው ነው።

እቅድ ሥራዎችን በየደረጃቸው እና በጊዜ አስቀምጠን እንድንሰራ የሚረዳን ትልቅ መሳሪያ ነው፤ ብዙ ሰዎች አዲሱን ዓመት የሚጀምሩት እቅድ በማቀድ ነው፤ ለምሳሌ በዚህ ዓመት ይሄን ያህል ገንዘብ እቆጥባለሁ፣ በዚህ ዓመት ትምህርት እጀምራለሁ፣ ወይም ደግሞ የግል ሥራ የምጀመርበት ዓመት ነው፤ አልያም ወደ ሀገሬ በአዲሱ ዓመት እመለሳለሁ ብለው የተለያዩ የግል እቅዶችን ያቅዳሉ፡፡

ታዲያ ይህ እቅድ ዓመት ገብቶ ዓመት በወጣ ቁጥር የሚወጣ ሊሆን አይገባም። ቢያንስ የእቅዱ ከግማሽ በላይ በተያዘለት ጊዜ መጠናቀቅ መቻል ይኖርበታል። ነገር ግን በዚህ ልክ አዲስ ዓመት ሲመጣ የያዝናቸውን እቅዶች ምን ያህሎቻችን ከግብ አድርሰናል የሚለው ለሁላችንም የሚቀርብ ጥያቄና መልሳችንንም ለራሳችን የምናደርገው ነው። ዕቅድን አቅዶ ውጤታማ አለመሆን በሕይወታችን ላይ አሉታዊ ተፅእኖዎችን ሊያመጣብን እንደሚችል ግን መገንዘብ በጣም አስፈላጊ ነው።



**በመጪው አዲስ ዓመት ግጭትና ያለመረጋጋት እንዲወገድ፣ ከቀያቸው በጦርነት ተፈናቅለው በየመጠለያው ያሉ ወገኖቻችን ወደየቤታቸው እንዲመለሱ፣ የወደሙ መሠረተ ልማቶች እንዲጠገኑ በአጠቃላይ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሕይወታችን እንዲታደስ ጠንክረን የምንሰራበት ዘመን ሊሆንም ይገባል**

በሌላ በኩልም አሁን ላይ በሀገራችን እየታዩ ያሉት ችግሮች ጊዜያዊ እንደሆኑና እኛ ኢትዮጵያውያን የሚያጋጥሙንን መከራና ችግሮች ማለፍ የምንችል ማኅበረሰቦች እንደሆንን በማመን ነገ የተሻለ ተስፋ እንዳለም መጠበቅ አንዱ የአዲስ ዓመት መገለጫው ሊሆን ይገባል።

ያሳለፍነው ክረምት በጣም ከባድና ተንቀሳቅሶ ለመሥራት በጣም አስቸጋሪ የሆነ ጊዜ ነበር። መስከረም ደግሞ በራሱ ከወራቶች ሁሉ ከፍተኛ ወጪ የሚወጣበት ወር ነው፣ ነገሮች እንደምናስባቸው ላይሳኩ ይችላሉ ወይንም ሰርተን የምናገኘው ገንዘብ የምፈልገውን ነገር አሁን ላይበቃ ይችላል። ነገር ግን፣ ነገ የተሻለ ሊሆን እንደሚችል በማሰብ ለዚህም ደግሞ ተስፋ ባለመቁረጥ ከሕይወት ጋር መታገል ግድ ነው። መጪው አዲስ ዓመትም የተሻለ ሰላም ሰፍኖ ሁሉም በተሰማራበት መስክ ላይ ጥሩ ሥራን ሰርቶ አቅዶ እቅዱንም ከግብ አድርሶ ሀገሩንም ራሱንም ተጠቃሚ ሊያደርግ ይችላል።

ተስፋ አለመቁረጥና ነገ የተሻለ ነገር ይመጣል ብሎ በሙሉ ልብ ማመንን ያቀድናቸውን እቅዶቻችንን ከግብ ለማድረስ ትልቅ አቅም ይሆኑናል።

እንደሀገር በአሁኑ ሰዓት የተለያዩ ጫናዎች ውስጥ እንገኛለን። ነገር ግን በአሁኑ ሰዓት መንግሥትና ሕዝባችን ያለውን አንድነት እና ጽኑ አቋም ስንመለከት፣ ሁሉንም ጫናዎች መቋቋምና አሸናፊዎች መሆን እንደሚቻል ያመላክታል። የምንሰማቸው ክፉ ዜናዎች በሙሉ ተወግደው ዕድገታችን የሚፋጠንበት ዘመን ይሆናል ። ነገ የተሻለ ነገር ለማምጣት ዛሬ ላይ እንደ ራሳችንም እንደ ሀገርም ትልልቅ እቅዶችን ማቀድ ለተፈጻሚነታቸውና ግባቸውን ለመምታታቸው ደግሞ ቆርጠን መነሳትን ይጠይቀናል። ነገሮች ወደ ሰላማዊ የመረጋጋት መስመር ውስጥ እንዲገቡ የሁላችንም ኃላፊነት ነውና ነገ የተሻለ እንደሚሆን ተስፋ እያደረግን ዛሬ ያለንን ነገር በአግባቡ እንጠቀም። በማለት እኛም አዲስ ዓመትና ተስፋው ብሎም ሰዎች አቅደው ስለመመራታቸው በተመለከተ በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የሥነልቦና መምህር ከሆኑት ከአቶ ጌታ ዋለልኝ ጋር ቆይታን አድርገናል።

**አዲስ ዘመን፡- አዲስ ዓመት ማለት ምን ማለት ነው?**

**አቶ ጌታ፡-** አዲስ ዘመን ማለት የጊዜ መለወጥ ማለት ሲሆን ይህ ጊዜ ሲለወጥ ደግሞ ብዙ ሰዎች ከጊዜው ጋር የመለወጥ ፍላጎትና ተነሳሽነትንም የሚያሳዩበት ነው። ማንኛውም ጤነኛ የሆነ ሰው ደግሞ ሁሌም በለውጥ ሂደት ላይ የሚሆን ከመሆኑም በላይ በተለይም ዘመን ሲቀየር ራሱን ከዘመኑ ጋር ለመቀየር በርካታ ተግባራትን ስለማድረጉም የሚያጠያይቅ አይሆንም።

ሁሌም ቢሆን ደስታችንም ሆነ የሕይወት እንቅስቃሴያችን የሚወሰነው በእድገት ላይ ነው። ይህንን ነገር ደግሞ የሚያስታውሰን አዲስ ዓመት ነው።

አዲስ ዓመት ሲለወጥ ደግሞ ሰዎች ራሳቸውን ከጊዜው መለወጥ ጋር ሕይወታቸውንም ለመለወጥ ተነሳሽነት የሚያድርባቸው ጊዜ ነውና ራሳቸውን የማደስና ሕይወታቸውን ለመለወጥ ተነሳሽነት ያድርባቸዋል። አዲስ አስተሳሰብም ይይዛሉ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- አዲስ ዓመት የመታደስ የመለወጥ አዲስ ውጥንን የመያዣ ጊዜ ከመሆኑ አንጻር አቀባበላችንስ ምን መምሰል አለበት?**

**አቶ ጌታ፡-** በነገራችን ላይ የነገሮች ወይም ደግሞ የዓመቱ መለወጥ ብቻውን ለእኛ መለወጥ ምክንያት ላይሆን ይችላል። ነገር ግን እኛም ራሳችን እንደ ዘመኑ ለመለወጥ ከነበርንበት ወደተሻለ ሁኔታ ለመቀየር በጠቅላላው ራሳችን ላይ ለመሥራት ፍቃደኛ መሆን ያስፈልጋል። በመሆኑም ዓመቱ ስለተለወጠ ብቻ አዲስ ሕይወት አዲስ ሀገርና ሁኔታ ይመጣል ማለት ባለመሆኑ ያንን ለውጥ ራሳችን ቆራጥ ሆነን ለማምጣት ዝግጁ መሆንና የሚጠበቅብንንም ሥራ ለመሥራት ፈቃደኛ መሆንን ይጠይቃል።

**አዲስ ዘመን፡-ራሳችንን ለመለወጥ ፍቃደኝነታችንን ከምናሳይበት መንገድ አንዱ እቅድ ማቀድ ይመስለኛልና በዚህ ላይ ምን ይላሉ?**

**አቶ ጌታ፡-** ከአዲስ ዓመት ጋር ተያይዞ ሕይወትን የተሻለ ሁኔታ ላይ ለማስቀመጥ ብዙ ሰው አቅዳለሁ ይላል ነገር ግን አብዛኞቻችን ያለን እቅድ ሳይሆን ፍላጎት ነው። ይህ ቢሆን ያንን ባሳካ ብለን ፍላጎት እናሳያለን እንጂ ጠንከር ያለ እቅድ ማውጣት ግብ መንደፍ ላይ ብዙዎቻችን አናስበውም ።

አዲስ ዓመት ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ እንዲህ ቢሆንልኝ፤ ይህንን ብሰራ፤ ወደዚህ ሀገር ብሄድ ወይንም ትምህርት ብጀምር ብቻ ብዙ ብዙ ነገሮችን እያስቀመጥን እንመኛለን ያ ምኞታችን የሚመስለን እቅድ ያቀድን ነው፤ ነገር ግን ይህ ሊሆንም ላይሆንም የሚችል ምኞት እንጂ እቅድ ሊባል አይችልም። እንደዚህ አስበን ብዙ ጊዜ

ወደ ገጽ 15 ዞሯል

# “በአዲስ ዓመት ሰዎች ስለራሳቸው ብቻ...

ከገጽ 11 የዞረ



**ማህበረሰቡም ቢሆን ሁሌም ቢሆን ለውጥ ከውጭ ሳይሆን ከራሳችን የምናመነጨውና ብዙ ለውጦችን ማምጣት የምንችል መሆኑን መገንዘብ ይገባል**

ላይሳካልን ከቻለ ደግሞ ተስፋ ማድረግን ትተን ወደጨለምተኝነት የምንመጣበት ሁኔታ ይፈጠራል።

ተስፋቢስነትን ተለማምደን ደግሞ ዓመት ቢቀየርም ምንም አዲስ ነገር አይኖርም፤ አይፈጠርም የምንልበት ሁኔታም ይመጣል። ከዚህ አንጻር ሰዎች ሙሉ በሙሉ ተስፋቢስ ሆነው አልያም በተስፋ ተሞልተው ዓመቱን ሊጀምሩት ይችላሉ።

እዚህ ላይ ልብ ልንል የሚገባን ነገር ለእኛ እቅድ የመሰሉን ምኞቶቻችንን ለማሳካትም ቢሆን ግብ መንደፍ በጣም አስፈላጊ ነው። በተለይም እቅድና ግብ እንዲኖረን ብዙ መማር ማንበብና ሁኔታውን በአግባቡ መረዳት የግድ የሚያስፈልግ ነገር ነው።

**አዲስ ዘመን፦ ምኞትን ወይም ፍላጎትን እንዴት ነው ወደ ዕቅድ መቀየር የምንችለው ?**

**አቶ ጌታ፦** ከላይ እንዳልኩት ብዙዎቻችንን እቅድና ግብ የለንም ከዛ ይልቅ ፍላጎትና ተስፋ ነው ያለን፤ ነገር ግን ግብ ነድፎ ተንቀሳቅሶ ውጤታማ መሆን በደንብ ይቻላል። ለዚህም ሃሳብን ሕልምን በጽሑፍ መያዝ በጣም አስፈላጊ ነው። እንደ አባባልም “በቃል ያለ ይረሳል በጽሑፍ ያለ ይወረሳል” እንደሚባለው ሁላችንም ዘመን ሲቀየር ማድረግ የምንፈልገውን መሆን የምንሻውን መድረስ ያለብንን ቦታ በሃሳብ ከመያዝ ወይም በቃል ከማውራት በጽሑፍ ግብ አድርጎ ማስቀመጡ ወደፊት ለመፈንጠር ዓይነተኛ መንገድ ነው።

መጀመሪያም ቢሆን እቅድን እቅድ የሚያሰኘው በጽሑፍ መስፈሩ ሲሆን ሌላው ውስን ግልጽና የሚለካ መሆኑ ይኖርበታል። ለምሳሌ በዓመቱ መጨረሻ ላይ ምንድን ነው አሳክቼ ማየት የምፈልገው? የሚለው ነገር በግልጽ መቀመጥ ያለበት ከመሆኑም በላይ በጊዜም የተወሰነ ሊሆን ይገባል፤ ተሳክቷል፤ አልተሳካም የሚለው ነገር ደግሞ ሊለካ የሚችል ሊሆን ይገባል። እንዲሁም ተጨባጭነት ያለውም ሊሆን ይገባል። የሚሳካ ሊሆንም ይገባል በእነዚህ ሂደቶች ውስጥ ተቀምጦ ነው እንግዲህ መሄድ ያለበት።

በመቀጠልም ምን አቅጄ የትኛውን ግብ አስቀምጬ እየተንቀሳቀስኩ ነው የትኛውንስ ማሳካት እችላለሁ የሚለው ነገር ደግሞ በየጊዜው መገምገምና መታየት ያለበት ጉዳይ ነው። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች የድርጅት እቅድና ግብ ለማስቀመጥ እሱንም ለማሳካት ብዙ ላይቸገሩ ይችላሉ፤ ነገር ግን የራሳቸው የሆነን ግብ ለማሳካት በጣም ይቸገራሉ። በመሆኑም ራስን በደንብ ማየት መገምገም ያስፈልጋል። በዚህም ለግቡ አለመሳካት ትልቁ ችግር ምንድን ነው? በምንስ ነው ሊፈታ የሚችለው? የሚለውን ከራሳችን ጋር በየጊዜው መገማገሙ በጣም አስፈላጊ ነው።

በዚህ መልኩ ምን አቅደን የትኛውን ግብ አስቀምጠን የት ደረስን? የሚለውን በለካንና ራሳችንን በገመገምን ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ የባህርይ ለውጥ እንድናመጣም ያግዘናል። እኛ ተለወጥን ማለት ግባችንን አሳካን ነውና ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ግብ ብቻውን ውጤት አያመጣም። ስለዚህ ለእቅዳችን መሳካት ወይ ማቆም ያለብን አጉል ባህርይ አለ፤ አለበለዚያም መላመድ ያለበን አስፈላጊ ነገር አለ ማለት በመሆኑ ይህንን በአግባቡ ተረድቶ መሥራት በጣም አስፈላጊ ነው።

**አዲስ ዘመን፦ ሰዎች እንግዲህ ፍላጎትም እንበለው አቅድ አስቀምጠው እርስዎ እንዳሉትም ግብ ለማስቀመጥ ጥረት አድርገው ግን ደግሞ ስኬትን አይጎናጽፉም የዚህ ዋናው ምክንያት ምንድነው ይላሉ?**

**አቶ ጌታ ፦** አዎ ሰዎች ግብ አስቀምጠው ውጤት ሊርቃቸው ይችላል ምክንያቱ ደግሞ መጀመሪያም ቢሆን ያስቀመጡት ግብ የሚገዳደራቸው አልነበረም ማለት ነው። ስለዚህ ምን ጊዜም የምናስቀምጠው ግብ ሊገዳደረን የሚችል ሊሆን ይገባል።

የማይሳካ ከባድ ወይም ደግሞ በጣም ቀላል ግብ ካስቀመጥን ለማሳካት አነሳሽ ነገር አይኖረውም። ነገር ግን ከዚህ በተቃራኒው የሚገዳደረን (የእኛን ጥረትና ትግል) የሚጠይቅ ሲሆን ግን ውጤታማነቱም የተሻለ ይሆናል። በሌላ በኩል ደግሞ ግባችን ላለመሳካቱ ከእኛ ቁጥጥር ውጭ የሆነ ኃይል ስላለም መሆኑን መርሳት አይገባም። ለምሳሌ አንድ ሰው ይህንን ይህንን አደርጋለሁ በማለት ግብ አስቀምጦ ነገር ግን የሀገራችን የማህበረሰቡ ሁኔታ ግቡን እንዳይመታ ተግዳሮት የሚሆንበት አጋጣሚ ብዙ በመሆኑ እነዚህን ነገሮች በሙሉ አስቦ ግብ ማስቀመጥ በጣም አስፈላጊ ነው።

እዚህ ላይ በጣም በትኩረት መታየት ያለበት ነገር እኛ ራሳችን ግባችንን ከዳር ለማድረስ ምን ያህል ቆራጦች ነን ? የሚለውን መፈተሽ ያስፈልጋል። ምክንያቱም አንዳንድ ጊዜ ለሁሉም ችግሮቻችን ውጫዊ ምክንያቶችን እየፈለግን በሄድን መጠን የእኛን ኃላፊነትም መርሳት ያመጣልና ቆም ብሎ እኔ ምን እየሰራሁ ነው? የሚጠበቅብኝን አድርጌያለሁ ወይ ለምንድን ነው ግቤ ያልተሳካው የሚለውን መመርመር ያስፈልጋል።

የዘንድሮው ግብ ካልተሳካ በሚቀጥለው ዓመት እንዴት ግብ ማስቀመጥ እንዳለበን፣ ምን ዓይነት ትምህርት መቅሰም እንዳለብን ሁሉ መማሪያ ይሆነናል። ሕይወት አንዴ አልተሳካም ማለት ሁሉም ነገር አበቃ አለቀ ማለት ካለመሆኑም በላይ በሚቀጥለው ዓመት ደግሞ ሌላ እድል ስለሚሰጥ የአሁኑን ባለበት አቁሞ ትምህርት ወስዶ ለቀጣዩ መዘጋጀት ብልህነት መሆኑን መረዳትም አስፈላጊ ነው።

ግን ሰዎች አቅደው ግብ አስቀምጠው ነገር ግን ሕይወታቸው ለምን ስኬትን ያጣል ካልን መልሶቹ የራስ ቁርጠኝነትና ተገዳዳሪ ግብን ያለማስቀመጥ ጉዳይ ናቸው።

**አዲስ ዘመን፦ ይህንን ግብ ወደ ሀገር ብንቀይረው እንደው ሀገር አዲስ ዓመት ሲመጣ ምን ዓይነት ግብ ይዛ መነሳት አለባት ይላሉ?**

**አቶ ጌታ፦** ሀገር እንደ ግለሰብ ሁሉ ተስፋ ያስፈልጋታል፤ አሁን ላይ ግን ሰዎች ተስፋ ቢስነትን እየተለማመዱት ያለ ይመስላልና መጀመሪያ ሕዝቡ ውስጥ ያለውን “በዚህም ዓመት ምንም ለውጥ አይመጣም” የሚለውን ተስፋ ቢስነት መስበር ያስፈልጋል። በመሆኑም መጪውን አዲስ ዓመት ልዩ የሚያደርገው ምንድን ነው? የሚለውን መፈተሽ በጣም አስፈላጊ ነው። አዲሱን ዓመት ልዩ የሚያደርገው ነገር አለ ካልን ደግሞ በተጨባጭ ምን እንደሆነ ማስቀመጥም ተገቢና አስፈላጊ ነው።

ሰው ተስፋ ሲኖረው ኃይል ይኖረዋል፤ ኃይል ካለው ደግሞ ራቅ አድርጎ ያቅዳል። ነገር ግን በዚህ ዓመትም ምንም አዲስ ነገር የለም ከተባለ ሲጀመርም እቅድ ላይ አይገባም። በመሆኑም ሀገሬ ተስፋ አላት ብለን ከተነሳን ማቀድ እንጀምራለን። በመሆኑም መንግሥት ሕዝቡ ተስፋ እንዲኖረው አዲሱ ዓመት ከአሮጌው ዓመት የተለየና ተስፋ ሰጪ እንዲሆን ሊወስዳቸው ያሰባቸውን ርምጃዎች በቆራጥነት ማሳወቅ ይገባዋል። እንደ ሀገር በተቻለ መጠን ሕዝብ እምነትንና ተስፋን እንዲሰንቅ ማድረግ ያስፈልጋል።

ማህበረሰቡም ቢሆን ሁሌም ቢሆን ለውጥ ከውጭ ሳይሆን ከራሳችን የምናመነጨውና ብዙ ለውጦችን ማምጣት የምንችል መሆኑን መገንዘብ ይገባል።

ስለዚህም የግለሰብ ዕቅድ እንዲሳካ የሀገር ዕቅድ መሳካት ይገባዋል። አዲስ ዓመት ሲመጣም ሰዎችም ስለራሳቸው ብቻ ሳይሆን ስለሀገራቸውም ማቀድ ይጠበቅባቸዋል። ሀገር ሰላም እንድትሆን፤ ልማቷ እንዲፋጠን፤ አብሮነትና ወንድማማችነት እንዲዳብር ሁሉም የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማበርከት መዘጋጀት አለበት፡፡

**አዲስ ዘመን ፦ ሀገራችን ላይ እያጋጠሙን ያሉ የሰላም መደፍረስና ሌሎችም ችግሮች አሉብንና ህብረተሰቡ አሮጌውን ዓመት ሸኝቶ አዲሱን ዓመት ለመቀበል ምን ዓይነት የአእምሮ ዝግጅት ማድረግ ይኖርበታል?**

**አቶ ጌታ፦** ችግሩ እያለ ችግሩን እንርሳው ወይም እንተወው ማለት አይቻልም፤ በተለይም እኛ ያሉብንን ችግሮች ሁሉ ረስተን አዲስ ዓመትን በአዲስ መንፈስ መቀበል የምንችልበት ቁመና ላይ እንገኛለን ብዬ አላስብም። ነገር ግን ችግሩን ለመፍታት እንደ ሕዝብ ያለን ቆራጥነት ምን ይመስላል? የሚለውን ማየት ግን ይቻላል። ይህንን ለማድረግ ደግሞ እንደ ማህበረሰብ ተስፋ ያስፈልግናል። በተለይም እኔ እንደግለሰብ የማደርገው ነገር ሀገሬ ላይ ለውጥ ያመጣል ብሎ ማሰብ በእጅጉ አስፈላጊ ነው።

እንደ ሕዝብ ብዙ ጫናና ችግሮች የተደራረቡብን ጊዜ ላይ ብንሆንም ዘመን ሲለወጥ ግን ማሰብ ያለብን ቀናውንና እስኪ በአዲሱ ዓመት ነገሮችን ላስተካክል ልፍታ ብለን ተነሳሽነት የሚያድርብን ሊሆን ይገባል፤ እኔ የምወረውራት አንዷት ጠጠር ወይም የምሰራት ትንሿ ሥራ ሀገሬ ላይ ለውጥ ለማምጣት አስተዋጽኦ አላት ብሎ ማመን ያስፈልጋል።

ይህንን ብለን ከተነሳን ደግሞ ማየት የምንፈልገው ለውጥ ይመጣል የሚል ሀሳብ አለኝ።

**አዲስ ዘመን፦ እንደ ባለሙያ ሀገርና ሕዝብ አዲሱን ዓመት እንዴት መቀበል አለባቸው ብለው ይመክራሉ?**

**አቶ ጌታ ፦** ሕዝቡ እኔ የማደርገው ነገር ከእኔ አልፎ ሀገሬ ላይ ትልቅ ለውጥ ያመጣል ብሎ የሚያስብበት፤ መንግሥት ኃላፊነቶቹን ለመወጣት ፍቃደኛ የሚሆንበት ዘመን ሊሆን ይገባዋል።

**አዲስ ዘመን ፦ ስለነበረን ቆይታ በጣም አመሰግናለሁ።**

**አቶ ጌታ ፦** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

# ለሀገራዊ የስንዴ ልማት ስኬት ዘላቂነት

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

ኢትዮጵያ በስንዴ ልማት ውጤታማ መሆኗን መንግሥት ሲገልጽ ቆይቷል፤ የስንዴ ልማቱ ሀገሪቱ ስንዴ ከውጭ ለማስገባት የምታወጣውን የውጭ ምንዛሬ ያዳነም ሆኗል። የሀገሪቱን የስንዴ ፍላጎት ከማሟላት አልፎ ሀገሪቱ በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ ስንዴ ለጎረቤት ሀገሮች ገበያ እንድታቀርብ አስችሏታል።

የስንዴ ልማቱ ስኬታማነት በተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት ጭምር የተመሰከረለት ስለመሆኑም መረጃዎች ያመለክታሉ። የአፍሪካ ልማት ባንክ የስንዴ ልማቱን በወቅቱ ከማድንቅም ባለፈው ለልማቱ ድጋፍ ማድረጉን መረጃዎች ይጠቁማሉ። የአሜሪካ የውጭ ግብርና ቢሮ ‹‹በኢትዮጵያ የስንዴ ምርት ትልቅ እመርታ እያሳየና ምርታማነቱ እየጨመረ ነው፤›› ሲልም ገልጾታል። ይህ የአሜሪካ ተቋም በሪፖርቱ ላይም ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ በ2022 እና 2023 ውስጥ 5 ነጥብ 7 ሚሊዮን ቶን ስንዴን ታመርታለች ብሎ መተንበዩንም መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

የስንዴ ልማቱ በተለይ በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ይበልጥ ተጠናክሮ የቀጠለ ሲሆን፣ የቆላ ስንዴ መስኖ ልማት በሚል መጀመሩም ይታወቃል። ይህ ልማት አሁን በሁሉም የአየር ንብረት አካባቢዎች በተለያዩ ክልሎች ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ (ዶ/ር) ለመጀመሪያ ጊዜ በየካቲት 2015 ዓ.ም የስንዴ ምርትን ወደ ውጭ የመላክ መርሃ ግብርን በኦሮሚያ ክልል ባሌ ዞን ይፋ በአደረጉበት ወቅት እንደተናገሩት፤ “ባሌ ላይ ያየነው ስንዴን ኤክስፖርት የማድረግ ሂደት ለኢትዮጵያ ማድረግ ከሚገባን ትንሹ ስኬት ነው። ምክንያቱም የምናደርገውንና የምናቅደውን በተግባር በአረንጓዴ ዐሻራና በሕዳሴ ግድብ እያሳየን መጥተናል። አሁን ደግሞ ስንዴን ከውጭ ማስገባት ከማቆም ባለፈ ስንዴን ወደ ውጭ በመላክ ያሰብነውን በተግባር ፈፅመን ለኢትዮጵያዊያንና ለዓለም አሳይተናል። ኢትዮጵያ ከስንዴ እርዳታ መላቀቅና ወደ ውጭ መላክ አትችልም ያሉንን ችለን በማሳየታችን ኩራት ተሰምቶናል” ብለዋል።

ለዚህ ስኬት ሁሉም ክልሎች ጉልህ አስተዋጽኦ ማበርከታቸውን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጠቅሰው፤ በተለይ የኦሮሚያ፣ የሶማሌ እና የአማራ ክልሎች በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ላይ ጠንካራ ሥራ ማከናወናቸውን አስታውቀዋል። በአፍሪካ ኢትዮጵያን ጨምሮ ከ250 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ እርዳታ ፈላጊ መሆኑን ጠቁመው፤ ይህ ችግር ይበልጥ በቁጭት ለልማት የሚያነሳሳና “ኢትዮጵያን ኤይድ” በሚል ስንዴ ለመለገስ ተግተን እንድንሠራ የሚያደርግ ነው ሲሉ አስረድተዋል። በዓለም ላይ የተፈጠረውን የስንዴ ገበያ ችግር ለማቃለልም ኢትዮጵያ የበኩሏን ድርሻ ትወጣለችም ሲሉ ተናግረዋል።

ይህ በስንዴ ልማት እየተመዘገበ ያለ ውጤትና እድገት ቀጣይነት እንዲኖረው ምን ማድረግ ያስፈልጋል? ስኬታማነቱስ ምን ያህል ዘላቂ ነው? የተገኘውን ስኬት አጠናክሮ ለማስቀጠል ምን ዓይነት እቅድ ተይዞ እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው?

በግብርና ሚኒስቴር የእርሻና ሆርቲካልቸር ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር መለስ መኮንን እንዳሉት፤ የመስኖ ስንዴ ልማት ከዛሬ አምስት ዓመት በፊት የተጀመረው በአንድ ክልል በሦስት ሄክታር መሬት ላይ ነበር። አሁን ግን ሥራው በየደረጃው ሰፍቷል። ልማቱም በሁሉም ክልሎች ሊባል በሚችል ሁኔታ ተስፋፍቷል። ሰፊ የእርሻ መሬት ላይ በማልማት እንዲሁም ተጠቃሚ አርሶ አደሮችን ጭምር በማብዛት በጥቅሉ ዘጠኝ ክልሎች ላይ መድረስም ተችሏል። በዚህ ደግሞ በ2013/14 የምርት ዘመን 1 ነጥብ 35 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በመስኖ ስንዴ ልማት ለመሸፈን ተችሏል። ከዚህም 53 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት ታቅዶ፤ በዓመቱ መጨረሻ ላይ 47 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ተገኝቷል።

ሀገሪቱ ምቹ የሆነ ሥነ-ምህዳር፣ መሬትና ታታሪ አርሶ አደር ያላት ብትሆንም ስንዴን ከውጭ በማስገባት ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ታወጣ ነበር ያሉት ሚኒስትሩ፣ አጠቃላይ የመስኖ ስንዴ ልማቱ እንደ ሀገር ሲጀመር የመጀመሪያው ግብ ከውጭ የሚገባውን ስንዴ ማስቀረት እንደሆነ ጠቁመው፤ ይህን ዕቅድ ለማሳካት ላለፉት ሦስት ዓመታት በተከናወነው ጠንካራ ሥራ በ2015 ዓ.ም ሙሉ ለሙሉ ከውጭ የሚገባውን ስንዴ ማስቀረት መቻሉን



> **በመኸር የእርሻ ሥራ ወደ 3 ነጥብ 6 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ ስንዴን ብቻ ለማልማት የታቀደ ሲሆን፤ እስካሁን ድረስ ባለው ሪፖርት ከ2 ነጥብ 9 ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት በዘር ተሸፍኗል። በቀጣይ ቀናት ከዚህ በላይ ማሳካት የሚቻልበት እድሎች አሉ። ይህ ደግሞ በስንዴ ልማት ምርት እንደሀገር ከታቀደው በላይ ስኬት ለማስመዝገብ ያስችላል**

ያነሳሉ። በዚህም እንደ ሀገር ለስንዴ ግዢ ይውል የነበረ ከአንድ ቢሊዮን ዶላር ያላነሰ ወጪ ማዳንና ይህንን ከፍተኛ ገንዘብ ለሌሎች ግልጋሎቶችና ልማቶች መጠቀም እንደተቻለም ያብራራሉ።

ዶክተር መለስ እንዳሉት፤ የስንዴ ልማቱ ስኬት በመስኖ ስንዴ ልማት ብቻ የመጣ አይደለም፤ በሌሎቹም የእርሻ ወቅቶችም በስንዴ ልማት በተሰራ ሥራም ጭምር ነው። በ2014/15 የምርት ዘመን በመስኖ፣ በበልግና በመኸር 4 ነጥብ 47 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በስንዴ ልማት ተሸፍኗል። በዚህም በሦስቱም ወቅቶች ከ154 ሚሊዮን ኩንታል ያላነሰ ስንዴ ማምረት ተችሏል። የተገኘውን ውጤት ይበልጥ ለማሳደግ በ2016 ዓ.ም በመኸር፤ በበልግና በመስኖ ስንዴ ልማት ሰፊ ሥራ እየተከናወነም እንደሆነ ገልጸዋል።

በመኸር የእርሻ ሥራ ወደ 3 ነጥብ 6 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ ስንዴን ብቻ ለማልማት የታቀደ ሲሆን፤ እስካሁን ድረስ ባለው ሪፖርት ከ2 ነጥብ 9 ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት በዘር ተሸፍኗል። በቀጣይ ቀናት ከዚህ በላይ ማሳካት የሚቻልበት እድሎች አሉ። ይህ ደግሞ በስንዴ ልማት ምርት እንደሀገር ከታቀደው በላይ ስኬት ለማስመዝገብ ያስችላል።

ለበርካታ ዓመታት ከአጠቃላይ በጀቷ ቀላል የማይባለውን መዋዕለ ነዋይ ከውጭ ስንዴ ለማስገባትና ለማጓጓዝ የምታውለው ኢትዮጵያ ካለፉት ሁለትና ሦስት ዓመታት ወዲህ ግዙፍ የሚባል የስንዴ ልማት ውስጥ ገብታለች። የተፈጥሮ የዝናብ ወቅትንና ኋላ ቀር የእርሻ ሥርዓትን ለዘመናት የሙጥኝ ብለው የሚያለሙ አርሶ አደሮቿን ከዚህ ልማድ ለማውጣትም ‹‹የበጋ ፤ የመስኖና የመኸር ስንዴ) በተሰኘ የልማት ፕሮግራምም እንዲያመርቱ እያለማመደች ትገኛለች የሚሉት ዶክተር መለስ፤ ይህንን ሥራ ለማጠናከር እንደ መንግሥት የዝናብ እጥረት በሚታይባቸው አካባቢዎች የውሃ ፓንፖችን፤ የመስኖ ውሃ አቅርቦትና መሠረተ ልማት ... ወዘተ መሰል ድጋፎችን በማድረግ ጭምር ሥራውን ማስፋቱን ተናግረዋል። በዚህ ደግሞ በዓይን የሚታይ የስንዴ ምርት ስኬት መመዝገቡን ያነሳሉ። በተገኘው ስኬት በአሁኑ ወቅት ከተለያዩ ዓለም አቀፍ አካላት ጭምር ዕውቅናንና አድንቆት እየተገኘ እንደሆነም ያብራራሉ፡፡

የፖለቲካል ምጣኔ ሀብት ተንታኝና ምሁሩ አቶ ሽዋፈራሁ ሽታሁን እንዳሉትም፣ የስንዴ ልማት ሀገሪቱ ካላት መልክአ ምድርና የሰው ኃይል አንጻር የተሻለ ምርት ማስገኘት የሚያስችል ነው። የስንዴ ፍጆታዋን በራሷ ምርት መሸፈን የምትችልበት ብዙ ዕድል አላት። ለዚህም ማሳያው በእነዚህ ሦስት ዓመታት በሠራችው ሥራ ምን ያህል ማምረት እንደቻለች የተመላከተው ነው በማለት የዶክተር መለስን ሀሳብ የሚያጠናክር ሀሳብ ይሰጣሉ።

በስንዴ ልማቱ ላይ በርካታ ማነቆዎች ስለመኖራቸው ሚኒስትር ዴኤታውም አረጋግጠዋል። በተመሳሳይ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም፣ የግብዓትና ፋይናንስ ተደራሽነት፣ የገበያ ሥርዓት ክፍተቶች፣ የምርምርና የኤክስቴንሽን አገልግሎት ውስንነቶች፣ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ፣ ኋላቀር የአመራረት ዘዴ፣ በተለይ አሁን ላይ አርሶ አደሩን እየፈተነ ያለው የአፈር ማዳበሪያ እጥረት፣ ድርቅ፣ በመኸር እና መስኖ ልማት ላይ እየተከሰተ ያለው የግሪሳ ወፍ ... ወዘተ የስንዴ ልማቱ ዋና ዋናዎቹ ችግሮች መሆናቸውን ያብራራሉ።

ኢትዮጵያ የሀገሯን ዜጋ ብቻ ሳይሆን የምትመግበው ጎረቤቶቿን ጭምር ነው። ጅቡቲ፤ ሱማሌ ላንድ፣ ኬንያ፣ ሱዳንና ኤርትራ በርካታ ምርቶችን ከኢትዮጵያ ይወስዳሉ የሚሉት ዶክተር መለስ፤ ሀገራቱ ምርቶችን ከሀገሪቱ በሕጋዊ መንገድ ብቻ ሳይሆን በአብዛኛው በሕገ ወጥ መልኩ እንደሚያገኙም ይገልጻሉ። ይህ ደግሞ የልማቱ ውጤት እንዳይታይ ከማድረጉም በላይ የተስተካከለ የግብይት ሥርዓት እንዳይኖር ማድረጉን ያነሳሉ።

በሌላ በኩል ሀገሪቱ ዝቅተኛ ቴክኖሎጂን የሚጠቀም፤ ከዝናብ ጥገኝነት ያልተላቀቀ አርሶ አደር ያለባት በመሆኗ ምርትና ምርታማነቱ በሚፈለገው መጠንና ፍጥነት ሊያድግ አልቻለም የሚሉት አቶ ሽዋፈራሁ፣ በመሆኑም ከራስ ፍጆታ ያለፈ ትርፍ ምርት በማምረት ለገበያ ከማቅረብ አኳያ የሚጠበቀውን መዋቅራዊ ሽግግር በሚፈለገው ደረጃ ለማምጣት ካለመቻሉም በላይ የሀገሪቷን የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ እንደማይቻልም ነው የተናገሩት።

እርሳቸው እንደሚሉት፤ አሁን ላይ በበጋም ሆነ በመኸር አለያም በመስኖ እየተመረተ ያለው ምርት ይበል ያሰኛል። ሆኖም እያንዳንዱ የምርት ሂደት ግን መፈተሽ ይኖርበታል። ከሚፈለገው አንፃር ምን የተገኘ ነገር አለ? ሀገሪቱ የሯሷን ፍጆታ ከመሸፈን ባለፈ ምን ያህል ምርት አምርታ ወደ ውጭ መላክ ትችላለች? አርሶ አደሩ ምን ያህል እሳቤውን ተቀብሎታልና አስርጾታል? የሚሉትና መሰል ጉዳዮች መልስ ማግኘት አለባቸው። በማንኛውም ጉዳይ ውስጥ የገበሬውን ድካም ማየት ይገባል።

ኢትዮጵያ ከሰሃራ በታች ካሉ የአፍሪካ ሀገሮች መካከል በስንዴ ምርቷ በቀዳሚነት ትታወቃለች። በዓመት ከ107 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የስንዴ ምርት ትሻለች። ይህንን ፍላጎት ለማሟላት ከውጭ ለምታስገባው ስንዴም ከ700 ሚሊዮን ዶላር እስከ አንድ ቢሊዮን ዶላር ታወጣም ነበር። እናም ይህንን እልባት ለመስጠት የስንዴ ልማት ላይ አተኩራ እየሠራች ትገኛለች። በዚህም የዜጎችን የስንዴ ፍላጎት ከማሟላት ባሻገር ከራሷ ፍጆታ የተረፉትን ለውጭ ገበያ እንደምታቀርብና ከውጭ መግዛትን እንደምታስቀር ይታመናል። ይህም ደግሞ ባለፉት ዓመታት የታየ ሀቅ ነው።

መረጃዎች እንዳሚያመለክቱት፤ ኢትዮጵያ በጀመረችው ሀገራዊ የስንዴ ልማት እ.ኤ.አ በ2020 በመስኖ ስንዴ ልማት ብቻ ይሸፈን የነበረው 117 ሺህ ሄክታር ነበር። ይህ አሃዝ አአአ በ2021 ወደ 672 ሺህ ሄክታር፣ እአአ በ2022 ደግሞ ወደ 1 ነጥብ 3 ሚሊዮን ሄክታር ከፍ ብሏል። በዚህም በየዓመቱ የሚገኘው ምርትም እየጨመረ መጥቷል። ለአብነት እአአ በ2022/23 የምርት ዘመን በመስኖ፣ በበልግና በመኸር የእርሻ ወቅቶች 4 ነጥብ 47 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በስንዴ በመሸፈን ከ154 ሚሊዮን ኩንታል ያላነሰ ምርት ተገኝቷል።

የስንዴ ምርት ዘርፍ ትልቅ እመርታ እያሳየና ምርታማነቱ እየጨመረ ነው። ይህንን እምርታ ለማስቀጠልም በዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮች መፈታት ይኖርባቸዋል። ችግሩንም ለመፍታት እንደ መንግሥት የተለያዩ ሥራዎች እየተከናወኑ መሆናቸውን ሚኒስትር ዴኤታው ገልጸው፤ ለእዚህም በኤክስቴንሽን ድጋፍ፣ የመስኖ ልማቱን አጠናክሮና አስፋፍቶ በማስቀጠል፣ በዘመናዊ መሣሪያ የታገዘ የእርሻ ሥርዓት እንዲሁም ሌሎች ግብዓቶች በማቅረብ በኩል የተከናወኑ ተግባሮችን በማሳያነት ይጠቅሳሉ።

በበጋና በክረምት የሚደረገውን የልማት እንቅስቃሴ ቀጣይነትና ዘላቂነት ለማረጋገጥ ምርጥ ዘሮች፣ ማዳበሪያና ሌሎች ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ካላቸው ነባራዊ የዋጋ መጨመር የተነሳ ለገበሬው በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርብበትና የሚፈልገውን ያህል ግብዓት የሚያገኝበት እድል መፈጠሩም ሌላው ድጋፍና የመፍትሔ አቅጣጫ ተደርጎ እንደሚወሰድ ይናገራሉ።

አቶ ሽዋፈራሁ በበኩላቸው እንደሚሉት፤ ልማቱን ዘላቂ ለማድረግ የመጀመሪያው መፍትሔ በሀገሪቱ ሰላምና መረጋጋትን መፍጠር ነው። አርሶ አደሩ እንደልቡ ተንቀሳቅሶ መሥራትና ግብዓቶችን ማግኘት እንዲችል ከሁሉም በላይ የሰላም ጉዳይ ዋጋ ሊሰጠው ያስፈልጋል፤ መንግሥት ሰላም መፍጠሩ ላይ ተግቶ ሊሠራ ይገባል።

የስንዴ ልማቱ ሥራ በዘመቻ የሚደረግና ለፖለቲካ ፍጆታ ሥራ የሚውል መሆን የለበትም ሲሉም ገልጸው፣ በዚህ አይነት መልኩ የሚሰራ ከሆነ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ መቀዝቀዙ አይቀርም ብለዋል። እናም ከዚያ ይልቅ አርሶ አደሩ ሊያበረታታ የሚችልበትን ሥራ ማከናወን ያስፈልጋል። አሳምኖ ወደ ተግባሩ እንዲገባ ማድረግ ይገባል። አምኖበት ከሠራ ደግሞ ተጠቃሚና ውጤታማ የማይሆንበት ምንም ምክንያት የለም። ከዚያ ለራሱ ገቢ (ጥቅም) ሲል ሥራውን ቀን ከሌት ጠንክሮ የማይሠራበት ምክንያት አይኖርም ሲሉ ያብራራሉ።

አርሶ አደሩ አስተማማኝ የእርሻ መሬት እንዲኖረው፣ ምርጥ ዘር እንዲቀርብለት፣ የምርት ሽያጭ ሰንሰለቱ ጤናማ እንዲሆንለትም መሥራት ይገባል የሚሉት ኢኮኖሚስቱ፤ አንዳንዴ በኢ-መደበኛ ግብይት ውስጥ ምርቱ ያልፍና መቃቃሮች ሊፈጠሩ እንደሚችሉም መታመን አለበት። ለዚህ ደግሞ መንግሥት ከደላላው አንስቶ የሀገሪቱን መውጫ ድንበሮች አጥብቆ መቆጣጠር ይጠበቅበታል ብለዋል። አርሶ አደሩ ትርፋማ ከሆነና ውጤቱን ከተገነዘበ ሀገርም ሆነች ሸማቹ ማኅበረሰብ በሁሉም መስክ ስኬታማ ይሆናሉ ብለዋል።

ዶክተር መለስ ስንዴን በስፋት የሚያመርቱት ሀገሮች (ዩክሬይንና ሩሲያ) ችግር ውስጥ በመሆናቸው ዓለም ላይ የስንዴ ምርት እጥረት ገጥሟል ሲሉ ጠቅሰው፣ በተለይ ከነዚህ ሀገሮች የስንዴ ምርት የሚያስገቡ ብዙ ሀገሮች ቀውስ ውስጥ መግባታቸውን ተናግረዋል። ኢትዮጵያ ይህን ዓለም አቀፍ ችግር መሻገር የቻለችው በስንዴ ላይ እየተሠራ ባለው ሥራና በተገኘው ውጤት እንደሆነ ያመለከቱት ሚኒስቴር ዴኤታው፤ ስንዴን የማልማቱ ጉዳይ የፖለቲካ ፍጆታ ሳይሆን የመኖርና ያለመኖር ጉዳይ እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል ብለዋል። ምክንያቱም አርሶ አደሩ ስንዴን በማምረቱ ሀገር ታወጣ የነበረውን ከፍተኛ የሆነ የውጭ ምንዛሪ ከማዳኑ ባለፈ ሀገርን ከተረጂነት ታሪክ ይታደጋል ሲሉ ጠቅሰው፣ ስለሆነም ልማቱን ፖለቲካ ማድረጉን ትቶ መሥራት ላይና፤ ለሥራው ጉልበት መሆን ላይ ሁሉም ዜጋ ሊያተኩር እንደሚገባ ያሳስባሉ።

ከትንታኔው መረዳት እንደሚቻለው፤ ሀገሪቱ በስንዴ ልማቱ ያገኘችውን ውጤት አጠናክራ ካስቀጠለች የምግብ ዋስትናዋን ከማረጋገጥ አልፋ፣ ስንዴን ለውጭ ገበያ በማቅረብ የውጭ ምንዛሬ ማግኘት ትችላለች። ስንዴ ከውጭ ለማስገባት የምታውለውን የውጭ ምንዛሬ ለሌላ የልማት ሥራ ማዋል ትችላለች። በተቃራኒው የስንዴ ልማቱን ዘላቂ ማድረግ ካልቻለች ደግሞ ብዛቱ እያደገ የመጣውን ሕዝቧን የምግብ ዋስትና ማረጋገጥና የዋጋ ንረትን መቆጣጠር ትቸገራለች።

# የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ሳይንስ እና ጥበብ

ዋስልኝ አየለ

እንቁጣጣሽ፤ ባህል ነው፣ ሃይማኖት ነው፣ ጥበብ ነው፣ ሳይንስ ነው ስንል የልጃ ገረዶችን ጨዋታ ጨምሮ ብዙ ባህላዊ ክዋኔዎቹ ማሳያ ይሆኑናል። ሃይማኖት ነው ስንል በተለይም በኦርቶዶክስ አማኞች ዘንድ ሃይማኖታዊ አከባበር ስላለው ነው። ጥበብ ነው ስንል ከግጥምና ዜማ ጀምሮ ብዙ ጥበባዊ ትውፊቶች ስላሉት ነው። ሳይንስ ነው ስንል የዘመን አቆጣጠራችን መነሻ ስለሆነና ሳይንሳዊ ቀመሮች ስላሉት ነው። ከፊዚክስና ሒሳብ ያልተናነሱ ቀመሮችንም በዚሁ ጽሑፍ እናያለን።

እንቁጣጣሽ ከሌሎች በዓላት ሁሉ ይለያል። ሌሎች በዓላት ሃይማኖታዊ ወይም ባህላዊ ይዘታቸው ይጎላል። ለምሳሌ መስቀል፣ ገና፣ ፋሲካ ብንል ሃይማኖታዊ ይዘታቸው ይበልጣል። ጥምቀት፣ አሸንዳ፣ አሸንድዬ፣ ሻደይ እና ሶለል ብንል መነሻቸው ሃይማኖታዊ ይሁን እንጂ ባህላዊ ይዘታቸው ጎልቶ ይታያል። በሌላ በኩል እንቁጣጣሽ የእነዚህ ሁሉ በዓላት ማስጀመሪያ ነው። ለምሳሌ የ2016 ዓ.ም መስቀል፣ የ2016 ዓ.ም ገና፣ ጥምቀት፣ አረፋ፣ መውሊድ፣ ፋሲካ፣ አሸንዳ… እያልን የምንጠራው እንቁጣጣሽ በቀየረው ዓመት ነው። እንቁጣጣሽ ብዙ ጥበብና ሳይንስ የያዘ በዓል ነው። ይህ ሳይንሳዊ ባህሪው ሃይማኖት ዘለል በዓል ያደርገዋል።

በብዙ ነገሮቻችን ሁሉ ‹‹የራሳችን የዘመን አቆጣጠር ያለን›› እያልን እንጠራለን። ኢትዮጵያ ልዩ የሚያደርጋትም ይሄው ነው። ‹‹የ13 ወር ፀጋ›› በሚል ትታወቃለች። ይሄ ደግሞ ከዓለም ለየት ያደርጋታል። ይሄ ሁሉ የሆነው በእንቁጣጣሽ ጥበብ እና ሳይንስ ነው። እንቁጣጣሽ ኢትዮጵያ ምን ያህል የመጠቁ ሊቃውንት እንደነበሯት ያሳያል። የእንቁጣጣሽ ጥበባዊና ሳይንሳዊ ቀመር ምስክራችን ነው። ብዙዎቻችን ልብ የማንላቸው (አንዳንዴም ሃይማኖታዊ እየመሰለን) ሳይንሳዊ ቀመሮች አሉት። እንቁጣጣሽን በተመለከተ የተለያዩ መጻሕፍት፣ መጽሔቶችና ሰነዶች የተለያዩ መረጃዎችን አስፍረዋል።

ለምሳሌ የሥነ ጽሑፍና የሥነ ከዋክብት ተመራማሪው መምህር አብነት ስሜ በ2008 ዓ.ም በአዲስ አድማስ ጋዜጣ ላይ የሚከተለውን ማብራሪያ ጽፈዋል።

‹‹የሀገራችን የባሕረ ሐሳብ ሊቃውንት የሚጠቀሙበት የጊዜ ስሌት እንደሚከተለው ነው።

1 ዕለት = 60 ኬክሮስ
1 ኬክሮስ = 60 ካልዒት
1 ካልዒት = 60 ሣልሲት
1 ሣልሲት = 60 ራብዒት
1 ራብዒት = 60 ኀምሲት
1 ኀምሲት = 60 ሳድሲት

በዚህ መሠረት አንድ ዓመት 365 ዕለት እና 15 ኬክሮስ ይባላል። 15 ኬክሮስ ሩብ ዕለት ወይም 6 ሰዓት ነው። በሌላ አገላለፅ 1 ኬክሮስ 24 ሰዓት ስለሆነ 15 ኬክሮስ 360 ደቂቃ ነው። 360 ደቂቃ ደግሞ 6 ሰዓት ነው።

365 ዕለት፣ 5 ሰዓት፣ 48 ደቂቃ እና 46 ሰከንድ የተባለው አንድ ዓመት በባሕረ ሐሳብ የጊዜ ክፍፍል 365 ዕለት፣ 14 ኬክሮስ፣ 30 ካልዒት፣ 11 ሣልሲት እና 30 ራብዒት ይሆናል። የ11 ደቂቃ እና 14 ሰከንድ ጉድለት የተባለው በባሕረ ሐሳብ ቅመራ መሠረት ጉድለቱ 29 ካልዒት፣ 48 ሣልሲት እና 30 ራብዒት ነው የሚሆነው። 5 ሰዓት፣ 48 ደቂቃ እና 46 ሰከንድ ሲጠጋጋ 6 ሰዓት እንደሚሆነው ሁሉ 14 ኬክሮስ፣ 30 ካልዒት፣ 11 ሣልሲት እና 30 ራብዒት ወደ 15 ኬክሮስ ይጠጋጋል።

የዓመቱ ዕለት እና ዝርዝሩ ከላይ እንደተቀመጠው ነው፤ ለልዩ ንጽጽር የተፈለገ ለየት ያለ ቀመር ግን ይታያል። ይኸ ቀመር አንድን ዓመት 365 ዕለት፣ 15 ኬክሮስ እና 6 ካልዒት ያደርገዋል።

በዚህ አካሔድ 15 ኬክሮስ ራሱ ተጠጋግቶ የተገኘ ሆኖ ሳለ እንደገና 6 ካልዒት ተጨምሯል። 6 ካልዒት 2 ደቂቃ እና 24 ሰከንድ ነው። ይህ በየዓመቱ በትርፍ የሚገኘው 6 ካልዒት በ600 ዓመት ውስጥ ተጠራቅሞ አንድ ዕለት ይሆናል። 6 x 600= 3600 ካልዒት= 60 ኬክሮስ= አንድ ዕለት። 2 ደቂቃ እና 24 ሰከንድም በ600 ሲበዛ 24 ሰዓት ወይም አንድ ዕለት ይሰጠናል። እንግዲህ በየዓመቱ በተጠጋጋ ተረፍ የሆነው 6 ሰዓት በ4 ዓመት ተጠራቅሞ 24 ሰዓት ወይም አንድ ዕለት አስገኝቶ ጳጉሜን በ4 ዓመት አንዴ 6 እንደሚያደርጋት ሁሉ የ6 ካልዒት ትርፍ በእርግጥ ካለ (የአለ ግን አይመስለኝም) በ600 ዓመት አንዴ ጳጉሜን 7 ትሆናለች››

ቀመራዊ አሰራሩ እንዲህ በቀላሉ የሚገባን አይመስለኝም። ከዚህ የምንረዳው አባቶች ምን ያህል ሊቅ እንደነበሩ ነው። እነዚህን ሽርፍራፊ ቁጥሮች ደማምረው ነው ጳጉሜን የፈጠሯት። ጳጉሜንም አምስት፣ ስድስት እና ሰባት ያደረጓት። የኢትዮጵያ ሊቃውንት ከፈረንጅ ምንም ነገር ሳይኮርጁ እንደሰሩት ማረጋገጫ ይሆናል።

በእንቁጣጣሽ በሚቀየረው ዘመን ዓመቱ የራሱ የሆነ መጠሪያ አለው። ዝርዝር ቀመራዊ አሰራር ቢኖረውም በአጭሩ እንግለጸው። ይሄውም ዓመታቱ ዘመነ ማቴዎስ፣ ዘመነ ማርቆስ፣ ዘመነ ሉቃስ እና ዘመነ ዮሐንስ እየተባሉ እንደሚጠሩ ነው። ዘመኑን ለማወቅ ዓመተ ኩነኔ (5500) እና ዓመተ ምሕረት (አሁን ያለንበትን ዓመት ማለት ነው) በመደመር የሚገኘውን ውጤት ለአራት እናካፍላለን። በዚህ ስሌት መሠረት ቀሪው አንድ ከሆነ ዘመኑ ማቴዎስ ይባላል። ቀሪው ሁለት ከሆነ ዘመነ ማርቆስ፣ ሦስት ከሆነ ዘመነ ሉቃስ እና ያለ ቀሪ ከተካፈለ ደግሞ ዘመነ ዮሐንስ ይባላል ማለት ነው። በዚህ ስሌት መሠረት ዛሬ የተቀበልነው አዲሱ ዓመት 2016 ዓ.ም ዘመነ ዮሐንስ ነው። ምክንያቱም 5500+ 2016 = 7516 ነው። 7516 ለአራት ሲካፈል ቀሪ የለውም።

እንቁጣጣሽ እንዲህ አይነት ሳይንሳዊ ቀመር ቢኖረውም ሃይማኖታዊ ይዘትም አለው። ለአራት የተካፈለበት ምክንያትም በአራቱ ወንጌላውያን (ማቲዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስ እና ዮሐንስ) ነው። ጥቅል መጠሪያው (በብዙዎች የሚጠራው) እንቁጣጣሽ በሚለው ቢሆንም ሌሎች መጠሪያዎችም አሉት። እነዚህ መጠሪያዎች ሃይማኖታዊና ትውፊታዊ ናቸው። እንቁጣጣሽ ከሚለው ጀምረን እንያቸው።

ኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ሳባ የጠቢቡ ሰሎሞንን ዝና ሰምታ ኢየሩሳሌም ተጉዛ ስትመለስ ‹‹እንቁ ለጣትሽ›› በማለት ከእንቁ የተሠራ የጣት ቀለበት ንጉሥ ሰሎሞን እጅ መንሻ እንዲሆናት አበረከተላት። ይህን ታሪክ መነሻ አድርገው ‹‹እንቁጣጣሽ›› የሚለው ስያሜ ከዚያ እንደመጣ የታሪክ ድርሳናት ያስረዱናል፤ አንዳንዶችም አፈ ታሪክ ይሉታል።


በኢትዮጵያ የዘመን መለወጫ ዕለት ምድሪቱ በክረምቱ ዝናብ ውሃ እና ጭቃ ሆና የቆየችው ጭቃና ጎርፉ ተወግዶ በአረንጓዴ እጽዋት ተውባ ሜዳው፣ ሸለቆውና ተራራው በአደይ አበባ ተንቆጥቁጠው የሚታዩበት ወቅት በመሆኑ ዕለቱ ‹‹እንቁጣጣሽ›› እንደተባለም ይነገራል።

ሌላኛው መጠሪያው ‹‹ዘመን መለወጫ›› የሚለው ነው። ይሄ ደግሞ ሳይንሳዊ ምክንያትን የሚከተል ይመስላል። ዘመን መለወጫ መስከረም ወር የሆነበት ምክንያት ብርሃንና ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት የዓመት ዑደታቸውን በጳጉሜ ወር ጨርሰው በመስከረም ወር ስለሚጀምሩ ነው የሚሉም አሉ። ሌሊቱ ከቀኑ ጋር ይስተካከላል። የዓመቱ ቀናት 364 እና 365 (የጳጉሜን 5 እና 6 መሆን ተከትሎ) እየተባሉ የሚጠሩትም በዚህ አቆጣጠር ነው። በሃይማኖታዊ ምክንያት ደግሞ በኖህ ዘመን ተጥለቅልቆ የነበረው የጥፋት ውሃ የጎደለበት ወር ስለሆነ መስከረም የዘመን መለወጫ እንደተደረገ የሃይማኖት አባቶች ይናገራሉ።

ቅዱስ ዮሐንስ የሚል መጠሪያም አለው። ይሄኛው መጠሪያ ሙሉ በሙሉ ሃይማኖታዊ ነው። ቅዱስ ዮሐንስ የተባለውም የመጥምቁ ዮሐንስ ተግባር ለዘመነ ወንጌል መነሻ በመሆኑ ነው።

በዚህም ምክንያት በድርሳነ ዮሐንስ (ከገጽ 1 እስከ 3) እንደተገለጸው የኢትዮጵያ አዲስ ዓመት መስከረም አንድ ቀን እንዲከበር አባቶች ወስነዋል። መጽሐፈ ስንክሳር ‹‹የመስከረም ወር የተባረከ ነው። እርሱም የግብጽና የኢትዮጵያ ዓመቶች መጀመሪያ ነው። የዚህ ወር ቀኑና ሌሊቱ እኩል 12 ሰዓት ነው። ከዚህ በኋላ ቀኑ እየጎደለ ይሄዳል›› ይላል።

ስለእንቁጣጣሽ ስሞችና ቀመሮች ይህን ካልን የዘመን አቆጣጠራችን ከሌሎች የዓለም ሀገራት ለምን እንደተለየ ደግሞ ሊቃውንት የሚነግሩንን እንመልከት። ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ‹‹ባሕረ ሐሳብ›› በሚል መጽሐፋቸው



የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ከምዕራባውያን የተለየበትን ምክንያት ሲገልጹ ‹‹ሮማውያን የሮም ከተማ የተቆረቆረችበትን ዘመን መነሻ አድርገው ይጠቀማሉ፤ ታላቁ እስክንድርም የገነነበት ዘመን መቁጠሪያቸው ሆኖ ነበር›› ይላሉ። የኢትዮጵያ ካህናትም ዘመነ እስክንድር በሚል ይጠቀሙበት እንደነበር መጻሕፍት ይመሰክራሉ።

ሶርያውያን የዘመን አቆጣጠራቸውን የሚለኩት በፀሐይ ቆጥረው የዓመቱን 365 ቀን ለስድስት አካፍለው ከሮማውያን በተዋሱት ጊዜ የዓመቱን መጀመሪያ አዲስ ዓመት ይሉታል። በኋላ የሰማዕታት መታሰቢያ እንዲሆን በ460 ዓመተ ዓለም ወደ መስከረም 1 ቀን ለወጡት። የሀገራችን ሊቃውንትም አዲስ ዓመታችን መስከረም አንድ ቀን እንዲሆን የወሰኑት ይኸንን በመከተል ነው። የዓመቱን መጀመሪያ በመስከረም ማድረግን ከሶርያውያንም ሆነ ከግብጾች ብናገኘውም ጀማሪው በ46 ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ይገዛ የነበረው ዩልዮስ ቄሣር ስለነበር የዩልዮስ ባሕረ ሐሳብ ይባላል።

ዩልዮስ ቄሣር በ46 ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ባወጣው የዘመን አቆጣጠር ሥርዓት መሠረት የዓመቱን 365 ቀናት ለስድስት ሰዓት አድርጎ ለአራቱ ወራት 30/30 ቀን ለአንዱ 28 ቀን በአራት ዓመት አንዴ 29 ቀናት፤ ለቀሩት ሰባት ወራት 31/31 ቀናት መድቦላቸው በ12 ቦታ ከፍሎታል። ለዚህም ነው በአውሮፓውያኑ አቆጣጠር ሁሉም ወሮች 30 ቀናት ያልሆኑት። በኢትዮጵያ አቆጣጠር ግን አሥራ ሁለቱም ወራት 30 ቀናት ይሆኑና ጳጉሜ የተለየች ትሆናለች።

አውሮፓውያኑ የሚጠቀሙበት ይህን አቆጣጠር መነሻ አድርገው ነው። የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ከአውሮፓውያን እንዴት እንደተለየ አሥራት ገብረማርያም ‹‹የዘመን አቆጣጠር›› በሚለው መጽሐፋቸው ሲገልጹ ‹‹ዲዮናስዮስ የተባለው የሮም መነኩሴ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ተወለደበት ዘመን በስሌት ለመድረስ የተከተለው መንገድ የታሪክ ክስተትን ነበር።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የኢየሱስ ክርስቶስን የልደት ዘመን ለመሰወን የታሪክ ክስተትን አልተከተለችም። ቤተ ክርስቲያናችን የተከተለችው ከክርስቶስ ልደት በፊት ያለውን 5500 ዘመንን ነው›› በማለት የልዩነቱን ምክንያት ይገልጻሉ።

የዘመን አቆጣጠር ልዩነት መነሻው የዚህ ክስተት መሆኑን አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ሲያረጋግጡ ‹‹ኢትዮጵያ ዘመነ ብሉይን እንዲህ አስከትላ 5500 ብላ ስትቆጥር ዘመነ ሐዲስ ልዩ ሆኖ ከማንም ቁጥር አይገጥምም። ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ከምስራቆቹም ከምዕራቦቹም ሁልጊዜ በሰባት ዓመት ታጎድላለች። ምክንያቱም ባለታሪኮችን ትታ ወንጌል ተርጓሚዎችን መነሻዋ ስላደረገች ነው›› ይላሉ። በዚህም ምክንያት የኢትዮጵያ እና የአውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር ልዩነት ሊኖረው ቻለ። ይሄ የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ከክርስቶስ ልደት በፊት ያለውን ጨምሮ የዓለምን መፈጠር ምክንያት አድርጎ የተቀመረ ወጥ አቆጣጠር እንጂ ነገሥታት በተቀያየሩ ቁጥር የሚቀያየር አይደለም።

ስለኢትዮጵያን የቀን አቆጣጠር ካወራን ስለጳጉሜን ማንሳት የግድ ነው። ከዘመን አቆጣጠር ስሌቷ በተጨማሪ ኢትዮጵያን ልዩ የምታደርጋት ይቺ የጳጉሜን ወር ነች። ይቺ ወር አምስት ወይንም ስድስት ቀን ናት። በአራት ዓመት አንዴ ስድስት ትሆናለች። በ600 ዓመት አንዴ ደግሞ ሰባት እንደምትሆን ሊቃውንት ይናገራሉ። ይቺ አሥር ቀን እንኳን ያልሞላች ‹‹ወር›› እየተባለች ትጠራለች። የቤት ኪራይ አይከፈልባትም፣ የወር ደመወዝ አይገኝባትም።

ጳጉሜን በገጠር አካባቢ ‹‹ቋግሜ›› እያሉ ይጠሯታል። በጽሑፍ ደግሞ ብዙ ቦታ ላይ ጳጉሜ ቢሆንም ‹‹ጳጉሜን›› እየተባለም ይጻፋል። ያም ሆነ ይህ ቃሉ አማርኛ ወይም ሌላ የሀገር ውስጥ ቋንቋ ሳይሆን የግሪክ ቃል ነው። ትርጉሙም፤ ቀሪ ዕለታት፣ ቅጥያ፣ ተጨማሪ…ማለት እንደሆነ ይነገራል።

የጳጉሜን ወር ብዙ ሃይማኖታዊና ትውፊታዊ ክዋኔዎች ይከወኑባታል። የጳጉሜን ውሃ ከሌሎች ወራት በተለየ ቅዱስ ነው ተብሎም ይታሰባል። በዚህም ምክንያት በተለይም በገጠር አካባቢ ሰዎች በማለዳ በመነሳት ሰውነታቸውን ይታጠባሉ። ጳጉሜን ሦስት ደግሞ ‹‹ሩፋኤል›› ይባላል። በዚህ ዕለት ዝናብ ከጣለ ዓመቱ የሰላምና የበረከት ይሆናል ተብሎ ይታመናል፡፡

ይህን ሁሉ ጥበብ የቀመሩልን እንግዲህ ሊቃውንት አባቶቻችን ናቸው። ሃይማኖታዊም ይሁን ሳይንሳዊ፣ ባህላዊም ይሁን ዘመናዊ ይህን የመቀመር ጥበባቸው የሥልጣኔ ጀማሪዎች እንደነበርን ማሳያ ነው።

የየትኛውንም ዓለም የዘመን አቆጣጠር ብንመለከት አንድን ክስተት መነሻ አድርጎ የተቀመረ ነው። ለዚያም ብዙ የዓለም ሀገሮች የሚጠቀሙት አንዲት ሀገር በቀመረችው ቀመር ነው። ኢትዮጵያ ግን ራሷ ቀምራ በራሷ የዘመን አቆጣጠር ትጠቀማለች። ‹‹የራሳችን የዘመን አቆጣጠር ያለን›› የሚባለው ለዚህ ነው።

**መልካም አዲስ ዓመት!**

ልዩ ዕትም

# እያደገ የመጣውን ገቢ የመሰብሰብ አቅም ለማጎልበት

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ ግብር የመክፈል ታሪክ ያላት ሀገር ብትሆንም በተለያዩ ምክንያቶች ኢኮኖሚዋ ከሚያመነጨው አንጻር ተመጣጣኝ የሆነ ገቢ መሰብሰብ ተስኗት የቆየ ስለመሆኑ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በሀገሪቱ ከፍተኛ ገቢ ተሰበሰበ በተባለባቸው ወቅቶች ሁሉ ተያይዞ የሚነሳውም ኢኮኖሚው ከሚያመነጨው ሀብት አኳያ ሲታይ የሚሰበሰበው ገቢ ዝቅተኛ መሆኑን ነው። ለዚህም የተለያዩ ምክንያቶች ሲጠቀሱ ቆይተዋል፤ ከእነዚህም መካከል የግብር ከፋዩና የገቢ ግብር ሰብሳቢው መሥሪያ ቤት በመግባባት፣ በታማኝነትና በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የግብር አከፋፈል ሥርዓት ማስፈን አለመቻላቸውን በቀዳሚነት መረጃዎቹ ይጠቀሳሉ።

ለሀገራዊ ገቢ ዕድገቱ ዓይነተኛ ድርሻ ያላቸው እነዚህ ሁለት አካላት በተለየ ቅርበትና በባለቤትነት ስሜት ካልተንቀሳቀሱ በስተቀር ሀገራዊ ገቢውን ማሳደግ እንደማይቻል ይገለጻል። ለዚህም የገቢ ግብር ሰብሳቢ ተቋም ሀገራዊ የታክስ አስተዳደር ሥርዓትን በመገንባት፤ ምቹ፤ ቀላልና ፍትሕዊ አገልግሎት በመስጠት፤ ግብርን በፍቃደኝነት የመክፈል ባህል እንዲዳብር የማድረግ ኃላፊነት ይኖርበታል። በተመሳሳይ የገቢ ዕድገቱን ለመጨመር ግብር ከፋዩ ግብር የመክፈል የውዴታ ግዴታ መሆኑን አምኖ በታማኝነትና በፈቃደኝነት የመክፈል ባህሉን ማሳደግ ለገቢ ዕድገት አይነተኛ ድርሻ እንዳለው ይታመናል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ሀገሪቷ ከምታመነጨው ኢኮኖሚ አንጻር የገቢ ዕድገቱ ገና ብዙ የሚቀረው ቢሆንም፣ የገቢ መጠን ከዓመት ዓመት እየተሻሻለ ስለመምጣቱ ከገቢ ሰብሳቢ መሥሪያ ቤቶች የሚወጡ መረጃዎች ያመላክታሉ። ከገቢ ሰብሳቢ መሥሪያ ቤቶች አንዱ የሆነው የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ በዋናነት ከሚያከናውናቸው ተግባራት መካከል ቀዳሚ ሥራው የላቀ ገቢ መሰብሰብ ሲሆን፤ ቢሮው የሚሰበስበው የገቢ መጠን ከዓመት ዓመት መሻሻል እየታየበት ስለመምጣቱ አስታወቋል። አያይዞም ከተማዋ ከምታመነጨው ኢኮኖሚ አንጻር ሲታይ ገቢ የመሰብሰብ አቅሙ ገና እንደሚቀረውም ጠቁሟል።

በገቢ ግብር አሰባሰብ ረገድ ቀሪ የቤት ሥራዎች ስለመኖራቸው የሚያምነው ቢሮው በተጠናቀቀው 2015 በጀት ዓመት የተሻለ ገቢ ሰብስቧል። ቢሮው እንዳስታወቀው፤ በበጀት ዓመቱ 100 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ አቅዶ ከዕቅድ በላይ 109 ቢሊዮን ብር ገቢ መሰብሰብ ችሏል። ይህም ባለፉት ዓመታት ከነበረው ገቢ ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ ለውጥና መሻሻል የታየበት ሆኗል።

የግብር ሥርዓት ውስጥ ያልገቡትን በሕጉ መሠረት ወደ ግብር ሥርዓቱ እንዲገቡ በማድረግና ወቅቱን ያላገናዘበ ግብር የሚከፍሉትንም ወቅታዊ እንዲሆኑ በማድረግ የገቢ መጠኑ በ2010 ዓ.ም ከነበረበት 37 ቢሊዮን ብር ገቢ ተነስቶ በተጠናቀቀው 2015 በጀት ዓመት 109 ቢሊዮን ብር መሰብሰብ ተችሏል። ከተደረገው ማሻሻያ በተጨማሪ የግብር ከፋዩ ቁጥር መጨመርም ለገቢው ማደግ ዓይነተኛ ድርሻ አለው ነው።

ከሀገር ውስጥ እንዲሁም ከወጪ ንግድ የቀረጥና ታክስ ገቢን የሚሰበስበው የገቢዎች ሚኒስቴር በበኩሉ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት የዕቅዱን 98 በመቶ ማሳካት እንደቻለ ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የተገኘው መረጃ ያመላክታል። ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከሀገር ውስጥ ከሚሰበሰብ ገቢ በበጀት ዓመቱ 266 ነጥብ 95 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ አቅዶ 264 ነጥብ 35 ቢሊዮን ብር ገቢ መሰብሰብ የቻለ ሲሆን፤ በዚህም የዕቅዱን 99 በመቶ ማሳካት ችሏል።

ከውጭ ንግድ ቀረጥና ታክስ እንዲሁ 183 ነጥብ 34 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ አቅዶ 177 ነጥብ 68 ቢሊዮን ብር ገቢ በመሰብሰብ ነው የዕቅዱን 96 ነጥብ ዘጠኝ ማሳካት የቻለው። ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የላቀ ገቢ ለመሰብሰብ ባደረገው ጥረት በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ከሀገር ውስጥ እና ከውጭ ንግድ ቀረጥና ታክስ አጠቃላይ 450 ነጥብ 29 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ አቅዶ 442 ነጥብ 03 ቢሊዮን ብር በመሰብሰብ 31 ነጥብ 28 በመቶ ዕድገት ማስመዝገብ መቻሉን ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የተገኘው መረጃ አመላክቷል።



**እንደ መንገድ ያሉ መሠረተ ልማቶችን ለመገንባት ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን ገቢ ለመሰብሰቡ ሥራ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል**

ገቢ የሀገር ሕልውናን በማረጋገጥ ሂደት ውስጥ ከፍተኛ ሚና እንዳለው የገለጹት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ ኃላፊ አቶ አደም ኑሪ፤ በበጀት ዓመቱ የተሻለ ገቢ መሰብሰብ የተቻለ ቢሆንም ከተማዋ ከምታመነጨው ኢኮኖሚ አንጻር ገና ብዙ መሥራት ይጠይቃል ይላሉ።

የዜጎችን የመልማት ፍላጎት ለማሟላት እንዲሁም ማህበረሰቡ በየጊዜው ለሚያነሳቸው የመሠረተ ልማት ጥያቄዎች በሙሉ ምላሽ መስጠት የሚቻለው ገቢን በአግባቡ መሰብሰብ ሲቻል ነው የሚሉት አቶ አደም፤ ለዚህም ግብር ከፋዩ ግብሩን በታማኝነትና በራስ ተነሳሽነት መክፈል እንዳለበትና ገቢ ሰብሳቢው መሥሪያ ቤትም ከግብር ከፋዩ ጋር ተቀራርቦ መሥራት እንዳለበት ነው የሚያስረዱት።

እሳቸው እንዳሉት፤ ግብርን በፈቃደኝነትና በታማኝነት ከመክፈል አንጻር በማህበረሰቡ ዘንድ ከጊዜ ወደ ጊዜ የመጡ ለውጦች ቢኖሩም ለውጡ የሚፈለገውን ያህል ነው ማለት አይቻልም። ይሁንና ዛሬም ሀገሪቱ ያልተሻገረቻቸው በርካታ ችግሮች ባሉበት ሁኔታ ግብር መክፈል እየተሻሻለ መጥቷል። ግብርን በታማኝነትና በራስ ተነሳሽነት የሚከፍሉ እንዳሉ ሁሉ ከግብር የሚሸሹ ሰዎች በርካቶች ናቸው። ይሁንና ግብር መክፈል «የውዴታ ግዴታዬ ነው» ብለው የሚያምኑ ግብር ከፋዮች በመኖራቸው ምክንያት ቢሮው የሚሰበስበው ገቢ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቷል።

ገቢው በተለያዩ ምክንያቶች እያደገ መምጣቱን የጠቆሙት አቶ አደም፤ ከምክንያቶቹ የግብር ከፋዩ ቁጥር መጨመር አንዱ መሆኑን አመልክተዋል፤ ጠንካራ ክትትልና ቅንጅታዊ አሰራርን ጨምሮ የቤት ግብርን ዋጋ ወቅታዊ ማድረግና የማይከፍሉ ሰዎችን ወደ ግብር ሥርዓቱ እንዲገቡ ማድረግ መቻሉ ለገቢው መጨመር ትልቅ ድርሻ እንዳለው አስረድተዋል። እሳቸው እንዳሉት፤ ሕጉ እያለ የፍትሕዊነት ችግር ያለባቸውን ጉዳዮች ማሻሻያ ማድረግ ተችሏል። የቤት ባለይዞታዎች ለመሥሪያም ሆነ ለመኖሪያ እንዲሁም ለኢንዱስትሪ ቦታ ከያዙ በሕጉ መሠረት ግብር እንዲገብሩ ተደርጓል።

በቀጣይም ገቢ እንዲጨምር የፍትሐዊነት ችግሮችን በመፍታት እንዲሁም ማሻሻያ የሚፈልጉና የገቢ መጠንን መጨመር የሚያስችሉ ጉዳዮችን በጥናት በመለየት ከተማዋ ከምታመነጨው ኢኮኖሚ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ገቢ ለመሰብሰብ እንደሚሠራ አመልክተዋል።

ሀገራዊ የገቢ መጠንን ማሳደግ የሀገር ሕልውናን ለማጽናትና የማህበረሰቡን ጥያቄዎች ለመመለስ ወሳኝ ስለመሆኑ በምጣኔ ሀብትና ተያያዥ ዘርፎች ላይ የሚሰሩ ባለሙያዎች ይገልጻሉ። ለዚህም መንግሥት የታክስ ፖሊሲን ከማሻሻል ጀምሮ የገቢ አሰባሰብ ሂደቱን ቀልጣፋ፣ ዘመናዊ፣ ከንክኪ የጸዳ ማድረግና ግንዛቤ በመፍጠር ግብር ከፋዩ አምኖበት በታማኝነት መክፈል የሚችልበትን ዕድል መፍጠር እንዳለበት ይናገራሉ።

የሕዝብ አስተዳደርና የፖሊሲ ባለሙያው ዶክተር ገመቹ አራርሳ በጨፌ ኦሮሚያ የመንግሥት በጀትና ንብረት ቁጥጥር የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ናቸው። እሳቸው እንደሚሉት፤ ለአንድ ሀገር ልማት፣ ለአገልግሎት አሰጣጥና ማንኛውም ሰላማዊ ሁኔታን ለማረጋገጥ መንግሥት ገቢ ሊኖረው ይገባል። ለዚህም ገቢ የሚያመነጭ ዜጋ ሁሉ ለመንግሥት ታክስ መክፈል መቻል አለበት። ምክንያቱም ማንኛውም ሰው ሀገሪቷ ያላትን አቅም ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ ሃብት ተጠቅሞ ሃብት የሚያፈራ በመሆኑና የታክስ ዋና መርሆም ያለው ለሌለው መስጠት በመሆኑ የአንድ ሀገር ሃብት ፍትሐዊ በሆነ መንገድ መከፋፈል ይኖርበታል።

የመንግሥት ተቀዳሚ ሥራ ግብር አሰባስቦ የልማት ሥራዎችን መሥራትና የሀገሪቷን ሰላምና ደህንነት መጠበቅ ሲሆን ማንኛውም ገቢ ያለው ሰው ደግሞ እንደ ገቢ መጠኑ ግብር ለሀገሩ መክፈል የዜግነት ግዴታው ነው። በሀገሪቱ ያለው የገቢ አሰባሰብ ሂደት ኋላ ቀርና የሚሰበሰበው ገቢም ዝቅተኛ መሆኑን ዶክተር ገመቹ ጠቅሰው፣ ማህበረሰቡ ካለው የልማት ፍላጎትና የመገልገል ጥያቄ አንጻር መንግሥት ያለው ሃብት በቂ አይደለም ብለዋል። ይህም የሀገሪቷ ኢኮኖሚ ከሚያመነጨው አቅም አንጻር የሚሰበሰበው ገቢ በቂ አለመሆኑን እንደሚያመለክት ይገልጻሉ።

ገቢያችን ኢኮኖሚያችንን መምሰል አለበት የሚሉት ዶክተር ገመቹ፤ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ የገቢ ግብር አሰባሰብ አይነቶች ስለመኖራቸው ጠቅሰው፣ በሀገር ደረጃ በተለይም በክልል ደረጃ ቀጥተኛ የታክስ አሰባሰብ ትልቁን ድርሻ መያዙን ነው ያመለከቱት። ይህም ለገቢ ዕድገቱ ዝቅተኛ መሆን ዋናው ምክንያት ነው ይላሉ። ገቢው እሴት የማይጨምርና ከፔሮል ላይ በቀጥታ ያለምንም ድካም የሚሰበሰብ እንደሆነ ገልጸው፣ የመንግሥት ትኩረት መሆን ያለበት ቀጥተኛ ባልሆነ የገቢ ግብር አሰባሰብ ላይ እንደሆነም ጠቁመዋል። ይህም ትላልቅ ከሆኑ ኢንቨስትመንትና የተለያዩ ቢዝነሶች ጋር የተያያዘ ታክስ መሆኑን ተናግረው፣ እዚህ ላይ ትኩረት አድርጎ በመሥራት ማሻሻል ያስፈልጋል ብለዋል።

ሌሎች ዜጎች በተለይም የንግዱ ማህበረሰብ ግብር መክፈል የዜግነት ግዴታና ክብር መሆኑን አምኖ መክፈል አለበት የሚሉት ዶክተር ገመቹ፤ ለዚህም የግንዛቤ ፈጠራ ሥራ በስፋት መሥራት እንዳለበት ነው የሚጠቅሱት። ከዚህ በተጨማሪም ታክስ የሚሰበሰብበት ሁኔታና የግብር ከፋዮች መረጃ የሚያዝበት አግባብ ዘመናዊ አለመሆኑ በራሱ ለገቢ ዕድገቱ መቀነስ ዓይነተኛ ምክንያት መሆኑን አመልክተው፣ የተጀመረው የኤሌክትሮኒክስ ክፍያ ሥርዓት ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ገልጸዋል።

የሕግ ክፍተቶች ያሉባቸው ጉዳዮች ስለመኖራቸውም ዶክተር ገመቹ ጠቅሰው፣ በዋናነት የቢዝነስ ታክስ አሰባሰብ ላይ ሰፊ ክፍተት ስለመኖሩና ከፍተኛ ገቢ የሚሰበሰበውም ከዚሁ በመሆኑ መንግሥት ትልቅ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ብለዋል። በቅድሚያ ግብር ከፋዮቹን መለየት፣ ማሳወቅና ማበረታታት እንደሚያስፈልግና አለፍ ሲልም አስፈላጊውን ርምጃ በመውሰድ ተገቢውን ግብር መክፈል እንዲችሉ ማድረግ እንዲሁም መቆጣጠር ከመንግሥት እንደሚጠበቅ አስታውቀዋል።

ሌላው ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉና በምጣኔ ሀብት ጉዳዮች ላይ ጥናታዊ ሥራዎችን በመሥራት የሚታወቁ የምጣኔ ሃብት ባለሙያ፤ የሀገሪቱን የገቢ አሰባሰብና የገቢ መጠን አስመልክተው በሰጡት ሃሳብ ኢትዮጵያ ከምታመርተው የምታገኘው ሀገራዊ ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢ ዕድገት እያሳየ እንዳልሆነ ይገልጻሉ። ባለሙያው ከሀገሪቷ ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢ 20 በመቶው የመሰብሰብ አቅም ቢኖረውም ዘጠኝ ነጥብ ስድስት በመቶ ያህሉ ብቻ እየተሰበሰበ እንደሆነ ነው ያስረዱት። ይህም ማለት ሀገሪቷ አመርታለሁ ከምትለው ዓመታዊ ሀገራዊ ምርት አንጻር አሁን ያለው ገቢ እየቀነሰ መሆኑን የዓለም ባንክ ዳታን ዋቢ በማድረግ ያስረዳሉ።

የገቢ ምጣኔ ዕድገት የሚለካው ከዓመት ዓመት በሚመዘገብ የቁጥር ለውጥ አለመሆኑን ያነሱት የምጣኔ ሃብት ባለሙያው፤ የገቢ ምጣኔ ዕድገት መለካት ያለበት ከሀገሪቷ አጠቃላይ ገቢ አንጻር እየተሰበሰበ ያለው ገቢ እየጨመረ ሲመጣ ነው ይላሉ። በዚህ ረገድ ሲታይ ደግሞ ገቢው እየጨመረ አለመሆኑን ነው ያስረዱት።

ገቢው እንዲጨምር ምን መደረግ አለበት ችግሩ ምንድነው ስንል ላነሳነው ጥያቄም የምጣኔ ሃብት ባለሙያው ሲመልሱ፤ በርካታ ቴክኒካል ጉዳዮች እንዳሉ ነው የገለጹት። እሳቸው እንዳሉት፤ በዋናነት የታክስ ፖሊሲውን በየጊዜው መፈተሽና ጠንካራና ደካማ ጎኑን በመለየት ጠንካራ ፖሊሲ ማውጣት አንደኛው ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በፖሊሲ የተቀመጠውን በጠንካራ አስተዳደር ማስፈጸም ነው። እነዚህ ሁለቱ ቁልፍ ጉዳዮች ሀገራዊ የምጣኔ ሃብት ገቢውን ለማሳደግ ወሳኝ ናቸው።

ለአብነትም የውጭ ኩባንያ በዓመት ውስጥ አምርቶ ለገበያ ያቀረበው ምርት ትርፍ አላስገኘልኝም፣ ኪሳራ ውስጥ ገብቻለሁ ካለ ኪሳራውን ለማካካስ በቀጣይ ዓመት ታክስ የማይከፍልበት ሕግ ስለመኖሩ ተናግረዋል። ይህም ለታክስ ገቢው መቀነስ አይነተኛ ድርሻ እንዳለው ነው የምጣኔ ሃብት ባለሙያው ያመለከቱት።

የኢትዮጵያ መንግሥት የኢንቨስትመንት ማበረታቻ በማለት ከፍተኛ ታክስ እያጣ ስለመሆኑን የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ይናገራሉ። በተጨማሪም ድርጅቶቹ ከውጭ ዕቃ ሲያስገቡ የጉምሩክ ቀረጥ አይከፍሉም። እነዚህንና ሌሎች ከታክስ ሕግ ጋር ተያይዘው ያሉ ጉዳዮችን ማጥናትና የፖሊሲ ማሻሻያ ማድረግ የገቢ መጠንን ለማሳደግ መፍትሔ ነው ሲሉም ያብራራሉ። ይህን ማስተካከል ከተቻለ በትንሹ ከጠቅላላው ሀገራዊ ዓመታዊ ምርት አምስት በመቶ ገቢ ማግኘት እንደሚቻል ነው ያስረዱት።

የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመትን ለመሳብ በሚል ሀገሪቷ ከፍተኛ ገቢ እያጣች ነው የሚሉት የምጣኔ ሀብት ባለሙያው፤ ታክስን ከማስቀረት ይልቅ አገልግሎት አሰጣጡን ማዘመንና ቀልጣፋ ማድረግ መፍትሔ እንደሆነ ይናገራሉ። እሳቸው እንዳሉት፤ የኢንቨስትመንት ካባቢን ጤናማ በማድረግ ቀልጣፋ፣ ግልጽና ከሙስና የጸዳ አገልግሎት ማግኘት የኢንቨስተሮች ምርጫቸው መሆኑን ጠቅሰው፣ ይህም በጥናት የተረጋገጠ ነው ይላሉ።

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው እንዳሉት፤ የዜጎች የገቢ አለመመጣጠን ከገቢ ግብር አሰባሰብ ክፍተት ጋር ተያይዞ የመጣ ነው፤ መንግሥት በተለይም ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ላይ ሰፊ ርብርብ በማድረግ እንዲሁም ታክስ በሚሰውሩና በሚያጭበረብሩት ላይ ደግሞ አስፈላጊውን ርምጃ በመውሰድ ገቢውን ማሳደግ ይችላል። ከዚህ በተጨማሪም ግብር ከፋዩ ግብር ሲከፍል ቀልጣፋ አገልግሎት ማግኘት ያለበት ቢሆንም፣ እርካታው ዝቅተኛ ነው ሲሉ ጠቅሰው፣ የግብር ከፋዩን እርካታ ለማሳደግ ቀልጣፋና ምቹ አገልግሎት መስጠት እንደሚገባ አስታውቀዋል። ሰዎች በፍላጎትና በታማኝነት ግብርና ታክስ መክፈል እንዲችሉ ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ መሠራት እንዳለበትም አጽንኦት ሰጥተው ተናግረዋል።